ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን
Mathiwos Wondu Foundation

# ፍርቱና FERTUNA

4ተኛ ዕትም

www.mathiwos.org




## መሪር የቤተሰብ ሀዘንን ወደ ስኬት የቀየረ

# ታሪካዊ ተልዕኮ!



## የመፅሔታችን ስያሜ

# ፍርቱና የሆነበት ምክንያት

ፍርቱና መሳይ የካንሰር ታማሚ ሆና ወደ ማዕከላችን ስትመጣ የ12 ዓመት ታዳጊ ነበረች፡፡ ህክምናዋን በምትከታተልበት ወቅት እንደሌሎቹ ህፃናት ወደ ቤተሰቦቿ መሄድ ባለመቻሏ በማዕከላችን እንደትቆይ ተደርጎ ህመሙ ፋታ ሲሰጣት ጀምራ ያቋረጠችውን  ትምህርት እንድትቀጥል ተደርጎ ነበር፡፡

በወቅቱ ከህመሟ ጋር እየታገለች ትምህርቷን በአዲስ ራዕይ ት/ቤት በነፃ እንድትከታተል ትምህርት ቤቱ ፈቅዶልን ትምህርቷን በሚገባ እየተከታተለች በሚኖራት ትርፍ ጊዜ እንደ ዕድሜ እኩዮቿ መጫወት ሳያምራት ለፋውንዴሽናችን ያላትን ፍቅር ለመግለፅ የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን ሰርታ አበርክታለች፡፡

ምንም እንኳ ከህመሟ አገግማ ሃኪም የመሆን ህልሟን እንድታሳካ የተቻለንን ሁሉ ብናደርግም ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ ይሁንና በአካል ከዚህ ዓለም በሞት ብትለየንም ፈገግታዋ፣ ደግነቷና ፍቅሯ አብሮን ለዘለዓለም ይኖራል፡፡

እኛም ለሷና ለሌሎች ህፃናት ያለንን ልዩ ፍቅርና ክብር ለመግለፅ ስንል የፋውንዴሽናችንን መፅሔት በስሟ «ፍርቱና» ተብሎ እንዲጠራ አድርገናል፡፡ የስሟም ትርጓሜ መልካም ዕድል እንደማለት ነው፡፡ የኛም ጊዜ ደርሶ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተን እንደገና እስከምንገናኝ ድረስ ፈጣሪ አምላክ ነፍሷን በአፀደ ገነት እንዲያኖርልን እንፀልያለን፡፡

# ማውጫ


ፍርቱና

2 የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን አጋር ድርጅቶች

4 ምስጋና

5 የፋውንዴሽናችን ኃላፊዎች መልዕክት

9 እናስተዋውቃችሁ ወ/ሮ ሚዛን ወንዱ

14 የበጎ ሰው ሽልማት ለማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ደራሲና ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ

16 ከመስራቾች አንደበት

22 የፋውንዴሽናችን አስተዋፅኦ

25 የእንግዳችን መልዕክት ዶ/ር ንጉሡ ለገሰ

26 ፋውንዴሽናችንን እናስተዋውቅዎ

28 የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ዳይሬክተር አስተያየት

30 የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ፕሮጀክቶች

35 የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የኦፕሬሽን ዳይሬክተር አስተያየት

38 ጤናማ አፍሪካ

46 የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ሃብት ማሰባሰብ፣ አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አስተያየት

51 ፓንጋሲሌ የማህበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ ማዕከል

53 የካንሰር ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው አስተያየት ማፓዎ አይበገሬዋ ቀንበጥ

61 ፋውንዴሽናችን ያገኛቸው ዐበይት ሽልማቶች

# የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን አጋር ድርጅቶች

## የወጪ አገር

## የአገር ውስጥ

Addis Ababa City Finance Bureau

AAFDA

Addis Ababa University

ALTA Computec

amref health africa

ANRS HEALTH BUREAU

OROMIA HEALTH BUREAU

CCRDA Consortium of Christian Relief & Development Associations

CHEMTEX

CLINTON HEALTH ACCESS INITIATIVE

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ Commercial Bank of Ethiopia

ዳሸን ባንክ Dashen Bank

DOCTORS WITH AFRICA CUAMM

EFDA ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ethio telecom

Ethiopian Public Health Institute

Ethiopian Thoracic Society

FDRE Authority for Civil Society Organizations

Marriott EXECUTIVE APARTMENTS

Mary Joy Ethiopia Since 1994

MCDO

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

MULMUL BREAD

psi Ethiopia

RESOLVE TO SAVE LIVES

SHERATON ADDIS HOTEL ADDIS ABABA

St. Paul's Hospital Millennium Medical College

ጥቁር አንበሳ TIKUR ANBESSA

USI UNITED SYSTEM INTEGRATORS

World Health Organization Ethiopia

ዘመን ባንክ Zemen BANK

# መእጋና

ይህ ዓመት ለማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የሌላ ምዕራፍ መንደርደሪያ ነው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን 10ሺህ ካሬሜትር መሬት ሰጥቶን አስፈላጊውን ህጋዊ ስነስርዓት አሟልተን በመረከብ ላይ እንገኛለን ። ገንብተን የማህበረሰባችንን ጤና እንደምንጠብቅና ለአገራችንና ለወገናችን እጅግ ጠቃሚ ፕሮጀክት መሆኑ ስለታመነበት በጣም እናመሰግናለን። ይህ እንዲሆን ለፈቀዱልን ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ (ዶ/ር)ና ለክብርት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ ጉዳዩ ለሚመለከታቸውና በልዩ ልዩ መንገድ ድጋፍ ላደረጉልን ሁሉ የከበረ ምስጋና እናቀርባለን። ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በህፃናት ላይ የሚከሰት ካንሰርን እንደመነሻ አድርጎ የጀመረ የበጎ አድራጎት ድርጅት ቢሆንም ላለፉት 22 አመታት የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት ሌሎች የካንሰር አይነቶች፣ የተለያዩ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችና አጋላጭ ምክንያቶቻቸው ላይ እየሰራ ይገኛል። ተልዕኳችን እየሰፋ ሲሄድ፣ የቀድሞ ስማችን የስራችንን ስፋት ሙሉ በሙሉ እንደማይገልፅ ለመረዳት ችለናል። ይህንንም ታሳቢ በማድረግና ማህበረሰቡን የማገልገል አላማችንን የበለጠ ለማሳደግ ስያሜያችን ወደ ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን አሻሽለናል።

አዲሱ አርማችን ደግሞ **“ማ”** ና **“ወ”** የሚሉት የአማርኛና **"M"** ና **"W"** የሚሉትን የእንግሊዝኛ ፊደላት ላይ የተመሰረተ ሲሆን የልብ ቅርጽና የሰው ምስሎችን ያካትታል። ይህም ለሰብዓዊነት የተቋቋመ ድርጅት መሆኑንና የማ.ወ.ፋ መሠረታዊ እሴቶች የሆኑትን **ትብብር፣ እንክብካቤንና ፍቅርን** ያመለክታል።

ሁለቱ ትልልቅ አረንጓዴ ምስሎች ማ.ወ.ፋ የሚሰጠውን አጠቃላይ ድጋፍ የሚያመለክቱ ሲሆን ትንንሾቹ ወርቃማ ምስሎች ደግሞ የምናገለግላቸውን ልጆችና ማህበረሰቡን በሚወክል መልኩ ተቀይሯል። አርማው ላይ የሚታየው ወርቃማ ቀለም በአለም አቀፍ መድረኮች የሕፃናት ካንሰርን፣ ተስፋና አልበገር ባይነትን በመወከል በሰፊው ይታወቃል። ይህም ማ.ወ.ፋ የተቋቋመበትን አላማ እንዲሁም እንደ ማቲዎስ ከካንሰር ጋር የሚታገሉ ሕፃናትን መደገፍ ላይ ትኩረት አድርገን መስራታችንን ያሳያል። አረንጓዴው ቀለም ደግሞ ጤናን የአካባቢን ልምላሜና ዕድገትን ሲወክል ከሥነ ምህዳር ተስማሚና ዘላቂ የሆኑ የማህበረሰብ ጤናን የሚያስጠብቁ ስራዎችን እንደምንሰራ ያመላክታል። ከውስጥ ያለው ወርቃማው ቀለም በአረንጓዴ ቀለም መከተሉ ፋውንዴሽኑ ከህፃናት ካንሰር በመነሳት ሰፊና ሁሉን አካታች ወደ ሆነው የምልአተ ጤና ትኩረቱን እያሰፋ መሄዱን ያሳያል።

ይህ ስያሜና አርማ ድርጅቱን ወካይና ፋውንዴሽኑን በሃገር አቀፍና አለም አቀፍ መድረኮች የሚያስተዋውቅ እንዲሆን በማዕከላችን የሚደገፉትን ህፃናትና ቤተሰቦቻቸውን፣ የድርጅቱ ቦርድ አባላትን፣ ሰራተኞችን እንዲሁም አጋር ድርጅቶችን ግብአት ባካተተ መልኩ ተዘጋጅቷል። ለዚህም ሃሳብ በመስጠት የተባበራችሁንን ሁሉ እናመሰግናለን።

**ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ማቲዎስ ወንዱ - የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ በሚለው መጠሪያው ማህበረሰቡን እንዲያገለግል ድጋፍ ያደረጋችሁ ተቋማትና ግለሰቦችን ሁሉ እናመሰግናለን። ጤና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን፣ የክልል ጤና ቢሮዎች፣ የፋውንዴሽናችን አባላትና በጎፈቃደኞች እንዲሁም የቦርድ አባላትና ሰራተኞች ካለፉት ጊዜያት በበለጠ ድጋፍ እንደምታደርጉልን በመተማመንን ለማህበረሰባችን ጤና በአዲስ ምዕራፍ አብረን እንቁም በማለት ጥሪያችንን እናቀርባለን።**

የፍርቱና መፅሔት አዘጋጆች
ዋና አዘጋጅ -ወ/ሮ አዜብ ታምሩ
ህትመት - እሥራኤል ማተሚያ ቤት

በማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ሃብት ማሰባሰብ፣ አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ተጋጅቶ የቀረበ
ኢሜል ICT@mathiwos.org
azebt@mathiwos.org
ስልክ +251 118 122838
ፓ.ሳ.ቁ. 80571
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን
Mathiwos Wondu Foundation



# የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ መልዕክት

**ዶ/ር ኩኑዝ አብደላ**
**የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ**

ከሁሉ አስቀድሜ የፋውንዴሽናችን 22ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ለማክበር በመቻላችን ለፋውንዴሽናችን ህብረተሰብ እንኳን ደስ አላችሁ ደስ አለን ለማለት እወዳለሁ፡፡ ፋውንዴሽናችን የተቋቋመባቸውን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢውን ህግና በየፕሮጀክቱ የሚገባቸውን ስምምነቶች በማክበርና በመፈፀም በተለይ ከጤና ሚኒስቴር፣ ክልል ጤና ቢሮዎችና ከኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣንና አጋር ድርጅቶች ጋር ተቀናጅተን በመሥራታችን ዛሬ ፋውንዴሽናችን እጅግ በጣም የታመነና የተከበረ ለመሆን በቅቷል፡፡ በዚህም ባለፉት 8 ዓመታት ውስጥ 6 ዓለም አቀፍና 3 አገር አቀፍ በድምሩ 9 ሽልማቶችን ለማግኘት በቅቷል፡፡

የፋውንዴሽናችንን 21ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መጋቢት 10 ቀን 2018 ዓ.ም በተሳካ ሁኔታ አካሂደናል፡፡ በዚህም የፋውንዴሽኑን 2025 በጀት ዓመት የሥራ አፈፃፀም በውጭ ኦዲተር የተመረመረውን የሂሣብ መግለጫና የ2026 በጀት ዓመት በጀት እንዲሁም የድርጊት መርሐ ግብር ዕቅድ አፅድቀልናል፡፡ ባለፈው ስብሰባ ሳይጠበቅ የፋውንዴሽናችን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፋውንዴሽናችንን ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በስብሰባው ላይ ባለመገኘታቸውና ለአፋጣኝ ህክምና ወደ ህንድ አገር መሄዳቸው መደናገጥን የፈጠረ ቢሆንም ህመሙንና ህክምናውን ለመቋቋም በሚያደርጉት ጥረት ተበረታተናል፡፡ ህክምናቸውን በተሣካ ሁኔታ አጠናቀው በሙሉ አቅም ወደ ሥራ ገበታቸው በመመለሳቸውና ስብሰባውን በንቃት በመሳተፋቸው የተሰማንን ጥልቅ ደስታና እርካታ እንገልፃለን ፡፡

የፋውንዴሽናችን መጠሪያ ስም ረዘም ያለና በአሁኑ ወቅት በመሥራት ላይ ከምንገኘው ሥራ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ አጠር አድርገን ማቲዎስ ወንዱ ፈውንዴሽን ተብሎ እንዲጠራና መለያውም ወይም ሎጎውም እንዲለወጥ ተደርጓል፡፡ ይህን የተሻሻለ መጠሪያና መለያ የማስተዋወቅ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሠጥቶት እንዲሠራ በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡ ፋውንዴሽናችን ለሚቀጥሉት 5 ዓመታት የሚመራበትን ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ ይኽም ፋውንዴሽናችንን ይበልጥ ውጤታማ ሆኖ እንዲቀጥል ያደርገዋል፡፡ ዕቅዱ ፀድቆ እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 ቀን 2026 እስከ 2030 ድረስ የሚሸፍን ሲሆን ከዚህ በፊት ከነበሩት 3 ዕቅዶች በተለየ ጥራት እንዲሠራ የፋውንዴሽኑ ሠራተኞች ላደረጉት ጥረት ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

**የጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክትን ተግባራዊ ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረትና እየታየ ያለው ውጤት የሚያበረታታ ቢሆንም ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ይኽ ፕሮጀክት በአገሪቱ በጤናው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ አቅም የሚፈጥርና በህክምና ቱሪዝም ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርግ እንዲሁም ለፋውንዴሽናችን ዘላቂ ህልውና ወሳኝ ሚና የሚጫወት በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ለአፈፃፀሙ ሁላችንም ተባብረንና ተቀናጅተን መሥራት ይጠበቅብናል። ለዚሁም ለመላው የፋውንዴሽናችን ቤተሰብ አበክረን ጥሪ እናቀርባለን።**

በመጨረሻም ለረዥም ጊዜ በጉጉት ስንጠብቀው የቆየነው ተሳክቶ 10,000 ካሬ ሜትር ቦታ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተሰጥቶናል፡፡ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልተን መሬቱን በመረከብ ላይ እንገኛለን፡፡ ይህ እንዲሆን ለፈቀደው ፈጣሪ አምላክ፣ በልዩ ልዩ ሁኔታ ትብብርና ድጋፍ ላደረጉልን ሁሉ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ፋውንዴሽናችን እዚህ ደረጃ እንዲደርስ በተለያዩ አማራጮች ትብብርና ድጋፍ በማድረግ ላይ ለሚገኙት አጋሮች በፋውንዴሽናችን ሥራ አመራር፣ አባሎች፣ ሠራተኞች፣ ህሙማንና ቤተሰባቸው ስም የከበረ ምስጋና እያቀረብኩ፤ ድጋፋቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቀርባለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚም 2026 በጀት ዓመት የሰላም፣ የጤናና የብልፅግና እንዲሆንልን እመኛለሁ፡፡ **አመሰግናለሁ**!!

# የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት



**ዶ/ር የትናየት አበበ**
**የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ**

ከሁሉ አስቀድሜ የፋውንዴሽናችን 22ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ለማክበር በመቻላችን ለፋውንዴሽናችን ህብረተሰብ እንኳን ደስ አላችሁ፣ ደስ አለን ለማለት እወዳለሁ፡፡

**ፋውንዴሽናችን የተቋቋመባቸውን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢውን ህግና በየፕሮጀክቱ የሚገባቸውን ስምምነቶች በማክበርና በመፈፀም በተለይ ከጤና ሚኒስቴር፣ ክልል ጤና ቢሮዎችና ከኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣን፣ አጋር ድርጅቶች ጋር ተቀናጅተን በመሥራታችን ዛሬ ፋውንዴሽናችን እጅግ በጣም የታመነና የተከበረ ለመሆን በቅቷል፡፡ በዚህም ባለፉት 8 ዓመታት ውስጥ 6 ዓለም አቀፍና 3 አገር አቀፍ በድምሩ 9 ሽልማቶችን ለማግኘት በቅቷል፡፡**

የፋውንዴሽኑን ስም በአሁኑ ወቅት ከሚሠራቸው ሥራዎችና ዓላማዎች ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ፣ ቀለማትና አርማ/ሎጎ፣ የፋውንዴሽኑን ድርጅታዊ አቋምና ሥርዓት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨባጭ የሆነ የሠራተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘናና የማትጊያ ሥርዓት (Performance Management & Reward System) የኃላፊነትና ስልጣን ውክልና (Delegation) ፣ የመተካኪያ ሥርዓት (Succession Plan) የሥራ አመራር ቦርድ የሥነ ምግባር ደንብ (Board Ethics Policy)፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ መመሪያ (Management Manual)፣ የሀብት ማሰባሰብ፣ አጋርነትና የህዝብ ግንኙነት መመሪያ (Resource Mobilization, Partnership and Communication Manual) በተጨማሪም የሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence – AI)፣ የወረቀት ሥራና በሰዎች ስህተት የሚፈጠሩ ችግሮችን በእጅጉ የሚቀንሰውና የሥራ ሂደትን በሚያቀላጥፈው የድርጅት ግብአት ዕቅድ (Enterprise Resource Planning – ERP) በአማካሪ ድርጅት አስጠንተን ሥራ ላይ ለማዋል ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡

ይኽ ተግባራዊ ሲሆን ፋውንዴሽናችን ይበልጥ ግልፀኝነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ሥራዎቹን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመሥራት ያስችለዋል፡፡ ሠራተኞቹም ተረጋግተውና እርግጠኛ ሆነው ሥራቸውን ለመሥራት ይረዳቸዋል፡፡ ፋውንዴሽናችን ለሚቀጥሉት 5 ዓመታት የሚመራበትን ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ ይኽም ፋውንዴሽናችን ይበልጥ ውጤታማ ሆኖ እንዲቀጥል ያደርገዋል፡፡ ዕቅዱ የፀደቀ ሲሆን እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 ቀን 2026 እስከ 2030 ድረስ የሚሸፍን ሲሆን ከዚህ በፊት ከነበሩት 3 ዕቅዶች በተለየ ጥራት እንዲሠራ የፋውንዴሽኑ ሠራተኞች ላደረጉት ጥረት ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ከፋውንዴሽናችን መሥራቾች አንዱና የፋውንዴሽናችን ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ወንዱ በቀለ ሳይጠበቅ የኮላንጂዮካርሲኖማ ህመም እንደያዛቸው በመታወቁ በሀኪሞች በተሰጠው አስተያየት መሠረት በአስቸኳይ ወደ ህንድ አገር ሄደው ሙሉ ወጪያቸው ተሸፍኖ የሚታከሙበት ምቹ ሁኔታ ፈጥረናል፡፡ በዚህም ህክምናቸውን ሲከታተሉ ቆይተው የተቀረውን እዚሁ ለመከታተል በቅተዋል፡፡ በዚህም ህክምናቸውን አጠናቀው በሙሉ ጤና ወደ ምድብ ሥራቸው እንደሚመለሱ እምነታችን የፀና ነው፡፡

በመጨረሻም ለረዥም ጊዜ በጉጉት ስንጠብቀው የቆየነው የመሬት ይዞታ ጥያቄ ተገቢውን መልስ አግኝቶ 10,000 ካሬ ሜትር ቦታ ተሠጥቶን በመረከብ ላይ በመሆናችን እንኳን ደስ አላችሁ ደስ አለን እላለሁ፡፡ ይህም እንዲሆን ለፈቀደው ፈጣሪ አምላክ፣ በልዩ ልዩ መንገድ ለተባበሩን ሁሉ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ፋውንዴሽናችን እዚህ ደረጃ እንዲደርስ በተለያዩ አማራጮች ትብብርና ድጋፍ በማድረግ ላይ ለሚገኙት በፋውንዴሻችን ሥራ አመራር፣ አባሎች፣ ሠራተኞች፣ ህሙማንና ቤተሰባቸው ስም የከበረ ምስጋና እያቀረብኩ፤ ድጋፋቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቀርባለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚም 2026በጀት ዓመት የሰላም፣ የጤናና የብልፅግና እንዲሆንልን እመኛለሁ፡፡



# የዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት

**ወንዱ በቀለ**
**ዋና ሥራ አስፈፃሚ**

ከሁሉ አስቀድሜ የፋውንዴሽናችን 22ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ለማክበር በመቻላችን ለፋውንዴሽናችን ህብረተሰብ እንኳን ደስ አላችሁ አለን ለማለት እወዳለሁ።

ማቲዎስ ወንዱ በደም ካንሰር ህመም በ4 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ በቤተሰቡ ላይ የተፈጠረውን እጅግ መራር ሀዘን ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር በማቲዎስ ወንዱ መኖሪያ ቤት የተቋቋመው ፋውንዴሽናችን ዛሬ 22 ዓመት ሆኖታል። በዚህኑ ጊዜ ለ6 ዓመት ያለአንዳች አስተዳደራዊ ወጪ በማቲዎስ ወንዱ ቤተሰቦች መኖሪያ ቤት ሲሰራ ቆይቶ በአሁኑ ወቅት ከ1,800 በላይ አባላትን፣ ከ500 በላይ የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች (Volunteers)፣ 43 ሠራተኞች በመያዝ 10 ፕሮጀክቶችን ሥራ ላይ በማዋል ላይ ይገኛል። ከእነዚህም ውስጥ 1 በሕፃናት ካንሰር፣ 3 በትምባሆ፣ 3 በሳንባ ካንሰር፣ 1 ፔንፕላስ፣ 1 በምግብ ፖሊሲና 1 ቀጣይነት ባለው የባለሙያ አቅም ግንባታ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።

ፋውንዴሽናችን የተቋቋመባቸውን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢውን ህግና በየፕሮጀክቱ የሚገባቸውን ስምምነቶች በማክበርና በመፈፀም በተለይ ከጤና ሚኒስቴር፣ ክልል ጤና ቢሮዎችና ከኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣን፣ እንዲሁም አጋር ድርጅቶች ጋር ተቀናጅተን በመሥራታችን ዛሬ ፋውንዴሽናችን እጅግ በጣም የታመነና የተከበረ ለመሆን በቅቷል። በዚህም ባለፉት 8 ዓመታት ውስጥ 6 ዓለም አቀፍና 3 አገር አቀፍ በድምሩ 9 ሽልማቶችን ለማግኘት በቅቷል። የፋውንዴሽናችንን ህልውና አጠናክሮ ለማስቀጠል እንዲቻል የተለያዩ የአቅም ግንባታ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ እንገኛለን፡፡

ከእነዚህም መካከል ጤናማ አፍሪካ የተባለ ፕሮጀክት አበልፅገንና በአማካሪ ድርጅት የአዋጪነት ጥናት አካሂደን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰጡንን አስተያየቶች አጢነን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ጥያቄ አቅርበን 10,000 ካሬ ሜትር መሬት ተሰጥቶናል:: ለዚህም የከተማ አስተዳደሩን እናመሰግናለን።

**የፋውንዴሽኑን ስም በአሁኑ ወቅት ከሚሠራቸው ሥራዎችና ዓላማዎች ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ፣ ስያሜው እንዲሻሻልና ቀለማትና አርማ/ሎጎ እንዲለወጥ አድርገናል ፣ የፋውንዴሽኑን ድርጅታዊ አቋምና ሥርዓት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨባጭ የሆነ የሠራተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘናና የማትጊያ ሥርዓት** (Performance Management & Reward System)**፣ የኃላፊነትና ስልጣን ውክልና** (DelEgation) **፣ የመተካኪያ ሥርዓት** (Succession Plan)**፣ የሥራ አመራር ቦርድ የሥነ ምግባር ደንብ** (Board Ethics Policy)**፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ መመሪያ** (Management Manual)**፣ የሀብት ማሰባሰብ፣**

**አጋርነትና የህዝብ ግንኙነት መመሪያ** (Resource Mobilization, Partnership and communication Manual)፣ **በተጨማሪም የሰው ሰራሽ አስተውሎት** (Artificial Intelligence – AI)፣ **የወረቀት ሥራና በሰዎች ስህተት የሚፈጠሩ ችግሮችን በእጅጉ የሚቀንሰውና የሥራ ሂደትን በሚያቀላጥፈው የድርጅት ግብአት ዕቅድ** (Enterprise Resource Planning – ERP) **በአማካሪ ድርጅቶች አስጠንተን ሥራ ላይ ለማዋል ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን።**

**ይኽ ተግባራዊ ሲሆን ፋውንዴሽናችን ግልፀኝነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ሥራዎቹን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመሥራት ያስችለዋል። ሠራተኞቹም ተረጋግተውና የበለጠ እርግጠኛ ሆነው ሥራቸውን ለመሥራት ይረዳቸዋል።**

እንደማንኛውም ጊዜ የጤና ምርመራ በማካሂድበት ወቅት ሳይጠበቅ የህሞት ከረጢት ባስወጣሁት አካባቢ ኮላንጂዮካርሲኖማ (CholangioCarcinoma)የሚባል የካንሰር  ሕመም እንዳለብኝ በመታወቁ ለከፍተኛ ሕክምና ወደ ህንድ አገር ሄጄ  ለሶስት ወራት ስታከም ቆይቼ ተመልሻለሁ።

ይኸም እኔ ከአሁን በፊት ማቲ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ እንዳደረኩት፤ በአንድ ወቅት ለመያዝ በተገደድኩባቸው በትምባሆና ካንሰር ሥራዎቼ መካከል ተቃርኖ ሲፈጠር ካንሰርን እንደመረጥኩት ሁሉ ይኸንንም እንደመልካም አጋጣሚ ወስጄዋለሁ።

በዚህም  ከፋውንዴሽኑ መሥራቾች አንዱና የፋውንዴሽኑ ሥራ አስፈፃሚ ሆኜ በተጨማሪ የካንሰር ህመምተኛ መሆኔ ከ22 አመት በላይ ሳገለግላቸው የቆዩት የካንሰርና ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው ከህመሙ ጋር ያላቸው ግብግብ ምን እንደሚመስል በተጨባጭ ለማወቅና ለመገንዘብ አስችሎኛል። ይኸም ህሙማኑንና ቤተሰቦቻቸው ይበልጥ እንዳገለግል ይረዳኛል። በዚህ አጋጣሚም ህክምናዬን በአገር ውስጥና በውጭ አገር የምታከምበትን  ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ የፋውንዴሽናችን ሥራ አመራር ቦርድና የፋውንዴሽናችን ሠራተኞች ተገቢውን ትብብርና ድጋፍ እንዲያደረግልኝ ሀሳብ በማቅረብና ገንዘብ በማዋጣት ላደረጉልኝ እርዳታ ከልብ አመሰግናለሁ።

ፋውንዴሽናችን ለሚቀጥሉት 5  ዓመታት የሚመራበት ስትራቴጂክ ዕቅድ ፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ተወስኖአል ። ይኽም ፋውንዴሽናችን ይበልጥ ውጤታማ ሆኖ እንዲቀጥል ያደርገዋል። ዕቅዱ እ.ኤ.አ ከጀነዋሪ 1 ቀን 2026 እስከ 2030 ድረስ የሚሸፍን ሲሆን ከዚህ በፊት ከነበሩት 3 ዕቅዶች በተለየ ጥራት እንዲሠራ የፋውንዴሽኑ ሠራተኞች ላደረጉት ጥረት ምስጋና አቀርባለሁ።

በመጨረሻም ፋውንዴሽናችን እዚህ ደረጃ እንዲደርስ በተለያዩ አማራጮች ትብብርና ድጋፍ በማድረግ ላይ ለሚገኙት የፋውንዴሽናችን ሥራ አመራር፣ አባሎች፣ ሠራተኞች፣ ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው ስም የከበረ ምስጋና እያቀረብኩ፤ ድጋፋቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቀርባለሁ። በዚህ አጋጣሚም 2026 በጀት ዓመት የሰላም፣ የጤናና የብልፅግና እንዲሆንልን እመኛለሁ።

**አመሰግናለሁ!!**



# እናስተዋውቃችሁ

**ወ/ሮ ሚዛን ወንዱ**
የአቶ ወንዱ በቀለ ሁለተኛ ልጅ

### ራስሽንና የቤተሰብ ሁኔታ አስተዋውቂን

አመሰግናለሁ የቤተሰብ ሁኔታ ባለትዳርና የሁለት ወንድ ልጆች እናት ነኝ፤ የትምህርት ደረጃ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽንና ኢንፎርሜሽን ሲስተም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢኤ ዲግሪ ምሩቅ ነኝ፤ የሥራ ሁኔታ ደግሞ የግል ሥራ ከባለቤቴ ጋር እንሰራለን ።

### እናትና አባትሽ ምን አይነት ሰዎች ናቸው በቤተሰብ በአካባቢ?

ሁለቱም ለኔ ያው በጣም ጥሩ እናትና አባት ናቸው። ማሚ እውነተኛ የእናት ምሳሌ ናት። የእናት ባህሪያት ያሏት መልካም ሴት ነች። ወንድዬም በጣም ጥሩ አባት ነው እሱም ደግሞ እንደ ወንድ በሥራው በአካባቢው ላይ ጠንካራ የወንድ ምሳሌ የምትይው አይነት ሰው ነው። በማህበራዊ ተሳትፏቸው በዕድር በቤተክርስቲያን ስለሚሣተፍ ማዳላት እንዳይሆን ብዙውን ነገር የቤቱን ሥራ ማሚ ነች የምትሸፍነው፤ እሱ በሥራ ላይ በጣም ስለሚጠመድ ግን በተቻለው አቅም ዕድርም ላይ ቤተክርስቲያንም ላይ ለመሳተፍ ይሞክራል። ግን በጣም መገኘት ባለበት ቦታ ላይ የማይቀር ሰው ነው።

**በበዓላት እንግዳ ሲመጣ**
**የእናንተ ቤት ምን ይመስላል?**

አውዳመት ጠዋት ላይ ብዙ ጊዜ የምናሳልፈው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ነው። ከዛ ከተመለስን በኋላ ደግሞ ከሰአት የቤተሰብ ፕሮግራም ይቀጥላል። አካባቢያችን ብዙ ቤተሰቦች የልጅ ልጆችም፣ ጎረቤትም ሰብሰብ ብለን በጥሩ ሁኔታ እናሳልፋለን፤ ግን ያው ዋናው በዓል በተለይ ለወንድዬ ትልቁ በዓሉ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሚያደርገው ስለሆነ ከዛ በኋላ ያለውን ደግሞ ደስ ብሎን በጣም ሰብሰብ ብለን በተለይ የእራት ፕሮግራም አለን የቤተሰብ ፕሮግራም ከዛ ላይ በቃ በጣም ደስ የሚል ፕሮግራም እናሳልፋለን ።

**ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በማቲ ምክንያት ነው የተመሰረተው ፤ ማቲ ደግሞ አንቺ ከተወለድሽ ከአስር አመት በኋላ ነው የተወለደው**
**እና እስቲ ሲወለድ የነበረውን ነገር ንገሪኝ?**

ማቲ ቆይቶ እንደመወለዱ ለረጅም ጊዜ የነበርኩት ትንሽ ልጅ እኔ ነበርኩ። የሁሉም ትኩረት ወደኔ ነበረ፤ እሱ ደግሞ ሲመጣ ያው አዲስ ልጅ በመምጣቱ በጣም አጓጉቶን ነበረ። ድሮ ከምንኖርበት ሰፈር ወደ አዲሱ ቤታችን ለመቀየር በጣም ትልቅ ዝግጅት ነበር፤ እና ሁሉም ነገር በጣም አዲስ ነበረ፤ ብዙ ደስታዎች ነበሩት። አዲስ ቤት ጥሩ ተለቅ ያለ ቤት መግባታችንም ለእኛ በጣም ትልቅ ደስታ ነበር፤ እና የነበረው ጊዜ ያው ታናሽነቴን መቀማቱ እንዳለ ሆኖ ግን በቃ በጣም ትልቅ ደስታ ነበረ። አባቴም እናቴም ላይ የነበረው ነገር ወንድሜ ዮኒም በጣም ደስ ብሎን ነበር የተቀበልነው። ለረጅም አመታት እኔ ነበርኩኝ የመጨረሻ ልጅ ሴትም ስለነበርኩኝ የተለየ እንክብካቤ የተለየ ትኩረት ይደረግልኝ ነበር። ለረጅም ጊዜ የነበረ ነገር ሲቀር የሁሉም እንክብካቤ ወደ ማቲ ሲዞር በቃ ተረሳሁ የሚል ስሜት መጣና በቃ ረሳችሁኝ እያልኩ አሾፍ ነበር፤ ግን በጣም ነበር ማቲዬን የምወደው።

**ምን አይነት ልጅ ነበር ማቲ**
**በተለይ እስከ ሁለት ዓመቱ?**

ማቲ በጣም ንቁ ነበር፤ ተጫዋች ነው። የራሱ ቃላቶች ነበሩት ብዙ ጊዜ አብረነው ስለምንውል ከኔጋ ቅርበት ነበረው። ሌሎቹ የሚለውን አይሰሙትምና ቃላት ራሱ አንዳንዱን ይጠይቁናል፤ አፉ ኮልታፋ ነበረ። ማቲዬ ደስ የሚል ለቤታችን አዲስ ህይወት የዘራ ልጅ ነበረ። ለማብላት፣ ለማጫወት፣ ለማስተኛት ሴትም እንደመሆኔ በደንብ እንከባከበው ስለነበር የማይረሱ ትዝታዎች አሉት።

የመጀመሪያ ቃሉ ትዝ የሚለኝ ሶኬት ሊሰካ ሲሞክር ማሚ በጣም ደንግጣ "አንተ ይደረጋል ?" ስትለው ገና አፉን አልፈታም ነበርና "አይደረግም" ብሎ በጣም አስደንግጦናል። ዘፈን ላይ ደግሞ "ያስብሻል ልቤ..." የሚለውን ዘፈን በጣም ደጋግሞ ይዘፍን ነበረ። ልቤ ፋና የሚባል ትምህርት ቤት ነበር እና እሱን በጣም ደጋግሞ ያነሳ ነበረ ። በጣም ጨቅላ ህፃን ነበር እና አሳ እንዲበላ ይፈለግ ነበር እና አሳ ብላ ምናምን ሲባል "እ አሳ ነው እንዴ....?" ብሎ አልበላም ይላል እና እኛ በቃ መሸወዳችን ነው እና ምንድነው ምታበይው ሲሉኝ ፊሽ ነው ስል እንዴ አሳ ነው እንዴ ምታበይኝ ብሎ አልበላም ያለበት ጊዜ ራሱ ትዝ ይለኛል ፤ ብዙ ትዝታዎች አሉን ።

**ከዛ በኋላ ሲታመም ምን ተፈጠረ ?**

ህመሙ ሲጀምረው ከኋላ እግሩ ላይ የሆነች እንደ ቁስል አይነት ነገር ወጣበት። በጣም ጤነኛ አክቲቭ ልጅ ስለነበረ ወይ አለርጂ ወይ የሆነ ነገር ነው በሚል ነው እነ ማሚ ሆስፒታል ይዘውት ይመላለሱ የነበረው፤ እና ቀላል ነገር ነው አድርገን የጠበቅነው ። ነገሮች እየከበዱ ህክምናውም እየበዛ መጥቶ በቃ ቤተሰብም ያለው ጭንቀት እየበረታ መጣ እና ከዛ መጨረሻ ላይ ህመሙ ታውቆ የደም ካንሰር መሆኑን ሲነገረን እኛ አልገባንም። ስለበሽታው እንኳን እኛ ቤተሰቦቻችንም ብዙ እውቀት አልነበራቸውም። ካንሰር የሚለው ነገር አስከፊ እንደሆነ ውስጣችን ሁላችንም ጋር አለ እና በጣም ነበር የደነገጥነው። ማቲዬ ይታመማል እናጣዋለን የሚል ሃሳብ አልነበረም። ህክምናው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሲሆን በጣም እየተጨነቅን መጣን ህመሞቹም እየከፉ መጡ። ህፃን ልጅ እንደዚያ ይታመማል የሚልም ውስጤ ግንዛቤ ኖሮ አያውቅም ከጉንፋንና ከቶንሲል ውጪ.... በጣም ከባድ ጊዜ ነበር በጣም.... ያኔ በዕድሜ ትንሽ ነበርኩኝ።

**በህመሙ ወቅት አእምሮሽ ውስጥ ከቀረው**
**አስቸጋሪው ነገር ምን ነበር?**

የማቲ ቤት ውስጥ አለመኖር፤ ለህክምና ብዙ ጊዜው ጥቁር አንበሳ ያሳልፍ ነበረ፤ ክረምት ነበረና ቤት ውስጥ ከታናሽ ወንድማችን ጋር እናሳልፋለን ብለን ነበር ያሰብነው። በጓጓንለት ጊዜ እሱም እናታችንም የሚያሳልፉት ሆስፒታል ሆነና በጣም ከባድ ነበር። ቤት ውስጥ ወንድማችንን አጥተን ድጋሚ እናቴም አባቴም ሁሌ ሆስፒታል ሲሆኑ ጭንቀት ነው፤ ሃሳብ ነው። ያ በጣም ከባድ ጊዜ ነበር። ነገሮች እየባሱ ማቲ ምግብ ላይ ማስቸገሩ፣ ስለ ህመሙ ከምናውቀው ውጪ መሆኑ፣ ቤት ውስጥ የምንሰማቸው ነገሮች በዛ እድሜ ነገሮች ከአቅም በላይ ነበሩ ።



ማቲን አቅፌ ሳስተኛው ወይም ሳዝለው በጣም ነው ደስ የሚለኝ፡፡ አዝዬው እዛው እያጫወትኩት ወይ እሹሩሩ እያልኩት ይተኛል፡፡ ህመሙ ሲጨምር ያው ውስጡ ብዙ ህመም አለ ምግብ አልበላ ይላል፤ ምቾት አይኖረውም ና በቃ አዝዬው ረጅም ሰአት ነው የምቆመው፤ እኔን ነው የሚፈልገው አዝዬው ስቆም ይደክመኛል፡፡ ከዛ ተኛ ብዬ ልክ ቀስ ብዬ ስቀመጥ እግሩን የሆነ ነገር ሲነካው ይነቃብኛል፡፡ ውስጡም ካለው መረበሽ ስለሆነ ያሳዝነኛል በጣም ….ብዙ ጊዜ አዝለው ነበር….

## ማቲ ያረፈበትን ጊዜ እስቲ አስታውሽን? በመካከሉም ደህና ሆኖ ነበረ አይደል?

ደህና ሆኖ ነበር ፤ ከዛ እንደገና አገርሽቶበት ታመመ፡፡ ማቲ ያረፈው መስከረም 13 1996 ዓ.ም. ነበር፡፡ የዚያን ቀን ወንድዬ ጠንካራ ለመሆን ይሞክራል፤ ከማሚ መደናገጥ ብዙ የምንረዳቸው ነገሮች ነበሩ፡፡ ወንድዬ እዛው ውሎ ነበር የመጣው:: የዛን ሰሞን ለህክምና አሜሪካ እንዲሄድ ፕሮሰስ ተጀምሮለት ነበረ፡፡ ታላቅ ወንድሜ ዮኒ እንዳጋጣሚ የእሱ ዶነር ለመሆን ሊሄዱ ነው በቃ ብቻዬን እሆናለሁ የሚል የሚያስጨንቅ ስሜት ነበረኝ፡፡ እና ግን ያው የወንድሜን መዳን ስለሆነ እጓጓ ነበር፡፡ ሄደው እንዴት ነው ቶሎ የሚመለሱት እያልን በምናስብበት ጊዜ ወንድዬ ማቲ እንዳረፈ ሲናገርና በስልክ ሲጯጯሁ ሰማን፡፡ ቤት ውስጥም ትልቅ ሰው ስላልነበረ ማረፍ ሚባለው ነገር ራሱ ቃሉ አልገባኝም "ምንድነው ማረፍ?" ከወንድሜ ጋር ተረበሽን አለቀስን ከዛ ወንድዬ እዛ አያድርም ስላለ ከትንሽ ሰአት በኋላ እራሱ ነው ይዞት የመጣው፡፡ እና ጥቅልል አድርጎ አቅፎት ነው የመጣው፤ አምጥቶ ራሱ አልጋ ላይ ነበር ያስተኛው፡፡ የሆነ ለየት ያለ ስሜት ነው የተሰማኝ፡፡ ወንድዬም አያለቅስም ማሚ ነች ምታለቅሰው እና በቃ ግን ውስጡ የተናነቀው ነገር ነበር፡፡ እና በቃ እውነት ማቲ መሞቱ ገባኝ ከዛ ያው ቤተሰብ ጎረቤት መሰብሰብ ጀመረ፤ እኔ ልጅም እንደሚሞት ያወኩት የዛኔ ነው፡፡ ከባድ ጊዜ አሳለፍን:: ወንድዬ አያለቅስም ግን ውስጡ በጣም ቁጭት እንዳለ በጣም ያስታውቅ ነበረ፡፡ "በቃ አጣሁት ልጄን…." እያለ ውስጡ የሚታገለው ነገር ነበር፡፡ በንጋታውም ቀብር ሆነ በቃ ቤተሰብም ሁሉም ሰው ተሰብስቦ ሥርዓተ ቀብሩ ተፈፀመ፡፡ በቃ ማቲ ሞተ የሚለውን ነገር ተቀበልን ፡፡

## ባለፉት 21 ዓመታትና አሁንም ወላጆችሽ ላይ ያለው መጽናናትና ብርታት ምን ያህል ነው?

ማቲን እንዳጣነው ካወቅን ሰዓት ጀምሮ ወንድዬ ላይ ያለው ቁጭት በጣም ከባድ ነበር ፡፡ የያዘው ኤ.ኤል.ኤል.ዋን የሚባለው የሉኬሚያ አይነት ተገቢ አይነት ህክምና ቢያገኝ የሚድን አይነት ህመም ነበር፡፡

በዚያ ላይ ማቲ ዕድለኛ ሆኖ ህክምናውንም ለማግኘት የተሻለ ዕድል ነበረውና እግዚአብሔር ስላልፈቀደ ብቻ ያ ስላልሆነ ሁሌ ቁጭት ይሰማዋል ፡፡ መዳን በሚችል ህምም የምትወጂውን ሰው ማጣት በጣም ከባድ ነው፡፡ እንደሱ አይነት ድጋሚ ሰው ባይጎዳ የሚል ሃሳብ ውስጥ መግባት ጀመረ ፡፡ ያው ማሚም በሃይማኖቷ ጠንካራም ስለነበረች እንጂ ልጅ ማጣት በጣም ከባድ ነገር ነው፡፡ ግን በቃ ሁሌ ሁላችንም ጋር ያለው ነገር ማንኛውም ሰው እኛ ያለፍንበትን ነገር ሌላ ሰው ላይ እንዳይደገም በሚል ሁለቱም በጣም ጠንካራ ነበሩ:: እግዚአብሔርም ስለረዳቸው ሁለቱም እየበረቱ ነው የመጡት:: እግዚአብሔርም አጠንክሯቸው ወንድዬ ሃሳቡን እያዳበረ በማቲ ስም ድርጅት ለማቋቋም ወሰነ፡፡

## ፋውንዴሽኑን ቤት ውስጥ ሲመሰረት የፈጠረብሽ ስሜት አለ? ያንቺም የዮናስንም አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር ይባላል?

ያኔ እንደዚህ አይነት ድርጅት አናውቅም ነበረ፡፡ እውነትም የሚሆን አይመስልም:: ለምን ወንድዬም ተቀጥሮ ነበር የሚሰራው፤ ማሚም እንደዛው እንዴት ከዛ ተነስተው ሰው ይረዳሉ የሚለው የማይሆን ሃሳብ ሚያስብ ሁላ ይመስለን ነበር፡፡ ቀስ በቀስ አጠገቡም ጥሩ ጓደኞችም ቤተሰቦችም ስለነበሩት ሃሳቡን እያካፈለ ነገሮችን እያስተካከለ መስራት ቀጠለ፡፡ ወንድዬ ካሰበ የሚሰራ አይነት ሰው ነው፡፡ አንድ ነገር ለመጀመር ጊዜ ሊወስድበት ይችላል እንጂ ከጀመረ በቃ በአግባቡ የሚሰራ አይነት ሰው ነው፡፡ እና ያ ነገር ከሃሳብ አልፎ ወደ ወረቀት ከዛም ሃሳቡ በደንብ እየተስተካከለለት ሥራው ቀጠለ፡፡ የምስረታው ጊዜ ትዝ ይለኛል፡፡ ቦሌ በሚገኘው ደሳለኝ ሆቴል እኛንም ወስዶን ነበር፤ ጥሩ ጊዜ አሳለፍን፡፡ ብዙ ሃሳቦች ተነሱ፤ ቢሮ ለጊዜው ቤት ውስጥ ነው ሚሆነው ተባለ፡፡ ሥራ ተጀመረ፡፡ ሃሳቡ በጣም ጥሩ ስለሆነና አባታችን ስለሆነ ሚያስበውን ነገር እንዲሳካለት እንፈልጋለን እና ዮኒም አይ.ቲ ላይ ብዙ ነገሮችን ስለሚያውቅ ቤት ውስጥ አንድ ዴስክቶፕ ነበረች፣ ፕሪንተር፣ አንድ መቀመጫ፣ አንድ ጠረጴዛ ተደርጎ በጣም በትንሽ ቦታ ከምግብ ጠረጴዛ አጠገብ ተመሰረተ፡፡ ማሚም የጽህፈት ነገሮችን እኔና ዮኒም እናግዘው ነበረ፡፡ አባላትን በመመዝገብ፣ ቲሸርቶችን በመሸጥ እንሳተፍ ነበር፡፡ ብሮሸር አይነት መረጃ ሰጪ ወረቀቶች ይታተማሉ፤ እነሱን ታትመው ሲመጡ እኔና ዮናስ ያን እያጠፍን እናግዛለን:: ብሮሸሩ ወረቀቱ ሻርፕ ስለሆነ ስናጥፈው እጃችን ይቆራረጥ ነበር፡፡ ገንዘብም እንሰበስባለን፡፡

**ከጓደኞቻችን ጀምሮ ግንዛቤው እንዲስፋፋ አባታችን የሚነግረንን መረጃዎች በማስፋፋት ሃሳቡን እንዲደግፉት በማድረግ እናቴም ከእድር ጀምሮ በቤተክርስቲያን በምታገኛቸው ማህበራት ሁላችንም ሃሳቡ እየሰፋ እንዲሄድ በማድረግ ወደ ተለያዩ ቢሮዎች በመላክ  ወንድዬ ያስፈልጉታል በሚባሉ አገልግሎቶች ሁሉ  ለረጅም ጊዜ እናግዘው ነበር።**

**አሁንስ እገዛችሁ ምን ይመስላል?**

አሁንም አጠገቡ አለሁ። ግን ልጆች ከወለድኩ በኋላ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስሄድ ከውስጤ የማይወጣ ትዝታ ይሰማኛል፡፡  የተጎዳ ልጅ ሳይ በልጆቼ ነው ማስበው እና እዛ ከሄድኩ በኋላ በቃ ውስጤ ጥሩ መንፈስ አይሰማኝም። በጣም ጭንቀት ነው ሚሰማኝ እና በተለይ ትንሹን ልጄን ከወለድኩ በኋላ መሄድ አቃተኝ፡፡  ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስሄድ እናትም ከሆንኩ በኋላ በጣም ስሜቱ ገባኝ መሰለኝ አልቻልኩም። የሰው ልጅ እዛ ጋር ታሞ ሳይ በጣም  ውስጤ ህመም ነው እየተፈጠረብኝ ያለው እና  ሳልፈልግ  መሸሽ ጀመርኩ ፡፡  አይቼ ከተመለስኩ በኋላ በዓሉም በዓል አይመስለኝም  ያንን ልጅ በአእምሮዬ ስስል  ህመሙ ሲያሳዝነኝ  እንደ ማቲ ሊሆንባቸው ነው በሚል  ውስጤ በጣም ከባድ ቁስል ይፈጠራል፡፡ ጥቁር አንበሳ መሄድ ፈራሁ እንጂ በማንኛውም ነገር አሁንም አባታችን የሚሰራውን ስራ ስለምንወድ አግዘዋለሁ ፡፡

**አቶ ወንዱ በጣም ጠንካራ ሰው ናቸው፤ ፋውንዴሽኑን ለማቋቋምና ህሙማንን ለመርዳት ያደረጉትን  ትግል እንዴት ትገልጪዋለሽ?**

**ወንድዬ በጣም ጠንካራ ነው። አንድን ነገር  ካሰበ በቃ የሚያደርግ አይነት ሰው ነው።  መፍትሄ እስካላመጣ ድረስ የሚያርፍ አይነት ሰው አይደለም ። ህመምን ዜሮ ማድረግ ባይቻልም ሰው ግንዛቤ ኖሮት ህመምን መከላከል መቻል ትልቅ ነገር ነው። እኛ ያለፍንበትን  መንገድ ድጋሚ ሌላ ሰው  እንዳያልፍበት ማድረግ ነው የሚፈልገው። ያንን ለማድረግ  ከባድ ትግል ያስፈልገዋል።   ችግሩ በጣም ሰፊ ስለሆነ የግድም መጠንከር አለበት።**

ቢያጫውተን እንኳን ወንድዬ በጣም አጭር ሰዓት ነው የሚያጫውተን፡፡  አሁን ከልጅ ልጆቹ ጋር ሲጫወት  እሱ በጣም ረጅም ሰዓት መሮጥና መጫወት ይፈልጋሉ ፡፡

ወንድዬ ያንን ፍቅር አይነሳም ጥሩ አያት ነው፤ ሁሉ ስስቱ ወደ ስራው ስለሆነ ረጅም ሰዓት ለቤተሰብ  አይሰጥም ግን ሁላችንም ስለምንረዳው ቅር አይለንም። በጣም ቁም ነገረኛ ስለሆነ  ስራ ተኮር  እንጂ ቁጭ ብሎ ረጅም ሰዓት የሚያጫውት አይነት ሰው አይደለም ይህ ባህሪው ነው ፡፡

**ላንቺ ደግሞ የተለየ ፍቅር አላቸው ይባላል ። እንደውም የቁጥጥሩ ማዕቀብ የተነሳልሽ የሰርግሽ እለት ነው ይባላል እውነት ነው?**

ሴት ልጅም እንደመሆኔ  አባትና ሴት ልጅ የተለየ ጠንከር ያለ ግንኙነት አላቸው። እውነት ነው በጣም ልዩ ፍቅር ሰጥቶ ነው ያሳደገኝ፡፡ ጠንካራ እንድሆን እንድበረታ አድርጎ ነው ያሳደገኝ ፡፡ የነበረው ጥብቅ ቁጥጥር  ለእኔ ጠቀመኝ እንጂ አልጎዳኝም። ረጅም ጊዜ ድረስ ሶስት ሰአትን በጣም አይረሳትም፤ ሶስት ሰአት ድረስ እንድገባ በጣም ነበር ያስገድደኝ የነበረው ልክ ያቺ ሰአት ስታልፍ በጣም ነበር የምጨነቀው፡፡  ላገባ  ሽማግሌ እንኳን ተልኮልኝ ከቤት እስክወጣ ድረስ ያችን ሰአት በጣም ነበር ማከብራት ፡፡  በጣም እቀርበዋለሁ፤ አከብረዋለሁ፤ በጣምም
እፈራዋለሁ ፡፡ ጥሩ ትምህርት ቤት አስተምሮኝ ሁሉን ነገር አድርጎልኝ በመልካም ሁኔታ አሳድጎኛል፡፡

ማቲን ካጣ በኋላ ስራውን ልክ እንደ ማቲ ነው የሚያየው ፡፡ ፋውንዴሽኑ እንግዲህ አስቢው ከዛ ተነስቶ እዚህ ሲደርስ ይሄን ሁሉ ሰው እየረዳ ብዙ የፖሊሲ ለውጦች እንዲመጡ አግዞ ፤ ከአዲስ አበባም አልፎ ብዙ ክልሎች ላይ እየሰራ ከካንሰር አልፎ  ተላላፊ ወዳልሆኑ ህመሞች እየገባ፤ ለሰው ግንዛቤ እየሰጠ እዚህ መድረሱ ለኔ በጣም በጣም ትልቅ ስኬት  ነው፡፡ እግዚአብሔርም ረድቶታል ብዬ ነው የማስበው። አንዳንዴ ራሱ ሲደክመው ወይም ሲያመው  " አይ እኔ አልሞትም"  ነው የሚለው ለምን ብዙ ያልጨረስኳቸው ነገሮች ስላሉ እግዚአብሔር ያንን ሳያሳየኝ አይገድለኝም ይላል፡፡  በጣም ይገርመኛል ፡፡

ኮስታራ የስራ ሰው ነው፡፡ ሲጫወት  ሲያስቅ አንዳንዴ የሚናገረው ቀልድ፣ አንድ ነገር ከያዘ  የማይለቀው ነገር፣ ደስ ይላል፡፡ የልጅ ልጆቹንም ይከታተላቸዋል፡፡ ጽፈን የምናስቀምጠው አይነት ነገር ውስጡ ብዙ መረጃዎች ብዙ እውቀቶች አሉት ፡፡ መልካም አባት ነው መልካም ባለቤት ሲያወራ የምትጠግቢው አይነት ሰው አይደለም፡፡ አባቴም ስለሆነ ሳይሆን  እውነት ነው፡፡  በእንደዚህ አይነት ነገር  የታደለ ሰው ነው፡፡

**የበጎ ሰው ሽልማት ላይ ደምቀሽ ሽልማቱን ተቀብለሻል፤ ይህ አንዱ ሆኖ የአባትሽን የቤተሰብሽን ድካም በተመለከተ በጣም የተደሰትሽበት ጊዜ የትኛው ነው ?**

**የበጎ ሰው ሽልማት በጣም ነው ውስጤን የሚሰማኝ። ራሱ ቃሉ በጎ ሰው በጣም ከባድ ቃል ነው። ያ ሰው መልካምነቱ ውስጥ ብዙ ትርጓሜዎች አሉት። ወንድዬ እውነት በጎ ሰው ነው፤ ከቤተሰቡ አጉድሎ የሚሰጥ ፤ ብዙ ቤተሰብ አሳድጓል ብዙ ሰው ረድቷል፤ ሁሌ እሱን የሚጠብቁ አቅመ ደካሞች አሉ። ድሮ ትምህርት ቤት ሲያደርሰኝ አምባሳደር አካባቢ ቁጭ ብለው የሚጠብቁት እናቶች ነበሩ። በጣም መስጠት የሚወድ ሰው ነው። ቤት ሞልቶ ሳይሆን ከቤት አጉድሎ የሚሰጥ አይነት ሰው ነው። ኮስታራ ሊመስል ይችላል ፤ አጨዋወት ላያውቅበት ይችላል ፤ ግን ወንድዬ አንድ የሚችልበት ነገር ቢኖር መስጠት ነውና ለዚህ ትልቅ ሽልማት ሲታደል በጣም ነው ደስ ያለኝ ። በጣም ለፍቷልና ድካሙ ተቆጥሮለት እዛ ጋር ሄጄ እኔ ቁጭ ስል በጣም ነበር የከበደኝ ። በአጋጣሚ ስላልነበረ ነው እንጂ በጣም ሊያስደስተው ከሚችል ቀን በላይ ይሆን ነበር ። በጣም ሲደሰት ወንድዬ ካየሁት ቀን የሰርጌ ቀን ነበር እና ከዛ ቀን በላይ ይደስታል ብዬ ነው የማስበው።**

በቃ በጣም ደንግጬ ነበር። የተቀመጥኩት ከትልልቅ ሰዎች ጋር ነበር። በቃ ወንዱ በበጎ ሰው ላይ ታጨ ሲባል በጣም ነበር ደስ ያለኝ። ከነበሩት ተፎካካሪዎች አንጻርም ያሸንፋል ብዬ ስላልጠበኩኝ በደንብም አልተዘጋጀሁም። ልክ ደግሞ ስሙ ተጠርቶ አሸናፊ እንደሆነ ስሰማ የተሰማኝ ስሜት የተለየ ነበር። መቆም ሁሉ ነው የከበደኝ። ትልቅ መድረክ ነበረና ቆጨኝ። ወንድዬ እዛ ጋር ኖሮ ደስታውን ቢያጣጥመው የእውነቱን በጎ ሰው መሆኑን ቢያውቅ እዛ ጋር እሱ ሊያቀርበው የሚችለውን ንግግር ሳስበው በጣም ነው ደስ የሚለኝ የሚቆጨኝም ፤ ብዙ መናገር የምፈልጋቸው ነገሮች ነበሩ። ግን ከነበረኝም ልምድ ማነስ የተነሳ ማለት የምፈልጋቸውን ብዙ ነገሮች አላልኩም። ግን በጣም በጣም ደስ ያለኝ ቀን ነበር።

**የማቲ መምጣት የቤተሰባችሁን ህይወት ወደ ሌላ አቅጣጫ የለወጠው አይመስልሽም?**

በጣም ቀይሮታል። አንዳንዴ ማሚ የምትለው ነገር አለ። ማቲ መስዋት ሆኗል አንዳንዴ የተሻለ ነገር እንድታዪ እግዚአብሔር በሆነ መንገድ ያሳልፍሻል።

ማቲዬን ማጣታችን የሁሌ ቁጭታችን የሁሌ ሀዘናችን ቢሆንም በዛ ስር ግን በጣም ትልቅ ነገርን ፈጥሮ ነው ያለፈው። ማሚዬ ማቲዬን ብናጣም ሁሌ ሺህ ማቲዎች አሉ ትላለች። እንደ ልጅ ያው ከባድ ነው ግን ለሀገር መፍትሔ ይዞ የመጣ ስለሆነ በቃ አሜን ብለን ሁላችንም ተቀብለነዋል። ሁሌም ማቲን አንረሳውም። ልደቱንም ህልፈቱንም እሁድ እሁድ ያረፈበት ፉካ ተገኝተን ሻማ ማብራታችንም ሁሌም ያለ ነገር ነው እና ማቲ ሁሌ ከልባችን አይጠፋም ግን ሌላ ማቲዎች ደግሞ እንዲድኑ እና እንድናይ ህይወታችንን በደንብ በደንብ ቀይሮት ነው ያለፈው።

**ፋውንዴሽኑ ከካንሰርም አልፎ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ ነው እየሰራ ያለውና እዚህ ላይ መድረሱ ምን ያስረዳሻል?**

እነዚህ ህመሞች ሰውን ከካንሰር ባልተናነሰ እየጎዱ ነው። መስራት ያስፈልጋል። መረጃ ሰጪ ካልተገኘ በስተቀር አይታወቅም። ህመሙ ራሳችን ላይ እስኪመጣ ወይም የምንወደው ሰው ላይ እስኪመጣ አይታየንም። ከእግዚአብሔር በመቀጠል በመከላከል፣ ከአጋላጭ ነገሮች በመራቅ ጤናችንን መጠበቅ እንዴት እንደምንችል ከአመጋገብ ጀምሮ ብዙ ነገሮች አሉና እዚህ ነገር ላይ መስራቱ ያስደስተኛል። ብዙ ነገሮችን በመረጃ ማቅለል እንችላለን እና ይሄንን ነገር እያስፋፋ መምጣቱ አንድም ግንዛቤው ራሱ በጣም ትልቅ ነገር ነው። እኛ ቤተሰባችንን በዛ መልኩ ጎድቶብን ስለነበረ ማደጉ መስፋቱ ጥንካሬውን ያሳየኛል። ሁሉም ነገሮች ደግሞ ተሳክቶለት ማየት እፈልጋለው። አሁን ላይ እያቆምነው ያለነው ነገር ልክ እንደ ምሰሶ መስሎ ይታየኛል።

**በመጨረሻ ለፋውንዴሽኑ ምን ትመኛለሽ?**

አባቴ ህልሙ የሆነውን በጤናማ አፍሪካ ትልቅ ማዕከል ተገንብቶ እንደሚለው ያለው በገንዘቡ የሌለው ደግሞ በነፃ ታክሞ ሀገራችን ላይ ያ ማዕከል በምርምር ትልልቅ ነገሮች የሚገኙበት ራሱን የሚያስተዳድር ተቋም እንዲሆንና የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የሚል ማዕከል ወንድዬም እኛም ካለፍን በኋላ ቆሞ ለሰዎች ተስፋ የሚሆን ለአገርና ለወገን አለኝታ እንዲኖረን በጣም ትልቅ ምኞቴ ነው አመሰግናለሁ።



# የበጎ ሰው ሽልማት ድርጅት የቦርድ አባል

ደራሲና ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ

የበጎ ሰው ሽልማት ድርጅት ከተቋቋመ ጀምሮ በተባባሪ አዘጋጅነት በብዙ መልኩ እያገለገልኩ እገኛለሁ። የበጎ ሰው ሽልማት ድርጅት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ነው። ዘርፎቹም እየበዙ ነው። በተለያዩ ዘርፎች ነው ሽልማት የምንሰጠው ። በዋናነት ግን ለበጎ ሰው ሽልማት ሰዎች የሚበቁት በሙያቸው ስለሰሩ ብቻ ሳይሆን በጎነትን ሲያከናውኑ ነው። ከራሳቸውና ከቤተሰባቸው አልፈው ሙያቸውን ለምን የበጎ ሥራ አዋሉት የሚለው በስፋት ይታያል። ይሄ ነው ለበጎ ሰው ሽልማት የሚያበቃቸው። በጎ ሰዎችን እየሸለሙ ሌሎች በጎ ሰዎችን የማፍራት መርሐግብር ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ ዘርፉ እያደገ እየጠነከረ በሰዎች ዘንድም ይበልጥ እየታወቀና እየተወደደ መጥቷል።

የ2016 ዓ.ም የበጎ ሰው ሽልማት ከሌላው ጊዜ የሚለይባቸው አንዳንድ ነጥቦች አሉ። ለማህበረሰቡ ፣ለሀገር፣ በዓለማቀፍ ደረጃ ብዙ አስተዋጽኦ በማበርከቱ ታዋቂና የብዙ ሽልማቶች ባለቤት የሆነው ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በኢትዮጵያ ደግሞ በበጎ ሰው ሽልማት ላይ ዕውቅናና ሽልማት ያገኘበት መርሐ ግብር መሆኑ ለየት ያደርገዋል። ማቲዎስ ወንዱን አውቀዋለሁ የአቶ ወንዱ ወንድም ዶ/ር ያዕቆብ በቀለ ቤት ከአቶ ወንዱ ጋር ተዋወቅን። ለጥቂት ደቂቃዎች ከተጨዋወትን በኋላ መፅሔቶች ሰጡኝ ቢሮዬ ገብቼ ሳነበው በጣም ደነገጥኩኝ፤ ስሜቴ በእጅጉ ተላወሰ ። ያንን በጣም አንጀት የሚበላ እምቦቃቅላ ማቲዎስን ታሪክ ሳነብ በእጅጉ ልቤ ተነካና ጨርሶ ማንበብ አቃተኝ። ከዚያ ደግሞ የወላጆቹ ጥንካሬ አስደነቀኝ። ይህንን ድርጅት መስርተው ለሌሎች ህፃናት ፣ለሌሎች ኢትዮጵያውያን፣ ለሰው ዘር በሙሉ የካንሰር ህክምና የሚያገኙበትን ከካንሰር እንዲፈወሱ  የሚታገዙበትን መንገድ የከፈቱበት እጅግ ከፍ ያለ ሀዘናቸውን በውስጣቸው ይዘው አሁንም ድረስ ፊቴ ላይ የሚመጣ ስለሱ ለማውራት የሚከብደኝን የዚያን ተወዳጅ ልጅ  ታሪክ እዚያ ውስጥ በማንበቤ ነው ስለ ድርጅቱ ያወኩት ።

ከዚያ በኋላ ይህንን ድርጅት እንዴት ነው የምረዳው፤ ምንድነው የማግዛቸው የሚል ነገር እያሰብኩ ላገኘሁት ሰው ሁሉ እነግራለሁ። እንዴት እንደሆነ በማላውቀው ሁኔታ የማቲዎስ ነገር ይገርመኛል። እያደጉ የመጡ ዛሬ ወጣት የሆኑ ጓደኞቹን ሳይ የወላጆቹን ጥንካሬ በእጅጉ ነው የማደንቀው።

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በጥቆማ ወደ በጎ ሰው ሽልማት ድርጅት ቦርድ የደረሰበት የራሱ ሂደት ነበረው። በአሰራራችን መሰረት ከህዝቡ ጥቆማ መጥቷል። ያንን መሰረት አድርገን የሁሉንም ታሪክና ማንነታቸውን እንፈትሻለን። ከበርካቶች ውስጥ ከአምስቱ አንዱ ሆኖ አለፈ። አምስቱም ለቦርዱ ቀርበው ታሪኩ  በሚነበብበት ሰዓት ልባችን ውስጥ ጠልቆ የገባ ነበር። መተያየት እስከማንችል ድረስ በሀዘኔታ በተመስጦ ነበር ያደመጥነው። ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ለውድድር ከሌሎች ጋር የሚቀመጥ አልነበረም። ከአምስቱ ሁለቱን መምረጥ ስለነበረብን ለመምረጥ ብዙ አልተቸገርንም። ነገር ግን ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ከአንደኝነትም በላይ ድምጽ ያገኘ ነው። ከውድድር በላይ በሆነው በሰውኛ ስሜት በያዙት ትልቅ ዓላማ፣ በስሙ ለሰሩለት እንዲህ አይነት በጎ ተግባር ማቲዎስ እየታየን ነው ለማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ትልቁን ሽልማት ያበረከትንለት። እስከዛሬ ካወዳደርናቸው በከፍታ ውስጥ ካሉት መካከል ነው።




ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በመሸለሙ በግሌ የተሰማኝ ስሜት ዕዳ አለብኝ ብዬ ስለማስብ ብዙ ሥራ መስራት አለብኝ ብዬ ስለማስብ አንዲት ጡብ ያዋጣሁ ያህል ነው የተሰማኝ፤ ደስ የሚል ስሜት። ምክንያቱም ጊዜ ከማጣት የሥራ ፀባዬ ሙሉ ጊዜዬን ስለሚፈልግ እንደምፈልገው መስራት ባለመቻሌ ከጓደኞቼ ጋር ሁሉም የኔንን ዓይነት ስሜት ተሰምቷቸው ሙሉ ድምፅ ሲሰጡ ሳይ በጣም ተደሰትኩ። በእንባ የታጀበ ነበር። በህይወቴ ለሽልማት መጥተው ድምፅ ከሰጠሁባችው የሚያስደስተኝ ከፊት የማስቀምጠው ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ነው። እስካሁንም ድረስ ያ እርካታ ይሰማኛል። ድርጅቱ ዓለማቀፍ ዕውቅና ስላለው ከዚያም በላይ ብዙ መስራት አለበት።እኔም ባለኝ አቅም ሁሉ ይህንን ድርጅት አብሬው ለመሆን ይበልጥ ቤተሰብ የሆንኩበት ነው።

**የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን መሸለም ለሌሎች ድርጅቶችም ትምህርት ይሰጣል ብዬ አስባለሁ። እንዲተዋወቅ ማድረግ ያስፈልጋል። ብዙ ኢትዮጵያውያን አውቀውታል። በመገናኛ ብዙሀን በቀጥታ ይተላለፍ ስለነበር ታሪኩ ሲነበብ ሽልማቱን የተቀበለችው ልጃቸው ንግግር ስታደርግ ያልተነካ የለም። ብዙ ሰው እንዲያውቀው አድርጎታል። መታወቁ ከዚህ በኋላ አብሮ ለመስራት ብዙ ችግር እንዳያጋጥም ያደርጋል። ኢትዮጵያ ብዙ እንዲህ ዓይነት ተቋማት ያስፈልጓታል። የገንዘብ አቅም ያላቸው ተቋማት ገንዘባቸውን ለዚህ መሰል በጎ ዓላማ እንዲያውሉ ከማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ጋር አብረው እንዲሰሩ ሌሎችንም ተቋማት እንዲመሰርቱ ማድረግ ይቻላል። የሰው ልጅ ምድር ላይ ለአጭር ጊዜ ነው የሚኖረው። ለትውልድ የሚተርፍ ነገር ሰርተን እንደማለፍ ጥሩ ነገር የለምና ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በመመስረቱ ለሀገር ነው የጠቀመው። ማቲዎስ አለ፤ ከዚህ በላይ መኖርና ማደግ የለም። በሱ እልፈት ሌሎች እየዳኑ ህያው ሆኗል። በዚህም በመሸለሙ በጣም ደስ ይለኛል።**

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የሰራውን ያህል ታውቋል የሚል እምነት የለኝም። ሥራው ምድራዊ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊና መንፈሳዊ ነው። በማቲዎስ ስም ቤተሰቦቹ እየከፈሉት ያለው ዋጋ ልጃቸውን ቢያጡም ሌሎችን ለማዳን የሄዱበት ርቀት የሚገባውን ያህል ዕውቅና አላገኘም። የራሳችንም ተቋም እንደመሆኑ ሁላችንም የህዝብ የምናደርግበት በመረዎችም መደረክ ይሄ ፋውንዴሽን እንዲመሰገን ፣ እንዲሸለም ፣ የህዝብ እንደመሆኑ መንግስትና የጤና ተቋማት ድጋፍ እንዲያደርጉለት መደረግ አለበት። ቤተሰቦቹ ናቸው እስካሁን ተሸክመው ያመጡት፣ ያንን መስቀል ሁሉም መሸከም አለበት። የበጎ ሰው ሽልማት ፋይዳው ዓላማው በጎዎችን መሸለምና ዕውቅና መስጠት ሌሎች በጎዎችን ማፍራት ነው። እንደ ማቲዎስ ወንዱ በበጎ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሲሸለሙ እንኳን ማህበረሰቡ እኛ የቦርድ አባላቱም አብረን ለመስራት በጎ ፈቃደኞች የሆንንበት አጋጣሚ ነው የተፈጠረው። ይህንን በመገናኛ ብዙህን የተመለከቱ ሁሉ ራሳቸውን ምን በጎ ነገር አበረከትኩ ብለው እንዲፈትሹ ከዚያም ፋውንዴሽኑን እንዲደግፉ ያደርጋል። በሽልማቱ ከሌሎች የተቀበልኩት አስተያየት 12 ዓመት ሙሉ የት ነበራችሁ ይህንን የመሰለ ተቋም ሳትሸልሙና ዕውቅና ሳትሰጡ የሚል ወቀሳ ነው ። በአሰራሩ መሰረት ከህዝብ በመጣ ጥቆማ ነው ውድድር የምናካሂደው። እስከዛሬ ጥቆማው ስላልመጣ ነው ያልተሸለመው ። የ2016ቱን ሽልማት የሚያስታውሱ ማቲዎስ ወንዱን ያስታውሳሉ። ትልቅ ተቀባይነትም አግኝቷል።

የካንሰር ህመም በሀገራችን የብዙ ሰዎችን ህይወት እየቀጠፈ ነው። በህጻናት ደረሰ ሲባል የማቲዎስን ታሪክ ነው የሰማሁት፤ ከዚያ በኋላ ግን ብዙ እንዳውቅ አድርጎኛል። የታመሙ ሰዎችን ሳይ እጨነቃለሁ፤ ከካንሰር የዳኑ ሰዎችን ስመለከት ደስ ይለኛል። ስለካንሰር በሬዲዮ ብዙ ፕሮግራም እንዲሰራ አድርጌያለሁ። ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን አሁን ደግሞ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ እየሰራ ይገኛል ።እነዚህ ህመሞች አሳሳቢ ሆነዋል። ይህ የፋውንዴሽኑ ሌላው በጎ ተግባር ነው። በሀገራችን የጤና ኢንሹራንስ ባለመስፋፋቱ እነዚህ ህመሞች ብዙ ሰዎችን እየጎዱ ነው። ከአኗኗር ዘይቤ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው አመጋገባችን ላይ ጥንቃቄ ቢደረግና ትምህርት ቢሰጥ ጥሩ ነው። የግንዛቤ መስጫ መድረኮች በስፋት መኖር አለባቸው።

በሬዲዮ በቴሌቪዥን በቋሚነት መርሐ ግብሮች ቢዘጋጁ፣ በየተቋማቱ የጤና ምርመራ መርሐግብር ቢኖር፣ ጤናችንን እንወቅ የሚል ንቅናቄ ቢዘጋጅ፣ ማህበረሰቡን ማስተማር ይቻላል። የማቲዎስ እኩዮች ዶክተሮች ሆነዋል፤ አድገዋል። እነሱን በጎ ፈቃደኛ አድርጎ በማንቀሳቀስ መስራት ይቻላል። 22ኛ ዓመቱን እያከበረ ላለው ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን እስከዛሬ ለሰራችሁት መልካም ተግባር እግዚአብሔር ብድራችሁን ይመልስላችሁ። ልጆቻችሁን የማቲዎስ ወንድም፣ እህት፣ ጓደኞች ፣አብረዋችሁ የሚሰሩትን ሁሉ የወላጆቹንም ጤና ይጠብቅልን። ከዚህ በኋላ ያለው ጉዞ የሁላችንም ነው። እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።



# ከመስራቾች አንደበት

## አቶ ወንዱ ህንድ አገር የሄዱት ለምን ይሆን?

**ጥያቄ እ.ኤ.አ ከማርች** 2025 **ጀምሮ ወደ ህንድ ሀገር ሄደው ለሶስት ወራት ቆይተው ነው በቅርቡ የተመለሱት የሄዱት ለምን ጉዳይ ነው**?

**መልስ** እንደወትሮው በየጊዜው የጤና ምርመራ ሳካሂድ ጉበቴ አካባቢ ያልተጠበቀ ህመም እንዳለ በመጠርጠሩና ጥርጣሬውን ለማቃለል ከሚረዱት መሳሪያዎች አንዱ ፔት ስካን/PET- SCAN/ እዚህ ኢትዮጵያ ስለሌለ ለዚህ ምርመራ ነው ወደ ህንድ ከባለቤቴ ወ/ሮ አምሳለ በየነ ጋር የሄድነው፡፡

**ጥያቄ ህመሙ ምን ዓይነት ነው**?
**መንስኤውስ** ? **ታክሞ የመዳን ዕድሉስ**?

**መልስ** ህመሙ የካንሰር ዓይነት ሲሆን በተለይ ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ የሚከሰትና በጊዜው ታውቆ ተገቢው ህክምና ከተሰጠ የመዳን ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

**ጥያቄ ህክምናው ምን ዓይነት ነው**? **ውድ ነው?**
**በሀገር ውስጥ ይሰጣል?**

**መልስ** ለህመሙ ሁለት ዓይነት የህክምና አማራጮች አሉ፡፡ እነሱም ጂሚውኖ ቴራፒና ኬሞቴራፒ ናቸው፡፡ ህክምናው ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው ሁለቱ አንድ ላይ ሲሰጡ ነው፡፡ ነገር ግን የጂሚውኖ ቴራፒው ህክምና በጣም ውድ ነው፡፡ እንደ የአገሩ ቢለያይም በአሜሪካና በአውሮፓ እስከ 500 ሺህ ዶላር ያስወጣል ይባላል፡፡ በህንድም ቢሆን ለአንድ ሳይክል 5 ሺህ ዶላር ወይም 670 ሺህ ብር ያስከፍላሉ፡፡ ይህ እንግዲህ ለምርመራና በተዛማጅነት የሚወጣውን ወጪ ሳይጨምር ነው፡፡

**ጥያቄ እርስዎ ምን ያህል ዙር ወይም ሳይክል ነው የወሰዱት?**

**መልስ** እኔ በሀኪሞች የታዘዘልኝን 7 ዙር ወይም ሳይክል ሲሆን ሶስቱን ህንድ አገር ከወሰድኩኝ በኋላ የተቀረውን 4 እዚሁ ሃሌሉያ ሆስፒታል ነው የወሰድኩት፡፡ ለዚሁም እንዲረዳኝ ለሶስት ዙር የሚያስፈልጉ መድሃኒቶችን በ15 ሺህ ዶላር ወይም በ2ሚሊዮን አስር ሺህ ብር ገዝተን ከህንድ አገር አምጥተን ነው ህክምናውን የወሰድኩት ፡፡ ምንም እንኳን ህንድ አገር ያለው ራጂግሪ ሆስፒታልና እዚህ የሚገኘው ሃሌሉያ ሆስፒታል በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቢሆንም በመድሃኒት አሰጣጥ ላይ ብዙም ልዩነት አላየሁባቸውም፡፡ ለዚህም ለሀኪሜ ዶ/ር ዮናስ ደንዳና ፣ ለዶ/ር ዝናሽና ለሲስተር ሆሳዕና፣ ለወ/ሮ ትርሲት የስነ-ምግብ ባለሙያ፣ በመጨረሻም ለውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ አምሳለ በየነ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡


**ጥያቄ ህመሙ ካንሰር መሆኑን ሲሰሙ ምን ተሰማዎት?**

**መልስ** እውነቱን ለመናገር መጀመሪያ ላይ ለመቀበል ተቸግሬ ነበር፡፡ "ምነው ፈጣሪ አምላክ እኔ ላይ አልበዛም?" እስከማለት ደርሼ ነበር ፡፡ በኋላ ላይ ግን እግዚአብሔር ፍፁም እንደሆነና እንደማይሳሳት ስለማውቅ ለበጎ ነው ብዬ ተቀበልኩት፤ ወዲያውም መረጋጋት ጀመርኩ ፡፡ ከሁሉ በላይ የከበደኝ የያዘኝን ህመም ለቤተሰብና ለስራ ባልደረቦቼ መግለፅና ማስረዳት ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን ምንም ነገር ሳላስቀር ማስረዳት ጀመርኩ፡፡



**ጥያቄ ህመምዎን ለቤተሰብና ለሥራ ባልደረቦችዎ በመግለፅ በኩል አልተቸገሩም?**

**መልስ** ብዙም አልተቸገርኩም፤ እንደውም ያለሁበትን ሁኔታ፣ እየወሰድኩ ያለውን ህክምና ውጤቱን በተመለከተ አጫጭር ቪዲዮ እየቀረፅኩ እልክላቸው ስለነበር ከሁሉም በላይ በቪዲዮ ያለሁበትን ሁኔታ ሲያዩ በጣም ይበረታቱ ነበር፡፡ እንዳውም የቪዲዮ መልዕክቱ ሲዘገይ መጠየቅ ጀምረው ነበር፡፡



**ጥያቄ ለፋውንዴሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ ፣ ለአጋር ድርጅቶችስ ያሳውቁ ነበር?**

**መልስ** አዎ በእያንዳንዱ ዙር ያለሁበትን ሁኔታና እየወሰድኩ ያለሁትን ህክምና ስወስድ በፎቶግራፍ አስደግፌ ውጤቱን ጭምር ለሥራ አመራር ቦርድ፣ ለሠራተኞች፣ ለአጋር ድርጅቶችና እርዳታ ለሚያደርጉልን ሁሉ ስለምልክ መልዕክቱን በደስታ በመቀበል እንዲያውም በመካከሉ ሲዘገይ መጠየቅ ጀምረዋል፡፡

**ጥያቄ ህክምናውን እንዴት አገኙት?**

**መልስ** ህክምናው እልፎ እልፎ ስለሚሰጥ ብዙም አይከብድም፡፡ አንዳንዴ በሳምንት ሌላ ጊዜ በየ15 ቀኑ ይሰጣል፡፡ በየ15 ቀኑ የሚሰጠው በአንድ ጊዜ ከ3 ሰዓት በላይ በተከታታይ ስለሚሰጥ ይከብዳል፡፡

**ጥያቄ ህክምናው የሚያስከትለውን ተፅዕኖ እንዴት ተቋቋሙት?**

**መልስ** ከሀኪሞች የሚነግሩኝ በጣም የተለየ ነው፡፡ የማስመለስ፣ የማስቀመጥ፣ ምግብ አልበላ የማለት፣ ክብደት የመቀነስ...ወዘተ ይኖራል ብለው ነው የነገሩኝ፡፡ እኔ ግን አንዱም አላጋጠመኝም፡፡ እንደውም ብዙ የመብላት ፍላጎት ስላለኝ የክብደቴ መጠን እየጨመረ በመምጣቱ በዚህም ምክንያት ለተለያዩ ለስኳር፣ ለልብ፣ ለደም ግፊት... ወዘተ ህመም እንዳልጋለጥ እየተጠነቀቅሁ ነው፡፡ ይህም በሀኪሞቼ ዘንድ አግራሞትን ፈጥሯል፡፡



**ጥያቄ ህክምናውን ለማገዝ በእርስዎ በኩል ምን አይነት ጥረት ያደርጋሉ?**

**መልስ** እኔ ሀኪሞች የሚሉኝንና የሚሰጡትን አስተያየትና ምክር በሚገባ አከብራለሁ።



ሆኖም ግን ተስፋዬ በእግዚአብሔር ላይ ነው። በዚህም ከሁሉም አማራጮች በላይ እግዚአብሔርን ተስፋ አደርጋለሁ፣ አመሰግናለሁ ፣ ጥያቄ አቀርባለሁ በዚህም

1. በፈጣሪ ላይ ሙሉ እምነት ጥዬ አበክሬ እፀልያለሁ እንዲረዳኝ እጠይቃለሁ።
2. በሀኪሞች በተሰጠኝ መመሪያና አስተያየት መሰረት ተገቢውን መጠጥና ምግብ እመገባለው።
3. በቂ የአካል እንቅስቃሴ አደርጋለሁ፣ ኤሮቢክስ እሰራለሁ፣ የእግር ጉዞ አደርጋለሁ።
4. በቀን እስከ 3 ሊትር ውሃ ቢጠማኝም ባይጠማኝም እጠጣለሁ።
5. ከጭንቀት ለመራቅና ራሴን ለማዝናናት ጥረት አደርጋለሁ።
6. ከህመሙ ታክሜ እድናለሁ የሚል ፅኑ ተስፋ ይዤና ሰው በሚለው ሳልበረግግ ህክምናዬን በመከታተል ላይ ስለሆንኩ እስካሁን ባለው የህክምናዬ ውጤት ውጤታማ ሊሆን ችሏል።

**ጥያቄ ከህመሙ ጋር ባለው ሁኔታ ምን ተገንዝቤያለሁ ብለው ያምናሉ?**

**መልስ** እግዚአብሔር ይኼንን ህመም እንዲይዘኝ ያደረገው አንዳንዶቹ እንደሚያስቡት ለቀጣኝ አስቦ እንዳልሆነ በሚገባ እረዳለሁ። ይልቅ ሊያሳየኝ ወይም ሊያስተምረኝ የፈለገው ነገር እንዳለ አምናለሁ። በዚሁም የካንሰር ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው ከህመሙ ጋር የሚያደርጉትን ግብግብ በወሬ ሳይሆን በቀጥታ ለማወቅ አስችሎኛል። ችግሮቻቸውን በሚገባ እንዳጤን ረድቶኛል። ይኼም ህሙማንና ቤተሰቦቻቸውን በርትቼ እንዳገለግላቸው ረድቶኛል።

**ጥያቄ በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?**

**መልስ** የካንሰር ህመም በአገራችን በጣም ተጋኖና አንዳንዴም በተሳሳተ ሁኔታ ሲቀርብ እናያለን ። ይኼም የካንሰር ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው እንዲሸማቀቁና እንዲደበቁ እያደረገ ይገኛል። ካንሰር ቀላል ህመም አይደለም። እንደሚቀርበውም የሞት ፍርድ ዓይነት ህመምም አይደለም። 40 በመቶ የሚሆነውን የካንሰር አምጪ ምክንያቶች አስቀድሞ መከላከል ይቻላል፤ ህመሙ እንደያዘ በወቅቱ ከታወቀና በአግባቡ ከታከሙት የሚድን ህምም ነው። ዛሬ በአሜሪካ አገር 18.1 ሚሊዮን ሰዎች በካንሰር ህምም ተይዘው ታክመው ድነው መደበኛ ህይወታቸውን በመኖር ላይ ይገኛሉ። እናም ከሌላው ዓለም በመማር ለካንሰር ህሙማኑና ቤተሰቦቻቸው ተገቢውን ክብር፣ ትብብርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅብናል።

**ኢትዮጵያ በየዓመቱ 31 ቢሊዮን ብር ወይም የአገር ውስጥ ምርቷን 1.8% የሚሆነውን ካንሰርን ጨምሮ ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ምክንያት ታጣለች። ስለሆነም አስቀድመን መከላከል በምንችላቸው ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ወገናችን ከዚህ ዓለም ያለጊዜው መለየቱ እንዲያበቃ ፤ ውዷ አገራችንም ለኑሮና ለሥራ የተመቸች እንድትሆን እንድናደርግ በትህትና እጠይቃለሁ።**




# ወደ አሜሪካ የተደረገ የስራ ጉብኝት

መዳረሻዎች፡- ሳንዲዬጎ፣ ሎስ አንጀለስ፣ ኒው ዮርክ፣ ዋሽንግተን፣ ቺካጎ





የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን መስራችና ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ወንዱ በቀለ በብሪስትል ማየርስ ስክዊብ ፋውንዴሽን(BMSF) ግብዣ በካሊፎርኒያ ሳንዲያጎ የተካሄደው የዓለም የሳንባ ካንሰር ኮንፈረንስ ተሳትፈዋል፡፡ ሳንዲያጎ በካሊፎርኒያ የፓስፊክ ወንዝ ዳር ላይ የሚገኝ ከተማ ሲሆን በባህር ዳርቻዎች፣ በፓርኮችና በአየር ፀባይ ምቹነት ይታወቃል፡፡ ኮንፈረንሱ ከአለም የሳንባ ካንሰር ባለሙያዎች ጋር የተለያዩ ልምዶችን ለመጋራትና አዳዲስ ዕይታዎችን ለማግኘት ጠቃሚ ነበር፡፡

**ሎስ አንጀለስ፣ ካሊፎርኒያ** አቶ ወንዱ በሳንዲዬጎ ከአምስት ቀናት ቆይታ በኋላ ወደ ሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ አምርተዋል፡፡ ካሊፎርኒያ በአሜሪካ ውስጥ ትልቁ ግዛት ሲሆን አገር ቢሆን አምስተኛ ትልቅ ኢኮኖሚ ያለው አገር ይሆን ነበር፡፡

**ሺካጎ፣ ኢሊኖይስ** በአሜሪካ የአቶ ወንዱ ጉብኝት ሶስተኛ ትልቅ ከተማ ወደ ተሰኘችው ሺካጎ ነበር፡፡
ከተማዋ በአስደናቂ አርክቴክቸር የታወቀች እንዲሁም የአርት ኢንስቲትዩት ኦፍ ሺካጎና የዓለም ታዋቂ ሙዚየሞች ቤት ናት፡፡
ከተማዋ በጆን ባፕቲስ ፖይንት ዱ ሳብል የተመሰረተች ስትሆን በግምት 15,000 ኢትዮጵያውያን በሺካጎ ይኖራሉ፡፡

**ኒው ዮርክ** ኒው ዮርክ "የዓለም የኢኮኖሚ ዋና ከተማ ወይም ካፒታል" የምትባል ከተማ ነች፡፡ አቶ ወንዱ ከሎስአንጀለስ ወደ ኒውዮርክ ያደረጉት ረጅም በረራ የአሜሪካንን ትልቅነት ያሳያል፤ ለምሳሌ ከአዲስ አበባ እስከ አቴንስ፣ ግሪክ ወይም እስከ ሙምባይ፣ ህንድ የሚደርስ እኩል ነው ጉዞ ያደረጉት፡፡ ስለዚህ ብዙዎች "አሜሪካ አንድ ሀገር አይደለም፣ ኮንቲነንት ነው" ይላሉ፡፡


በዚሁ አጋጣሚ አቶ ወንዱና ወ/ሮ አምሳለ በተጋበዙባቸው ከተሞች የኢትዮጵያን ዲያስፖራ ህብረተሰብ ኮሚኒቲ ለማግኘትና ፋውንዴሽኑን የማስተዋወቅ ሥራ ሠርተዋል፡፡ አሜሪካ ከሚገኙ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በቅርብ ተገናኝተው ተወያይተዋል ፤ ከፋውንዴሽኑ ጋር አብረው ሊሠሩ ከሚችሉ አዳዲስ ድርጅቶች ማለትም JSI, PSI, NSH ወዘተ ጋር በቅርብ ተገናኝተው ተወያይተዋል፡፡ በዚህም የሚያበረታታ ውጤት ይዘው ተመልሰዋል፡፡ ሁለቱም የፋውንዴሽኑን 20ኛ አመት እንዲሁም የትዳራቸውን 40ኛ አመት አስመልክተው ጠቃሚ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ በዚህም ፋውንዴሽኑን ለማስተዋወቅ ምቹ ሁኔታ ፈጥረው በሰላም ተመልሰዋል፡፡



# የፋውንዴሽናችን አስተዋፅኦ

## ወ/ሮ ማህሌት ወርቁ

የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የሥራ አመራር ቦርድ አባልና
የኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ድርጅት ህብረት
ዋና ሥራ አስኪያጅ



## ከማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ጋር እንዴት ተገናኘሽ?

ከፋውንዴሽኑ ጋር የተገናኘሁት የዛሬ ስድስት ዓመት መገናኛ የሚገኘውን የካንሰር ህሙማን መርጃ ማዕከል ልጎበኝ በሄድኩብት ጊዜ ነው፡፡ በዚያን ወቅት እኔ ራሴ ከካንሰር ህመም አገግሜ እንደኔ በዚያ ህመም በችግር ውስጥ እያለፉ ያሉ ሴቶችን፣ ህፃናትና ሌሎችንም ለማበረታታትና አይዟችሁ ለማለት እንደ ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ያሉ በኢትዮጵያ የካንሰር ህሙማንን የሚረዱ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን እያፈላለግሁ በነበርኩበት ጊዜ ስለ ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ዌብሳይታቸውን በማየት ተረዳሁ፡፡ አድራሻቸውን አፈላልጌ በአካል በመሄድ በማዕከሉ የተጠለሉ ህፃናትና ተንከባካቢዎቻቸውን ጎበኘሁ፡፡ በማዕከሉ የሚገኙ ሰራተኞች እጅግ ቀና በሆነ መንገድ ነበር የተቀበሉኝ፡፡ ማዕከሉን ስጎበኝ ህሙማኑን ማበረታታት ካንሰር የሞት መንገድ ብቻ እንዳልሆነ እንዲገነዘቡ የራሴን አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚኖርብኝ ለራሴ ቃል ገባሁ፤ ከዚያም የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ቤተሰብ ሆንኩ፡፡

## ስለ ካንሰር ለመወያየት ህሙማኑን ለመጎብኘት ልብሽ እንዴት ፈቀደ ?

ካንሰር ላይ ትኩረት የኖረኝ ህሙማኑን ለመጎብኘትና ያለኝን ልምድ በማካፈል አዎንታዊ ተፅዕኖ ለመፍጠር የተነሳሳሁበት ዋነኛው ምክንያት እኔ ራሴ ያለፍኩበት መንገድ ነው፡፡ እንደኔ በህመሙ ውስጥ እያለፉ ያሉ ሰዎችን የስነልቦና ድጋፍ ለመስጠት ከፍተኛ ፍላጎት አደረብኝ፡፡ የካንሰር ህመም አካላዊ በቻ ሳይሆን የስነልቦና ቀውስና ተስፋ መቁረጥ የሚያስከትል፣ የአስተሳሰብ መዛባት የሚያመጣ ህመም ነው፡፡ እስከዛሬ ህመሙ የሚሳልበት መንገድ እጅግ በጣም አሰቃቂ ነው፡፡ እንደ ሀጢያት ወይም እንደ ቅጣት የሚቆጠርበትም ሁኔታ አለ፡፡ ይህም በህሙማኑ ስነልቦና ላይ ከባድ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ ስሙ በራሱ በጣም ይፈራል፡፡ እኔም አንድ ሰው በካንሰር ታመመ ከተባለ ውስጤ ይፈጠር የነበረው ተስፋ መቁረጥና ሀዘን ከፍተኛ ነበረ፡፡ ይህ ደግሞ የመዳን ተስፋን ያመነምናል፡፡ ይህንን ሁሉ ስናገር ህመሙ ቀላል ሆኖ አይደለም፡፡ ቀዶ ህክምናው ፣ ኬሞ ቴራፒው፣ የጎንዮሽ ጉዳቶቹ ሁሉ ተዳምረው ህመሙን በጣም ከባድ ያደርጉታል፡፡ ሆኖም ከቅድመ መከላከል ጀምሮ ሥራ ሊሰራበት ይገባል፡፡ አንዴ ህመሙ ካጋጠመ ደግሞ ተገቢውን የህክምና ክትትል በማድረግ ሊድን እንደሚችል ፤ ህክምናውም እየዘመነ መድሃኒቶቹም የጎንዮሽ ጉዳታቸው እየቀነሰ በመምጣቱ በጥንካሬና በእምነት ከታገሉት ማለፍ የሚቻል እንደሆነ ነገር ግን ቅድመ መከላከል ላይ በማተኮር ጤናማ የአኗኗር ዘዴን በመከተል ጤናማ ህይወት መምራት እንደሚቻል ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረት ማድረግ እንዳለብኝ በመገንዘቤ ካንሰር ላይ እየሰራሁ እገኛለሁ፡፡

## ላለፉት 22 ዓመታት ድርጅቱ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴና ለውጥ ምን ያህል አስደሳች ነው?

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የተቋቋመው ሁላችንም እንደምናውቀው ወ/ሮ አምሳለና አቶ ወንዱ "ማቲ" ብለው የሚጠሩትን 3ኛ ልጃቸውን በካንሰር ህመም ከዚህ ዓለም ከተሰናበተ በኋላ ነው፡፡ ዓላማውንም ወላጆች እነሱ ላይ የደረሰውን ሀዘን እና ፈተና ለሌሎች ጥሩ ዕድል መፍጠሪያ ብሎም የካንሰር ህመም ሊያደርስ የሚችለውን አስከፊ ጉዳት ማስቀረት ላይ አድርጎ ሀዘናቸውን ውጠው በጥንካሬ በመቆም በእግዚአበሔር እርዳታ የመሰረቱት ጥልቅ ተልዕኮ ያለው ድርጅት ነው፡፡ ለካንሰርና ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች አጋላጭ ምክንያቶችን ለመቀነስ እየሰራ ያለ ድርጅት ነው፡፡ ለዚህም ተግባር ከሀገር ውስጥም ሆነ በዓለማቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያገኘ ሲሆን ከጤና ሚኒስቴርና ከሌሎችም መንግስታዊ ተቋማት ጋር በመተባበር የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በአዲስ አበባ እና በተለያዩ ክልሎች በመተግበር ላይ የሚገኝ ሲሆን ለሀገርና ለማህበረሰብ እያበረከተ ያለው የበጎ አድራጎትና የልማት ሥራ የላቀ እንደሆነ መናገር ይቻላል፡፡

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ሲጀመር በካንሰር ህመም ላይ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ወደ ፕሮጀክት በማጠቃለል እየሰራ ይገኛል። ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ተያያዥ የሆኑ አጋላጭ ምክንያቶች እንዳላቸው ይታወቃል። አጋላጭ ሁኔታዎች (Risk Factors) ላይ መስራቱ ከቅድመ መከላከል ሥራዎች ዋናው እንደሆነ በመረዳት መስራቱ ጠቃሚ ሆኗል።

## በኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ምን ያህል አሳሳቢ እየሆኑ ነው?

ከተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ዋና ዋናዎቹ የልብ ህመም፣ ካንሰር ፣ የኩላሊት ህመም፣ ከመተንፈሻ አካላት ጋር የተገናኙ ህመሞች ፣ ስኳር ፣ የአእምሮ ጤናና ሌሎቹም በዓለማቀፍ ደረጃም ሆነ በኢትዮጵያ እየጨመሩ ያሉበት ሁኔታ ነው ያለው። በዓለም ላይ 70 በመቶ የሚሆኑ ሰዎች ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ህይወታቸውን እንደሚያጡ ጥናቶች ያመለክታሉ። በሀገራችን ከ 3 ሰዎች አንዱ ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች እንደሚያዝ ጥናቶች ያመለክታሉ። የዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ዕድሜያቸው ሳይደርስ ህይወታቸው የሚያልፍ ሰዎች ቁጥር 18.3 በመቶ እንደሆነ ያመለክታል። ከምጣኔ ሀብት ቀውስ አንጻር ደግሞ ኢትዮጵያ በየዓመቱ 31.3 ቢሊዮን ብር በእነዚህ ህመሞች ምክንያት ኢትዮጵያ እንደምታጣ አሳውቋል። ይህም አሳሳቢነቱ እየጨመረ መምጣቱን ይጠቁማል። በኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች እያደረሱ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ እየጨመረ መጥቷል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ በ 2022 በወጣው የፖሊሲ ብሪፍ መሰረት ህይወታቸውን ከሚያጡ ሰዎች ውስጥ 43ከመቶ የሚሆኑት በተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ማለትም በልብ ህመም፣ በካንሰር፣ በስኳር፣ በኩላሊትና በመሳሰሉት ምክንያት እንደሆነ ያሳያል። የህክምና አገልግሎቶች በበቂ ሁኔታ እነዚህን ህሙማን የማስተናገድ አቅማቸው ካለው የህመምተኛ ቁጥር አንጻር ዝቅተኛ መሆኑን ከተሰሩት ጥናቶች ለመገንዘብ ይቻላል። በታማሚዎችና በቤተሰቦቻቸው ላይ ከሚደርሰው የስነ ልቦና ጉዳት በተጨማሪ ህክምናውም ረጅም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑና አምራች የሆነውን የሰው ኃይል የሚጎዳ በመሆኑ ያልታቀደ ወጪ ይመጣል፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫናው በጣም ከባድ ነው። ጉዳቱ ዘርፈ ብዙ ነው። ለዚህም ነው ህመሙ የጤና ብቻ ሳይሆን የልማት ነው የሚባለው።

## የኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ህብረት መቼ ተቋቋመ? ዓላማው? ምንስ እየሰራ ይገኛል? ለህብረቱ መቋቋም የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን አስተዋጽኦ ምንድነው?

እየጨመረ የመጣውን የተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች አሳሳቢነት ለመታገል በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ የሚሰሩ 7 ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ህብረትን መስርተዋል። የዚህ ድርጅት ራዕይ ተላላፊ ካልሆኑ ህመሞች ነፃ የሆነ ማህበረሰብ መፍጠር ነው። ይህንን ድርጅት እ.ኤ.አ. 2012 የመሰረቱት አምስት ድርጅቶች ሲሆኑ ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ፣ የኢትዮጵያ ስኳር ማህበር፣ የኢትዮጵያ የልብ ማህበር፣ የኢትዮጵያ ኩላሊት ማህበር እንዲሁም የኢትዮጵያ ካንሰር አሶሴሽን ናቸው። ከምስረታው በኋላ የኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲና ዓለምፍሬ ፒንክ ሀውስ ካንሰር ፋውንዴሽን ጥምረቱን ተቀላቅለዋል።

የጥምረቱ ተልዕኮ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶችን በማስተባበር ህመሞቹን በመከላከልና በመቆጣጠር፣ በህሙማን ድጋፍና በፖሊሲ አድቮኬሲ እንዲሁም ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን ላይ በመስራት የማህበረሰባችንን ጤንነት ለመጠበቅ ያለመ ጥምረት ነው። ዋና ዋና ዓላማዎቹም በፖሊሲ አድቮኬሲ አዎንታዊ ሚና በመጫወት ጥሩ ውጤት ለማምጣት፣ የኢትዮጵያን የጤና ስርዓት ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ ሊሰጥ የሚገባውን ሚና ማጠናከር፣ በመረጃና ዕውቀት ላይ የተመሰረተ የመፍትሔ አካል ለመሆን እንዲሁም የአባል ድርጅቶችን አቅም መገንባትና ይህንን የመሰሉ ዓላማዎችን ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ለጥምረቱ መመስረት ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ከፍተኛውን አስተዋፅኦ አበርክቷል። ቢሮ በማመቻቸት፣ የሰው ኃይል ድጋፍ በማድረግ፣ የሰራተኛ ደመወዝና የተለያዩ ክፍያዎችን በመሸፈን፣ የጠቅላላ ጉባዔና የቦርድ ስብሰባዎችን በማካሄድ፣ የዓለማቀፉ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ህብረት አባል እንዲሆን በማድረግና የአባልነት መዋጮ በመሸፈን ጥምረቱ ህጋዊ እንዲሆን የጎላ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

## ዓበይት ክንውኖቹ ምን ምን ናቸው?

ከጥምረቱ አበይት ክንውኖች መካከል የጤና ሚኒስቴር ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን በተመለከተ ያወጣው እስትራቴጂክ ፍሬምወርክ መሠረት በማድረግ የብሔራዊ ካንሰር መቆጣጠሪያ ዕቅድ፣ ሌሎች የፖሊሲ ማሻሻያዎች፣ እንደ ትንባሆና አልኮል መጠጥ ያሉ ለተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች አጋላጭ ምርቶች ላይ ተጨማሪ ቀረጥና የማስታወቅያ ገደብ እንዲጣል ማድረግ በመሰሉት እንቅስቃሴዎች ላይ ከሚመለከታችው አካላት ጋር በመስራት አዎንታዊ መሻሻሎችን አስገኝቷል። በተጨማሪም ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን በተመለከተ የህሙማን ድምጽ በመሆን የፖሊሲ ትንታኔ በማዘጋጀት በዘርፉ የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል ብዬ አምናለሁ።

## በህብረት መንቀሳቀሱ ምን ያህል ጠቃሚ ነው?

ተመሳሳይ ዓላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አንድ ላይ በመተባበር ለማህበረሰቡ የተሻለ ጥቅም ያስገኛሉ ተብሎ ይታመናል። ከዚህም በመነሳት ነው ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች አብረው በመሆን ተሰሚነትና ተደራሽነትን ከማስፋት አንፃር እየሰሩ የሚገኙት።

## ህብረቱ ወደፊት ምን ምን ማከናወን ይፈልጋል?

ሀብት በማሰባሰብ፣ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በመተግበር ከመንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በአጋርነትና በቅርበት በመስራት ተመሳሳይ ዓላማ ይዘው ከሚሰሩ ማህበራት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ተቋማትን የህብረቱ አባል በማድረግ በጤናው ዘርፍ ጤናማ ሀገር ለመገንባት ስፊ የሆነ ማህበረሰብን ተጠቃሚ የማድረግ ትልቅ ራዕይ አለን። ይህንንም ዕውን ለማድረግ አባል ድርጅቶች፣ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ትብብር እንፈልጋለን። ይህንንም ለማሳካት ጠንክረን እንሰራለን።



# የክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ማኅበራት ኅብረት (CCRDA) ዋና ሥራ አስፈፃሚ

ዶ/ር ንጉሡ ለገሰ

ከምንም ነገር በፊት በልቤ ውስጥ ትልቅ ቦታ ስላለው አንድ ሰው ጥቂት ነገር ማለት እፈልጋለሁ። ይህ ጊዜ ይህንን የተለየ ሰው የምናከብርበትና በሥራዎቹ የምንደሰትበት ነው። ወንድሜ አቶ ወንዱ በቀለ ከህመም ጋር እየታገለ እያገገመ ሥራውን እየሰራ ይገኛል ። ይህ ከካንሰር ህመም ጋር እየታገሉ በስራ ገበታ ላይ መገኘት የማይታመን መስዋዕትነት ነው። እንዲህ ዓይነት ያልታሰቡ አጋጣሚዎች ከሰው አቅም በላይ ናቸው። አቶ ወንዱ ህይወቱን ለካንሰር ህሙማን ሰጥቶ ሲሰራ ቢቆይም አሁን ደግሞ እሱም የካንሰር ታማሚ ሆኖ ህክምናውን በሀገር ውስጥና በውጭ እየተከታተለ ይገኛል። ይህንን ትግል በብርታት፣ በፅናትና በትዕግስት እንዲያሸንፍ እንመኝለታለን። በግል ህይወቱ የተጋፈጠው ህመም ቀላል ባይሆንም ህይወቱን ከሰጠለት ለሌሎች የመቆም ዓላማ ወደኋላ አላለም።

ባለፉት ወራት ብዙዎቻችን ስለ አቶ ወንዱ መዳን ስንፀልይ ነበር። ተጨንቀን መዳኑን ጠብቀናል፤ በየህክምናው መሀል የሚልክልን የሚያበረታታ መልዕክትም በተስፋ እንድንጠብቅ አድርጎናል። ፈጣሪ ምላሽ ሰጥቶን አቶ ወንዱ ጤንነቱ እንዲሻሻል አድርጎልናል። የአቶ ወንዱ መዳን መባረክና ለሌሎች ምሳሌ መሆን ነው። ጥንካሬውም የሚደነቅ ነው። መዳን ብቻ ሳይሆን ካንሰርን ታግሎ የተመዘገበ ድል ነው። አቶ ወንዱ ቤተሰብህና ጓደኞችህ እንዲሁም ህይወትህን የሰጠህቸው በሺህ የሚቆጠሩ ህሙማን መሀል በጤና ለመቆም ያበቃህን ፈጣሪ አመሰግናለሁ። አቶ ወንዱ በልጃቸው ሞት ያሳለፉት ጥልቅ ሀዘን ለሀገር ተስፋ ሆኗል። የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ታሪክ የሚጀምረው በትንሹ ማቲዎስ ህልፈት ሳቢያ ቤተሰቡ ላይ ባጋጠመው ልብ የሚነካ ሐዘን ነው። ተወዳጁ ህፃን በለጋ ዕድሜው የተቀጨው በካንሰር ህመም ሳቢያ በ4ዓመት ዕድሜው ነበር።

አቶ ወንዱና ቤተሰቡ ዓለም ላይ ፊትን ከማዞር፣ በርን ዘግቶ ከማልቀስና በሐዘን ከመሰበር ይልቅ ልጃቸውን በማጣታቸው የደረሰባቸውን መሪር ሀዘን ወደ ሀገራዊ ተልዕኮ ለውጠዋል።

**አቶ ወንዱ በዚህ ሳቢያ መደበኛ ሥራውን ተወ፤ ዕውቀት ፣ ጉልበትና ጊዜውን ሁሉ ለወገኖቹ ለማዋል ወሰነ። ቀሪ ህይወቱን በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ላሉ ልጆችና ቤተሰቦች አዋለ። ስንቶቻችን ይህንን እናደርጋለን?**

**ብዙዎች በዚህ መሰል ችግር ውስጥ አልፈዋል ፤ ከማዘን ባሻገር ስንቶች ሌሎችን ማዳንን መርጠዋል? ይህ ቀላል መስዋዕትነት ብቻ ሳይሆን ለታላቅ ዓላማ ከፈጣሪ መመረጥ ጭምር ነው።**

የክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ማኅበራት ኅብረት (CCRDA) ለማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ትልቅ ክብር አለው። በሀገራችን የሰራቸው ስራዎች በኩራትና በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። ላስመዘገባቸው ልዩነት ያመጡ ሥራዎችም ዕድለኞች ነን። ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን እንደ 500ዎቹ የክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ማህበራት ኅብረት (CCRDA) አባል ድርጅት ብቻ አይደለም፤ የልዩ ብርታት ምሳሌ ስለሆነ በታላቅ አክብሮት ነው ዕውቅና የምንሰጠው። የፋውንዴሽኑ መስራች አቶ ወንዱ ህይወትህ ትልቅ መልዕክት ያለው አስተማሪ ነው። መነሻህ ሕፃኑ ማቲዎስ ድርጅቱ በደገፋቸው ቤተሰቦች በሁሉም ልብ ውስጥ አለ። አሁንም ረጅም ዕድሜና ጤና እመኝልሀለው። በመጨረሻም ሁላችንም ተባብረን ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን እንድንከላከል መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

# የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽንን እናስተዋውቅዎ

1

## ሚያዝያ 9 ቀን 1996 ዓ.ም

ቦሌ ሩዋንዳ በሚገኘው ደሳለኝ ሆቴል በተደረገው የፋውንዴሽኑ የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባዔ ተመሰረተ።

2

## ከሚያዝያ ዘጠኝ ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ታኅሳስ 2002 ዓ.ም ድረስ

ፋውንዴሽኑ በማቲዎስ ወንዱ ቤተሰቦች ያለአንዳች አስተዳደራዊ ወጪ በበጎ ፈቃድ ሰራተኞች /Volunteers/ ሲሰራ ቆይቷል። ከፋውንዴሽኑ መስራቾች አንዱ የሆኑት አቶ ወንዱ በቀለ በ6 ዓመት ውስጥ ሁለት ሥራ ለመያዝ ተገደዱ። የፋውንዴሽኑ ዋና ሥራአስኪያጅ ሆነው ያለአንዳች ደመወዝና ክፍያ፣ በብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት ደግሞ በጥሩ ደመወዝ ሲሰሩ ቆይተዋል። በኋላ ላይ ፋውንዴሽኑ የዓለማቀፍ ካንሰር ድርጅት አባል ሆኖ ባገኘው መጠነኛ ድጋፍ በ10 የተመረጡ ት/ቤቶች የፀረ ትምባሆ ዘመቻ ማካሄድ ሲጀምር አቶ ወንዱ በያዙዋቸው ሁለት ከፍተኛ ኃላፊነቶች መካከል የማይታረቅ ተቃርኖ ወይም /Conflict of Interest/ ተፈጠረ። በመጨረሻም አቶ ወንዱ ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ስለነበረባቸው በአገራቸውና ወገናቸው ላይ የመጣውን አደጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት ማቲን በማስታመም የፋይናንስ አቅማቸው የተዳከመ ቢሆንም ከብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን ለቀው ፋውንዴሽኑን በሙሉ ጊዜያቸው ተቀላቀሉ። ብሔራዊ ትምባሆ ድርጅትም ተገቢውን መሸኛ በማድረግ ወርቅ ሽልሞ አሰናበታቸው።

## የፋውንዴሽኑ የሠራተኛ ዓይነትና ብዛት

**አባላት ብዛት ከ1ሺህ 800 በላይ**

**በጎፈቃድ ሠራተኞች ብዛት ከ500 በላይ**

**የሥራ አመራር ቦርድ ብዛት 8 ሲሆን**

5 የቦርዱ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢን ጨምሮ

3 ዋና ሥራ አስፈፃሚው ያለ ድምፅ/

**ቋሚና ኮንትራት ሠራተኞች ብዛት 43 ሲሆኑ- 21 22**

**በትምህርት ደረጃ**

7 ፒ.ኤች.ዲና ዶክተሮች

13 የማስተርስ ዲግሪ ምሩቃን

10 የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን

13 ልዩ ልዩ

## ለሠራተኛ የሚሰጡ ደመወዝና ጥቅማጥቅም

- ፋውንዴሽኑ ለሰራተኞቹ የተለየ ክብርና ፍቅር ስላለው ባለው አቅም ለሠራተኞቹ ጥሩ ደመወዝ ይከፍላል። የሠራተኞቹ ደመወዝ በዶላር ሂሳብ ተከፍቶ የሚከፈል በመሆኑ በዶላር ምንዛሪ ምክንያት የሚከሰተውን ችግር ለመቋቋም ተችሏል።
- ፋውንዴሽኑ ለሰራተኞቹ 24ሰዓት የኢንዶውመንት መድን ሽፋን ገብቶላቸዋል በዚህም
  - ሠራተኛው በማናቸውም ምክንያት ከዚህ ዓለም ቢለይ የአንድ ዓመት ደመወዙን በአደጋ ምክንያት ከዚህ ዓለም ቢለይ የሁለት ዓመት ደመወዙን ለህጋዊ ወራሽ ይሰጣል።
  - ለቀብር ማስፈፀሚያና ለማስተዛዘኛም ይከፍላል። ሠራተኛው በህይወት በፋውንዴሽኑ አምስት ዓመት ከቆየ የአንድ ዓመት ደመወዝ ለራሱ ይከፈለዋል።
- ፋውንዴሽኑ ለሠራተኞቹ ካለው ክብርና ፍቅር የተነሳ ሠራተኛው ወደ ሥራ ሲገባም ሆነ ሲወጣ አይፈርምም፤ ለዚህ ተብሎ የተዘጋጀ የሠራተኛ የሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ሥርዓት የለም።
- ፋውንዴሽኑ የሠራተኛውን የሥራና ሥነስርዓት የሚቆጣጠርበት መመሪያ ያለው ቢሆንም ሠራተኛው ሲያጠፋ ወይም ጉድለት ሲያሳይ የሥነስርዓት ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የእርምት ርምጃ መውሰድና ከጥፋቱ እንዲማር በማድረግ ላይ ያተኩራል።

## 3

# ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ

ቦሌ ሸዋ ዳቦ ቤት ፊትለፊት በሚገኘው ጌቱ ኮሜርሽያል ህንፃ ላይ በመከራየትና አንድ ፀሐፊ፣ ሂሳብ ሰራተኛና ፕሮጀክት ኦፊሰር በመቅጠር ሥራውን ማካሄድ ጀመረ። ከዚያም፡-

- ቦሌ ደምበል ጀርባ ባለው ቦታ ቤት በመከራየት ለህሙማን አገልግሎት የሚሰጥ ማዕከል ከፈተ፤
- መገናኛ ሰፋ ያለ ጊቢ በመከራየት ለህሙማን የሚሰጠውን አገልግሎትና ለሠራተኞቹ የተሻለ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር ተቻለ፤
- እንግሊዝ ኤምባሲ ፊት ለፊት ገባ ብሎ ቤት በመከራየት ለህሙማኑም ሆነ ለሰራተኛው የተሻለ የሥራ ሁኔታ መፍጠር ተቻለ፤
- ከዚያም አሁን በሚገኝበት ቀበና በሚገኘው አንድ ፎቅ ሙሉውን በመከራየት ለሰራተኛው የተሻለ የስራ ቦታ ለመፍጠር ከመቻሉም በላይ ለህሙማኑ ለብቻቸው የተሻለ ማዕከል ለመፍጠር ቢቻልም ብዙ ሳይቆይ በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት ቤቱ በመፍረሱ ማዕከሉ ድንበሯ ሆስፒታል አጠገብ ቤት በመከራየት ወደዚያው እንዲዛወር ተደረገ።

## 4

# ከጥቅምት 2018 ዓ.ም ጀምሮ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በለሚኩራ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 ውስጥ ሰሚት ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ 10ሺህ ካሬሜትር ቦታ ሰጥቶን በመረከብ ላይ እንገኛለን። ባሁኑ ወቅትም ቦታውን ለማጠናከር የተለያዩ ግንባታዎችን በማካሄድ የጤናማ አፍሪካን ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ በዝግጅት ላይ እንገኛለን።

# የፋውንዴሽኑ ከሌሎች መ.ያ.ዶች በምን ይለያል

ለግልፅነትና ተጠያቂነት ሲባል የማቲዎስ ወንዱ ቤተሰቦች በተለይም የፋውንዴሽኑ ሰራተኞች ዘመዶች በአጠቃላይ በፋውንዴሽኑ እንዲቀጠሩና እንዲሠሩ አይፈቀድም ፤ ይህም በመመሪያ ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል፤

የፋውንዴሽኑ ጠቅላላ ጉባዔ ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባዎች ወቅታቸውን ጠብቀው መካሄዳቸው፤

ፋውንዴሽኑ የሚረዳቸው ህሙማን የፋውንዴሽኑ ባለድርሻ አካላት /Share Holders/ ባለቤቶች ተደርገው መቆጠራቸውና፤

IFRS /IPSAS ሥርዓትን ከ5 ዓመት በፊት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ካደረጉ ጥቂት መ.ያ.ዶች አንዱ መሆኑ፤

አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (AI)ና የድርጅቶች ሀብት ዕቅድ /Enterprise Resource Planning- ERP /ሥራ ላይ ካዋሉ ጥቂት መ.ያ.ዶች አንዱ መሆኑ፤

በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ዘንድ እጅግ የተከበረና የታመነ መሆኑ ወዘተ ናቸው።





# የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ዳይሬክተር

**አቶ ዘላለም መንግስቱ**

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የተቀላቀልኩት በ2006 ዓ.ም ነው። ያኔ ሁለትና ሦስት ፕሮጀክቶች ነበሩን። ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በአሁኑ ሰዓት 10 ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ፕሮጀክቶቻችንን ስንጀምር በካንሰር ነው የጀመርነው። የህፃናትና በሴቶች ካንሰር ላይ በተለይም የማህፀን በርና የጡት ካንሰር ላይ እንቅስቃሴ ስናደርግ ነበር። ለካንሰር አጋላጭ የሆኑትን እንደ ትምባሆ ያሉትን ለመቆጣጠር ፖሊሲዎች እንዲወጡ የተሳካ እንቅስቃሴ ተካሂዷል። አሁን ደግሞ በተለይም ከ2013ዓ.ም ጀምሮ ስትራቴጂክ ዕቅዳችንን አሻሽለን ሰፊ ወደሆነው የማይተላለፉ ህመሞች ላይ ትኩረት በማድረግ ከዚያ ጋር የተያያዙ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ እያደረግን ነው።

**ትንባሆ ቁጥጥር ላይ ትኩረት አድርገን የምንሰራባቸው ፕሮጀክቶች አሉን። በAfrica Capacity Building Foundation, Campaign for Tobacco Free Kids, Vital Strategies ድጋፍ ትምባሆ ቁጥጥር ላይ እንሰራለን። በGlobal Health Advocacy Incubators ድጋፍ ጤናማ አመጋገብ ፖሊሲ ለውጥ ለማምጣት የሚሰራ ፕሮጀክት አለን ። በ NCDI Poverty Network ድጋፍ የPEN-Plus ፕሮጀክት አማካይነት ተላላፊ ያልሆኑ ረጅም ጊዜ የሚቆዩ እንደ ስኳር፣ ልብና ደም ግፊትና የመሳሰሉት ህመሞችን በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ህክምና ለመስጠት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የሚያተኩር ፕሮጀክት አለን። በሳንባ ካንሰር መከላከልና ህክምና ላይ የሚተገበሩ ሁለት ፕሮጀክቶች አሉን።**

**በተጨማሪም አዲስ የጀመርነው Global Health Workforce Program Phase II በህክምና ባለሙያዎች አቅም ግንባታ ላይ የሚሠራ ፕሮጀክት ነው። ሌላው ደግሞ የኤ.አይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሳንባ ካንሰርን ለመለየት የሚረዳ ፕሮጀክት አለን። እነዚህ ላይ እየሰራን እንገኛለን።**

ከጊዜ ወደጊዜ ፕሮጀክቶችን የመተግበር አቅማችን እያደገ እና እየጨመረ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መጀመሪያ ላይ አነስተኛ ቁጥር የነበረውን የሰው ኃይል አቅማችንን አጠናክረናል፤ የፕሮጀክት ባለሙያዎች አሉን፣ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሟልተናል ፣ ራሱን የቻለ የኮሙኒኬሽንና ሀብት ማሰባሰብ ክፍል አለን፣የኦፕሬሽን ክፍል እየተጠናከረ ነው፡፡ ስለዚህ ድርጅቱ ይበልጥ እየተጠናከረ ስለመጣ የማስፈፀም አቅማችንም ከፍ ብሏል፡፡ የፕሮጀክት ባለሙያዎቻችንም የተለያዩ ስልጠናዎችን እያገኙ አቅማችው ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ ሄዷል፡፡አብዛኞቹ ነባር ሰራተኞች ናቸው እነሱን እያሳደግን አዳዲስ ሰራተኞችንም እየቀጠርን ነው ያለነው፡፡ ይህም ለፕሮጀክት መፈጸም አቅማችን ማደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

አዳዲስ አሰራሮችን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ አንዱ ያደረግነው ነገር ፕሮጀክቶቻችንን ስንቀርጽ ማሻሻያዎች ማድረግ ነው፡፡ ውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ አስገብተን የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን ፕሮጀክቶች መቅረጽ አዲሱ አሰራራችን ነው፡፡ ሌላው በዓለማቀፍ ደረጃ ለውጦች አሉ፤ እንደ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ዲጂታል ሄልዝ ያሉትን ለማካተት እንቅስቃሴ እያደረግን ነው፡፡ የአሰራር ስርዓታችንን ዲጂታላይዝ በማድረግ አሰራራችንን የማዘመን ሥራ እየሰራን ነው፡፡ ይህንን የሚያጠናክር የሰው ኃይል እየገነባን ነው ያለነው፡፡ ለቀጣይ አምስት ዓመታት ውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ፣ ሰፊና ለውጦችን ማስተናገድ የሚችል የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ቀርፀናል፡፡

ድርጅቱ 20ኛ ዓመቱን ሲያከብር ቆም ብለን ከዚህ በፊት የነበሩትን ሥራዎቻችንን ለመመልከት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮልናል፡፡ ድርጅቱ ከዚህ በኋላ እንዴት መሄድ እንዳለበት ቆም ብሎ እንዲያስብ አስችሎታል፡፡ ባለፉት 22 ዓመታት በተለያየ መንገድ ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩ አካላትን ዕውቅና ለመስጠትና ለማመስገን አጋጣሚውን ፈጥሮልን አልፏል፡፡ ድርጅቱንም ሌሎች እንዲያዩት ዕድል ፈጥሯል፡፡ ያደረግናቸው የሚዲያ እንቅስቃሴዎች የፋውንዴሽኑን ታዋቂነት ከፍ አድርገዋል፡፡

እንደምናውቀው ፋውንዴሽኑ ከመኖሪያ ቤት ነው የተነሳው፤ በካንሰር ምክንያት ልጁን ያጣ ቤተሰብና ሌሎች በጎ ፈቃደኞች ተባብረው የመሰረቱት ድርጅት ነው፡፡ አሁን ያለበት ሁኔታ ከፍተኛ ለውጥ የሚያሳይ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ በቂ ነው ማለት አይደለም፡፡ ድርጅቱ ከዚህ በላይ የማደግ አቅም አለው፡፡ ያንን አቅም በመጠቀም አሁን ካለበት ወደተሻለ ደረጃ ከፍ እንዲል መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ ድርጅቱን በመወከል ፕሮጀክቶቻችንን በተመለከተ በሀገር አቀፍም ሆነ በዓለማቀፍ ደረጃ የተለያዩ ስብሰባዎች የመሳተፍ ዕድል አግኝቻለሁ ፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ በፌደራልም ሆነ በክልል የተዘጋጁ የተለያዩ ፕሮግራሞችና ዓመታዊ ስብሰባዎች ላይ ተሳትፌያለሁ፡፡

በዓለማቀፍ ደረጃም በተለያዩ ሀገራት የተካሄዱ ትልልቅ ስብሰባዎች ፣ ልምድ መለዋወጫ መድረኮችና ስልጠናዎች ላይ ተገኝቻለሁ፡፡ በውጭ ያሉ ደጋፊዎቻችን ለኛ ያላቸው አመለካከት በጣም ጥሩ ነው፡፡ ለማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ትልቅ አክብሮት አላቸው፡፡ እስካሁን የተሰጡንና ፕሮጀክቶች በአግባቡና በከፍተኛ ጥራት ተግባራዊ በማድረጋችን ከግብረሰናይ ድርጅቶች በአፈፃፀማችን ምሳሌ አድርገው ነው የሚመለከቱን፡፡

ድጋፍ የሚያደርጉልን አጋር አካላቶቻችን ዓለም ላይ ከተለያዩ ሀገራት ጋር ይሰራሉ፤ በተለይ ከአፍሪካ ሀገራት አንፃር በተሻለ ሁኔታ የሰጡትን ፈንድ በአግባቡ በመጠቀም ምሳሌ አድርገው የኛን ፋውንዴሽን ይጠቅሱታል፡፡ ፋውንዴሽን ብቻ ሳይሆን ለሠራተኞቹም የተለየ አክብሮት ነው ያላቸው፡፡ ይህንን መልካም ገፅታ ገንብተን ይዘን እንቀጥላለን፡፡

በሀገር ውስጥም ከጤና ሚኒስቴር ጀምሮ በጋራ ከምንሰራቸው አጋር አካላት ጋር በጣም ጥሩ የሥራ ግንኙነት ነው ያለን፡፡ ሠራተኞቻችንም አቅም እንዳላቸው፤ በስነምግባር የተሞሉ እንደሆኑ ፤ ለሥራዎቻቸው ትኩረት ሰጥተው እንደሚሰሩ ይመሰክራሉ፡፡

አሁን የምንሰራበት ዘርፍ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት በጣም ፈታኝ ነው፡፡ ዓለማቀፉ ሁኔታ ይህንን ፈታኝ ያደርገዋል፡፡ እንደዚያም ሆኖ በምንመራቸው ፕሮጀክቶች ላይ ፈታኝ ነገሮች አልገጠሙንም፡፡ የሀብት ማሰባሰብና ኮሙኒኬሽን ክፍላችን አጠናክረን ብዙ ፕሮጀክቶችን በመፈለግ ያሉንን ፕሮጀክቶች ቁጥርና የጊዜ ገደባቸውን በመጨመር፤ ያለንን የሀብት የፈንድ መጠን ከፍ በማድረግ ፤ ሰፋ ያለ ተጽዕኖ መፍጠር የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ለማምጣት እንቅስቃሴ እያደረግን ነው፡፡

እስካሁን ባለው ሁኔታ ድርጅቱ ወደፊት እየተራመደ ነው ፡፡ ይህንን የበለጠ ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ስትራቴጂክ ዕቅዳችንን በመቅረጽ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን በመተንተን ከዚያ በምናገኘው አቅጣጫ የተሻለ አፈጻጸም ይኖረናል፡፡ አሁን አዲስ የጀመርነው Global Health Work Force ፕሮጀክትን ነው፡፡ የ Campaign for Tobacco Free Kids የትንባሆ ቁጥጥር ሥራዎች ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርሱ መንግስት በቂ የሆነ በጀት እንዲመድብ ፕሮጀክት ቀርፀናል፡፡ ከአፍሪካ እኛና ናይጄሪያ ብቻ ይህንን ዕድል አግኝተናል፡፡ በናይጄሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና ወስደናል፡፡ ይህንን ፕሮጀክት ለመተግበር እንቅስቃሴ እያደረግን ነው፡፡

በድርጅቱ ከአስር ዓመት በላይ ቆይቻለሁ፤ ፋውንዴሽኑ ፈጣን እድገት እያደገ ነው፡፡ በዚህ ሳይወሰን ሰፋ ባለ መልኩ መስራት አለበት፡፡ በሚቀጥሉት አምስትና አሥር ዓመታት በሰው ኃይል፣ በፕሮጀክት ቁጥርና ተፅዕኖ በመፍጠርም የተሻለ ደረጃ እንዲደርስ እፈልጋለሁ፡፡

# የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ፕሮጀክቶች

1

## የህፃናት ካንሰር ፕሮጀክት

**ግብ** በካንሰር ለተያዙ ህፃናት ሁሉን አቀፍ እንክብካቤ መስጠት፡፡
**የደጋፊ አጋር ስም** ቋሚ የገንዘብ ድጋፍና አጋር ባይኖረውም የተለያዩ ሃገር በቀል ድርጅቶችና ግለሰቦች እርዳታ እያደረጉለት ነው፡፡
**የተጀመረበት ጊዜ** 1996ዓ.ም
**የትግበራ ቦታ** በ ፓንጋሲሌ ሚሻሌ የማህበራዊና የስነልቦናዊ ድጋፍ ማዕከል, 22 ድንበሯ ሆስፒታል አጠገብ፣ አዲስአበባ፣ ኢትዮጵያ,
**ወቅታዊ ደረጃ** እስከዛሬ ከ3,000 በላይ የካንሰር ታካሚዎችና ቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ያገኙ ሲሆን በአሁኑ ሰአት 176 ታካሚዎችና ቤተሰቦቻቸው ድጋፍ እያገኙ ይገኛል፡፡
**የወደፊት እቅድ** ወደ ሄልዚ አፍሪካ ፕሮጀክት በማሳደግ ተደራሽነቱን ማስፋት
**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** የካንሰር ታማሚ ህጻናትና አስታማሚዎቻቸውን ለመደገፍ የሚወጣው ወጪ ከፍተኛና በአገር ውስጥ ደጋፊዎች ብቻ የሚታገዝ በመሆኑ ሁላችሁም የአቅማችሁን ሁሉ ድጋፍ እንድታደርጉ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

2

## የትምባሆ ቁጥጥር ፕሮጀክት

**ግብ** ከትምባሆ ጭስ ነፃ የሆኑ የህዝብ መገልገያ ቦታዎችን መፍጠር፣ በተለይም በችርቻሮ መሸጫ ቦታዎች የትምባሆ ማስታወቂያ፣ ፕሮሞሽንና ማስተዋወቅን መቆጣጠር፣ ሶስተኛው ዙር የጤና ማስጠንቀቂያ በሲጋራ ፓኬቶች ላይ ተግባራዊ እንዲሆንና የትምባሆ ቁጥጥር ስራዎች ውጤታማና ዘላቂ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማስቻል ቋሚ የመንግስት በጀት እንዲመደብለት የአድቮኬሲ ስራዎችን መስራት፡፡
**የደጋፊ አጋር ስም** ካምፔይን ፎር ቶባኮ ፍሪ ኪድስ (CTFK)
**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ
**የትግበራ ቦታ** በፌደራልና በተመረጡ ክልሎች እንዲሁም በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ
**ወቅታዊ ደረጃ**
- የተመረጡ ክልሎች ማለትም አፋር፣ ሶማሌና ድሬዳዋ የትምባሆ ቁጥጥር ማስፈፀሚያ ደንብ እንዲኖራቸው ሆኗል፡፡
- የሲጋራ ምርቶች ማሸጊያ/ ፓኬቶች ላይ 3ተኛ ዙር የጤና ማስጠንቀቂያዎች ተግባራዊ እንዲደረጉና ለቀጣይ ዙሮች ደግሞ አገልግሎት ላይ የሚዉሉ ሀገራዊ ምስሎች እንዲዘጋጁ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡
- እንዲሁም በአዲስ አበባ በሶስት ክፍለ-ከተሞች ከትምባሆ ጭስ-ነጻ ፖሊሲ እንዲተገበር በመደገፍና ከጭስ ነፃ አካባቢ የፈጠሩ ሞዴል ተቋማትን እውቅና በመስጠት ሀገራዊ የትምባሆ ቁጥጥር ጥረቶች ይበልጥ እንዲጠናከሩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

**የወደፊት እቅድ**
- የአዲስ አበባ ከተማ ከትምባሆ ጭስ ነጻ ኢንሼቲቭ አጠናክሮ ማስቀጠል፤ የሚደገፉ ክፍለ ከተሞችንና ከትምባሆ ጭስ ነፃ የሆኑ የህዝብ መገልገያ ቦታዎችን ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ፤
- ቀጥተኛ ያልሆነ (indirect) የትምባሆ ምርቶችን ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞትና ስፖንሰር ማድረግ ክልከላ በበቂ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲደረግ መደገፍና
- ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር መንግስት ለትምባሆ ቁጥጥር ቋሚና ዘላቂ በጀት እንዲመደብለት የአድቮኬሲ ስራዎችን መስራት ነው፡፡

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** ጠንካራ ህግ ማውጣት ብቻ ተፈላጊውን ለውጥ ሊያመጣ አይችልም፤ ህግም ያለ በጀት ድጋፍ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም እንደአለም ምሳሌ የሆነው ህጋችን ሞዴል ሆኖ እንዲቀጥል መንግስት ለትምባሆ ቁጥጥር በጀት ሊመድብለትና አሁን የተጀመሩ ምርጥ ተሞክሮዎች ዘላቂነታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

3

## የትምባሆ ቁጥጥር ፕሮጀክት

**ግብ** የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽንን ተቋማዊና የሠራተኛ አቅምን በመገንባት የተቋሙን የድጋፍ ምንጮች አስፍቶ ቀጣይነትና እውቅናውን ለማሻሻል የሚረዱ መሰረቶችን መጣል፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ የትምባሆ ቁጥጥር ስነ-ምህዳርን ማስፋት፣ ማጠናከርና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ

**የደጋፊ አጋር ስም** አፍሪካ ካፓሲቲ ቢዉልዲንግ ፋውንዴሽን (ACBF)

**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) ከ2016 ጀምሮ በየ3 አመቱ እየታደሰ የቆየ ፕሮጀክት ሲሆን በአሁኑ ጊዜም 3ኛውን ዙር ፕሮጀክት እየተገበርን እንገኛለን

**የትግበራ ቦታ** በፌደራል (ብሔራዊ) ደረጃና በአዲስ አበባ

**ወቅታዊ ደረጃ**
- ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የተቋሙን ስያሜ ከማደስ አንስቶ የመለያ (logo) ና ሌሎች መዋቅራዊ ለውጦችን አድርጓል፤ መተዳደሪያ ደንቡን ጨምሮ ማንዋሎችንና ስትራቴጂክ ፕላኑን በአዲስ መልክ አሻሽሏል። ከዘመኑ ጋር ለመራመድ በAI/ERP የታገዘ ሲስተምን ተግባራዊ ለማድረግ በጥረት ላይ ይገኛል።
- በብሔራዊ እንዲሁም በአዲስ አበባ የሚገኙ የትምባሆ ቁጥጥር አስተባባሪ ኮሚቴዎችን በአዲስ መልክ እንዲደራጁ በማድረግ ለዘላቂ የትምባሆ ቁጥጥር ፕሮግራም ጠንካራ መሰረት ጥሏል።

**የወደፊት እቅድ**
- የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽንን ተቋማዊ አቅምና እውቀት ጎልብቶ ማየት፤ እንዲሁም የድጋፍ ምንጮቹ ተስፋፍተው ዘላቂነቱን ያረጋገጠና በሀገሪቱ ለህብረተሰብ ጤና መሻሻል አተኩረው ከሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል ግንባር ቀደም (ሞዴል) ተቋም ሆኖ መገኘት ነው።
- በኢትዮጵያ ከፌደራል አንስቶ እስከ ክልሎች ድረስ የትምባሆ ቁጥጥር ስራዎች ወጥነት ባለው መልኩ ይበልጥ ተጠናክረው፣ የሴክተሮች ቅንጅት ጎልብቶ ውጤታማና ቀጣይነት ያለው የቁጥጥርና የህግ አተገባበር እንዲኖር ማድረግ ነው።

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** የትምባሆ ቁጥጥር ስራ በተወሰነ ሴክተር ጥረት ብቻ ውጤታማ ሊሆን ስለማይችል ሁሉም ሴክተር የበኩሉን ሚና እንዲወጣ።

4

## ምዕራፍ አንድ እና ሁለት በኢትዮጵያ የሳንባ ካንሰር ምርመራና ቁጥጥር ፕሮጀክት /MLCCP/

**ግብ** በኢትዮጵያ በሚገኙ አራት ክልሎች የሳንባ ካንሰር የምርመራና ህክምና አገልግሎትን ማሻሻል

**የደጋፊ አጋር ስም** ብሪስተል ማየርስ ስክዊብ ፋውንዴሽን (BMSF)

**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) ጥር 01, 2020

**አጋር ድርጅቶች** አምሬፍ ሄልዝ አፍሪካ(በአፋር ክልል)፣ ዶክተርስ ዊዝ አፍሪካ ኩዋም (በኦሮሚያ ክልል)፣ ሜሪ ጆይ፣ የኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲ (አዲስ አበባ)ሲሆኑ ማ.ወ.ፋ የመሪነት ሚና እየተወጣ ነው

**የትግበራ ቦታ** በአዲስ አበባ በአለርትና ጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታሎችና አራት ጤና ጣቢያዎች፣ በአማራ ክልል ደብረብርሃን፣ ደሴና ኮምቦልቻ አጠቃላይ ሆስፒታሎችና ሶስት ጤና ጣቢያዎች

**ወቅታዊ ደረጃ** ምዕራፍ ሁለትን በማጠናቀቅ ወደ ምዕራፍ ሦስት ለመሸጋገር በዝግጅት ላይ ይገኛል

**የወደፊት እቅድ** የወደፊት ዕቅዱ የፕሮጀክቱን ትግበራ በተደራሽነትም ሆነ በአገልግሎት ዓይነት ማስፋት

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** የሳንባ ካንሰር ቅድመ ልየታ፣ ምርመራና ህክምና የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ህሙማኖችን በቶሎ መለየትና ታክመው እንዲድኑ ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል። በመሆኑም ግንዛቤ በመፍጠርና፣ የህክምናውን አሰጣጥ በመደገፍና በማጠናከር ረገድ ሁሉም የበኩሉን እንዲያደርግ ጥሪ እናቀርባለን።

5

## ፔን ፕላስ ፕሮጀክት

**ግብ** ከባድ የሆኑ እና የረጅም ጊዜ ህክምና ክትትል ለሚፈልጉ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን (NCDs) ጥራት ያለውን እንክብካቤ በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ላይ አጣምሮ በመስጠት፣ ለገጠሩ ማህበረሰብ ፍትሃዊና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ማድረስና ማሻሻል።

**የደጋፊ አጋር ስም** ኤን-ሲ-ዲ-አይ ፖቨርቲ ኔትወርክ (NCDI Poverty Network)

**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) ሴፕቴምበር 2022

**የትግበራ ቦታ** አዲስ ዘመን መጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል – አማራ ክልልና ሙከ ጡሪ መጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል – ኦሮሚያ ክልል

**ወቅታዊ ደረጃ** ከ815 በላይ ከባድ የሆኑና የረጅም ጊዜ ህክምና ክትትል የሚፈልጉ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች (NCDs) ያላቸው ታካሚዎች ጥራት ያለው የህክምና ክትትል እያገኙ ይገኛሉ። እነዚህም ዓይነት 1 የስኳር ህመም፣ የሩማቲክ የልብ ህመም፣ ከባድ የደም ግፊት፣ የልብ ድካም፣ ሌሎች የልብ ችግሮችና ከባድ የአስም ወይም የመተንፈሻ ቧንቧ ህመሞች ያለባቸው ታካሚዎች ናቸው። ፕሮጀክቱ ያመጣው ውጤት እጅግ አመርቂ ነው። ዓይነት 1 የስኳር ህመም ታካሚዎች ውስጥ የHbA1c አማካይ ውጤት ከ9.3% ወደ 7.8% በማሻሻል የደም ውስጥ ስኳር መጠን በመቆጣጠር የተሻለ የህክምና ለውጥ መምጣቱን ያሳያል። የሩማቲክ የልብ ህመም ያለባቸው ታካሚዎች ሕይወት አድንና አስፈላጊ የልብ ቀዶ ህክምና የvalvotomyና የልብ ቀዶ ጥገና ህክምና ተሰጥቷቸዋል። በተጨማሪም የህክምና ጥራት በመሻሻሉ የታካሚዎች በሆስፒታል ተኝቶ መታከም ደረጃ ያስፈለጋቸው ታካሚዎች ቁጥር ቀንሷል። የሞት ምጣኔም ቀንሷል፣ ታካሚዎችም በአገልግሎቱ ከፍተኛ እርካታ እና የጤናቸውን መሻሻል እንዳዩ ሪፖርት አድርገዋል።

**የወደፊት እቅድ** በሚቀጥሉት ዓመታት እስከ 2030 በሀገር አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ በ150 የመጀመርያ ደረጃ ሆስፒታሎች ለማስፋፋት የአገሪቱ የኦፕሬሽናል እቅድ ተዘጋጅቶ በመጠናቀቅ ኦፊሴላዊ በሆነ ሁኔታ ተመርቆ ሥራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ነው።

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** በተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ዙሪያ በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የሚደረገው የህክምና ጥረት መልካም ውጤቶችን ያሳየ በመሆኑ የበለጠ እንዲሰፋና ተደራሽ እንዲሆን የሁሉም አካላት ድጋፍና ርብርብ ያስፈልጋል።

6

## የሳንባ ካንሰር ህክምና አገልግሎትን ጥራት ለማሳደግ ዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማጠናከር

**ግብ** የሳንባ ካንሰር ህሙማንን የህክምና አገልግሎትና ውጤት ማሻሻል

**የደጋፊ አጋር ስም** ላንግ አምቢሽን አላያንስ፣ አስትራዜኒካ (Lung Ambition Alliance, Astra Zeneca)

**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) የካቲት 01, 2023

**የትግበራ ቦታ** በጥቁር አንበሳ፣ ጅማ፣ሃዋሳና ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎችና በቅዱስ ጳውሎስ ሚሌኒየም ሕክምና ኮሌጅ

**ወቅታዊ ደረጃ** ተጠናቋል፣ ሁለተኛው ዙር በቅርቡ ለመጀመር ዝግጅት እየተደረገ ነው

**የወደፊት እቅድ** ወደ ምዕራፍ ሁለት በመሸጋገር ሌሎች ሆስፒታሎችን ማካተት

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** ዘርፈ ብዙ የባለሙያዎች ቡድንን ማጠናከር በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን ለመወሰንና የህሙማኑን ህክምና ውጤት ለማሻሻል አይነተኛ መንገድ ነው። ስለሆነም ትኩረት ሰጥተን የበለጠ እንድንሰራበት ጥሪ እናቀርባለን።

7

## ሳንባ ካንሰር ፕሮጀክት IELCAP

**ግብ** በ LDCT (ሎው ዶዝ ሲቲ ስካን) የሚደረግ የሳንባ ካንሰር ቅድመ ልየታ የምርመራ ስርዓትን በሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) የተደገፈ በማድረግ ማጠናከርና አገልግሎቱን በኢትዮጵያ በሚገኙ ሆስፒታሎች ማስፋፋት

**የደጋፊ አጋር ስም** ብሪስተል ማየርስ ስክዊብ ፋውንዴሽን (BMSF)

**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) ሰኔ 1, 2024

**የትግበራ ቦታ** በጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሌኒየም ሕክምና ኮሌጅ

**ወቅታዊ ደረጃ** የሳንባ ካንሰር ታማሚዎች የተለዩ ሲሆን በሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) የተደገፈ ሎው ዶዝ ሲቲ ስካን (LDCT) የሚደረግ ምርመራ በሁለቱ ማዕከሎች ስራውን ጀምሯል።

**የወደፊት እቅድ** ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ የመጀመሪያው በመሆኑ ወደፊት ሥራውን በማስፋፋት በኢትዮጵያ ተጨማሪ ሆስፒታሎች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዷል

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** እንደ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ባሉ ቴክኖሎጂዎች ታግዞ የሳንባ ካንሰር ልየታ ማድረግ ሀብትን ቆጣቢ እንዲሁም ውጤታማ የሚያደርግ የቴክኖሎጂ አሰራር በመሆኑ የበለጠ ልንሰራበትና ልናሰፋው ይገባል። ለዚህም የሁላችሁም ትብብርና ድጋፍ ያስፈልጋል።

8

## የምግብ ቁጥጥር ፖሊሲ ለዉጥ ፕሮጀክት

**ግብ** በኢትዮጵያ የታሸጉና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችን ለመቆጣጠር የሚረዳ አዋጅ እንዲፀድቅ ድጋፍ ማድረግ።

**የደጋፊ አጋር ስም** ግሎባል ኼልዝ አድቮኬሲ ኢንኩቤተር (GHAI)

**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) 2022

በአሁኑ ግዜ እ.ኤ.አ ከየካቲት 1, 2025 - ጥር 31, 2026 የሚቆይ ፕሮጀክት እየተገበርን እንገኛለን።

**የትግበራ ቦታ** በሀገር አቀፍ ደረጃ

**ወቅታዊ ደረጃ** የአለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን መሰረት ያደረገና ጤናማ ያልሆኑና የታሸጉ ምግቦችን ለመቆጣጠር የሚረዱ መሰረታዊ የህግ ድንጋጌዎችን የያዘ ረቂቅ አዋጅ በጤና ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣን እንዲሁም በሚመለከታቸው አጋር አካላት በጋራ የተዘጋጀ ሲሆን ረቂቅ አዋጁ በበቂ ሁኔታ ከሚመለከታቸው የክልል እና የፌደራል ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ተደርጎበታል። ከምክክር መድረኮቹ የተገኙ ግብረ መልሶች ተካተውበት በአሁኑ ጊዜ ረቂቅ አዋጁ በሚመለከታቸው የህግ አውጪ አካላት እንዲታይና እንዲተች ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኳል።

**የወደፊት እቅድ** - የረቂቅ አዋጁን አስፈላጊነት በተመለከተ ለተቀሩት ፖሊሲ አዉጪ የመንግስት አካላት ግንዛቤ ማስጨበጥ።

- የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማስፋት ሰፊ የሚዲያ ንቅናቄዎችን መስራት፣
- የኢንዱስትሪ ጣልቃ ገብነት ስልቶችን በንቃት መከታተል፣ መረጃ መሰብሰብ እና ወቅቱን የጠበቀ ግብረ መልስ መስጠት፣

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** አዋጁን ለማፀደቅ እየተደረገ ባለው ጥረት ውስጥ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እያሳዩ ያለውን ቁርጠኝነትና እየተወጡ ያለውን ሀላፊነት አጠናክረው እንዲቀጥሉ፤ የተጀመሩ ስራዎች የታለመላቸውን ግብ እንዲመቱ በዶነር በኩል ያለው የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል።

9

## የትምባሆ ቁጥጥር ፕሮጀክት

**ግብ** አስር የተመረጡ የፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የ WHO FCTC አንቀፅ 5.3 ና የኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት አስተዳደር 1112/2011ን መሰረት ያደረገ የሥነ ምግባር ደንብ እንዲያፀድቁ ማድረግ።

**የደጋፊ አጋር ስም** ቫይታል ስትራቴጂስ (VS)

**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) 2025

**የትግበራ ቦታ** በአዲስ አባባና በክልል ከተሞች

**ወቅታዊ ደረጃ** በተመረጡ የመንግስት ሚኒስትር መስሪያ ቤቶችና በትምባሆ ኢንዱስትሪ መካከል ያለውን ያልተገባ ግንኙነትና ተፅዕኖ በመገምገም አብዛኛው የብሄራዊ ትምባሆ ቁጥጥር አስተባባሪ አካላት ከትምባሆ ኢንዱስትሪ ጋር የሚኖራችውን ያልተገባ ግንኙነት ግልፅና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን የስነ ምግባር ደንብ ተቀብለው አፅድቀዋል/ ፈርመዋል።

**የወደፊት እቅድ** ፕሮጀክቱ ከአላማው በላይ በማሳካት ተጠናቋል። ይህም ማለት ፕሮጀክቱ 10 ተቋማትን ብቻ ኢላማ ያደረገ ቢሆንም 23 ተቋማት በተሳካ ሁኔታ የስነ ምግባር ደንቡን ማፅደቃቸውን በፊርማቸው አረጋግጠዋል።

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** የስነ ምግባር ደንቡን የፈረሙ አካላት በተገቢው ሁኔታ እንዲተገብሩትና የትምባሆ ኢንዱስትሪ ጫናን በተገቢዉ ሁኔታ በመከላከል ለተሳካና ለተቀናጀ ሀገራዊ የትምባሆ ቁጥጥር ስራ የበኩላቸውን ሀላፊነትና ድርሻ እንዲወጡ፣ የኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣንም ክትትልና ግምገማውን አጠናክሮ እንዲቀጥል።

10

## ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችና የአዕምሮ ጤና ዙርያ የጤና ባለሞያዎችን አቅም ግንባታ ፕሮጀክት

**ግብ** በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ (CPD) ማዕከላትን በረዘም ያለ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች (NCDS)ና በአእምሮ ጤና ላይ አቅማቸውን በመሻሻል ማጠናከር።

**የደጋፊ አጋር ስም** ግሎባል ኼልዝ ፓርትነርሺፕስ (GHP, Formerly THET)

**የተጀመረበት ጊዜ** (እ.ኤ.አ) ግንቦት 2025

**የትግበራ ቦታ** የጤና ሚኒስቴር ፣ ቅ/ ጴጥሮስ አጠቃላይ ኮምፕሪሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የኢትዮጵያ የውስጥ ደዌ ሕክምና ማህበር፣ አዳማ ሜዲካል ኮሌጅ ሆስፒታል፣ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ አስራት ወልደየስ ጤና ሳይንስ ካምፓስ፣ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ

**ወቅታዊ ደረጃ** ዋና ዓላማው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ (CPD) አቅምና ዘመናዊነትን ለማጠናከር ሲሆን ፕሮጀክቱ ሰባቱ የCPD ማዕከላትን ጥራት ያለው ስልጠና ለመስጠት እንዲችሉ አቅማቸውን አጠናክሯል:: በተጨማሪም ፕሮጀክቱ የጤና ሚንስቴርን CPD መረጃ አስተዳደርን በመሻሻል የጤና የሰው ኃይል መረጃ ሥርዓት (IHRIS) ስርዓት ላይ ማሻሻያዎችን በማካተት ለመስራት ያለመ ነው። እንዲሁም የስልጠና ተደራሽነትና ዘመናዊነትን ለማስፋት በዲጂታል የስልጠና ሥርዓት አማካይነት ስልጠናዎችን ለመስጠት ያለመ ነው።

**የወደፊት እቅድ** ወደፊት ፕሮጀክቱ በCPD ተደራሽነትና ጥራት ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራል።

**የድጋፍና የትብብር ጥሪ** የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ(CPD)የጤና ባለሙያዎችን አቅም በመገንባት የተሻለ የአገልግሎት ጥራትና ውጤት የሚያረጋግጥ በመሆኑ የሚቻለውን ድጋፍና ጥረት እንዲያደርጉ እንጠይቃለን::::

ዘመን ባንክ
Zemen
BANK



**ዘመን ባንክ ለማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን**

የአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ድጋፍ አድርጓል



# የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ኦፕሬሽን ዳይሬክተር

**አቶ ለማ አየለ**

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽንን ከተቀላቀልኩ 14 ዓመት ሆኖኛል፡፡አስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ ሆኜ ነው ፋውንዴሽኑን የተቀላቀልኩት፡፡ ድርጅቱን ለ14 ዓመታት አውቀዋለሁ፡፡ የዛሬ 14 ዓመት ቤት ይሰራ ከነበረበት ወደ ቢሮ መከራየት የመጣበትና በአነስተኛ አቅም የሚሰራበት ጊዜ ነበረ፡፡ ነገር ግን በቤትም ውስጥ ለ6 ዓመታት ሰርቶ ስለነበር የፋይናንስ አቅሙ ደካማ ቢሆንም ብዙ ሥራዎችን እየሰራ የነበረ ድርጅት ነው፡፡ አሁን ግን ባለበት ሁኔታ በጣም ትልቅ በአንዳንድ ሥራዎች ዓለማቀፍ ግብረሰናይ ድርጅቶችን ሳይቀር የሚመራ ማንኛውንም ፕሮጀክት መተግበር የሚችል ከፍተኛ አቅምና ብቁ የሰው ኃይል የገነባ ታዋቂ፤ ትልቅ ስም የገነባ ድርጅት ሆኗል፡፡

ህሙማንን በተመለከተ ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የተለየ የሚያደርገው በርዳታ መልክ የተለየ ነገር አያደርግም፡፡ ሌሎች ድርጅቶች አንድ ነገር ብቻ ሊደግፉ ይችላሉ፡፡ ማቲዎስ ወንዱ ግን ድጋፉ ሙሉ ነው፡፡ ከቤታቸው መጥተው እስከሚመለሱ ሙሉ የትራንስፖርት ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በህክምና ሂደት የሚያስፈልጋቸውንና መንግስት ማቅረብ ያልቻላቸውን የምርመራና የመድሃኒት ግዢን የመሳሰሉ ሌሎች ወጪዎችን በሙሉ በተለይ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የማይገኙትን ሙሉ ለሙሉ ያቀርባል፡፡ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልም ሲተኙ ለጥቃቅን ወጪ መሸፈኛ በየወሩ አንድ ሺህ ብር ይሰጣል፤ እንዲሁም በህክምና መካከል ትምህርታቸውን ለሚማሩት በየወሩ አንድ ሺህ ብር ይሰጣል፡፡ በገንዘብ ማጣት ከትምህርት ገበታ እንዳይለዩ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በማዕከሉ በሚያርፉበት ጊዜም የተሟላ መጠለያና ምግብ ከነአስታማሚዎቻቸው ያቀርባል፡፡ አንድ ሰው ሲሞት የቀብር ማስፈፀሚያ ተብሎ 3 ሺህ ብር ይሰጣል፡፡ የተቀናጀ በምልአት መርዳት የሚችል ድርጅት ስለሆነ ለህሙማኑ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ህሙማኖቻችን ሼር ሆልደሮቻችን ናቸው ነው የምንለው፡፡ ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን እስካሁን ከ3 ሺህ በላይ ህሙማንን ከአስታማሚዎቻቸው ጋር ረድቷል፡፡ አሁን ላይ 176 ህሙማን ከአስታማሚዎቻችው ጋር አሉ፡፡ ለህሙማኑ የትራንስፖርት ገንዘብ ሰጥተን ፣ ምግብና መጠለያ አመቻችተን፣ የምርመራና የመድሃኒት ወጪ ሸፍነን ለአስታማሚዎቻቸውም አስፈላጊውን ሁሉ አድርገን ነው እየረዳናቸው ያለነው፡፡ ሠራተኞቻችንን በተመለከተ ላለፉት 14 ዓመታት ያሉትን ለውጦች እያየሁ ነውና አሁን የደረስንበትን ደረጃ ሳስበው እንደህልም ነው የሚታየኝ፡፡ በርግጠኝነት ነገ በተሻለ አቅም የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡ሁሉም ሰራተኛ በአግባቡ አስቦ የሚሰራ ስብስብ ነው፡፡ በስራ የሚመጣ እንጂ የሚተዋወቅ የለም፡፡ በሙያ ተገምግሞ ስለሚመጣ ሁሉም ሰው ባለሙያ ስለሆነ ኃላፊነት ተሰምቶት ፣ የተሻለ ነገር ለመስራት አቅዶ የሚሰራ ስለሆነ በዚያው ልክ ደግሞ ድርጅቱም ያከብረዋል፡፡

ፋውንዴሽናችን በየዓመቱ የሚያደርገው ጭማሪና ማነሳሻና አቅም ለመገንባት የሚያደርገው ጥረት እንዲሁም ሰራተኛው ከሌሎች ሰራተኞች እንዳያንስ ጥቅማ ጥቅሞችን በማመቻቸት የተለየ ነገር ያደርጋል። በኛ ሠራተኛ ንጉሥ ነው። የኛ ድርጅት አንዱ መለያው የሚተገብራቸው ሁሉ በመመሪያ የተቀመጡና የተፃፉ ናቸው።

ህሙማኑን በተመለከተ ከተፃፉ ነገሮችም በላይ አልፈን ሄደን የምናደርጋቸው ነገሮች አሉ። የተቋቋመው ሰው ለመርዳት ስለሆነ መመሪያ ማነቆ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች አሉ። ወደ 40 የሚጠጉ መመሪያና ማንዋሎች አሉን። ሁሉም ነገር በመመሪያና በደንብ ነው የሚከናወነው። "ማንም ሠራተኛም ሆነ ኃላፊ የራሱን ዘመድ መቅጠር አይችልም " የሚለው በመመሪያችን ላይ አለ፤ ይከበራል። ሠራተኞቻችንም መመሪያዎችን አክብረው የሚሰሩ ናቸው።

**በአጠቃላይ 43 የሚሆኑ ቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች አሉን 35ቱ ቋሚ ናቸው። በየዓመቱ የሠራተኞቻችን ቁጥር እየጨመረ ነው የመጣው። 20ኛ ዓመታችንን ካከበርን ወዲህ በአንድ ዓመት ብቻ ቁጥሩ 17በመቶ ጨምሯል። አንድ ብቻ አስተዳደርና ፋይናንስ ስንቀጥር ሌሎቹ በሙሉ የህክምና ዶክተሮች ናችው። የህክምና ባለሙያ ያበዛነው የምንሰራበት ዘርፍ እየበዛ የምንሰጠውም አገልግሎት እየሰፋ ፋውንዴሽኑን የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ይመች ዘንድ ሙያተኞቹን የህክምና ትምህርትና ልምድ ያላቸው አድርገናል። 8 ዶክተሮች አሉን፣ 16ቱ ማስተርስ ዲግሪ አላ ቸው፣ የተቀሩት ዲግሪና ዲፕሎማ አላቸው ። በማኔጅመንታችን "The right person to the right place" የሚለው ስለሚከበር ትክክለኛውን ሰው ለትክክለኛው ቦታ እያደረግን እየሰራን ነው። የሰው ኃይላችን በቁጥርም በብዛትም እያደገ ነው ያለው። ይህንን የሰው ኃይል ለተጠናከረ አንድ ዓላማ ማሰራት ትልቅ ስኬት ነው።**

ብሮንኮስኮፒና ኢበስ (በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነው) ሌሎችም መሳሪያዎችን ገዝተን ለጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አበርክተናል።ይህም የጤና ሥርዓቱን ለማጠናከር ነው። ስትራቴጂክ ዕቅዶቻችንም በዚህ መንገድ እያደጉ ነው። ከ20ኛ ዓመት ወዲህ ካሉት ለውጦች ሌላው ስማችን ማቲዎስ ወንዱ - የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ በማሻሻል "ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን" እንዲሆን በጠቅላላ ጉባዔ ተወስኗል። ሎጎዎች ፣ መዋቅሮችና ውስጣዊ አደረጃጀቶች ለውጥ እየተደረገባቸው ነው ። ይሄ ለውጥ ነገን ብሩህ የሚያደርግ፣ ሥራዎቻችንም እንዲሰፉ የሚያደርግ ነው።በብዙ መንገድ ውስጣዊና ውጫዊ ለውጦችን በማካሄድ ላይ ነን። ከዓመትና ሁለት ዓመት በኋላ የተሻለ ደረጃ ላይ ነው የምንገኘው።

ፋውንዴሽናችን በጣም የሚታወቅበትና እንደ ምሰሶ የሚወሰደው ከቦርድ፣ ከጠቅላላ ጉባዔና ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቅርበት መስራቱ ነው። ከጤና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን፣ ከክልል ጤና ቢሮዎችና ከሌሎችም የመንግስት ተቋማት ጋር ይሰራል። 21ኛ ዓመት ይዘናል ፤ የጠቅላላ ጉባዔያችን ተቋርጦ የሚያውቀው በኮቪድ ጊዜ ብቻ ነው። ከቦርዱም ሆን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጣም በቅርበት ነው የምንሰራው። የሁሉም ፍላጎት ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥራ መስራት ስለሆነ የኛ ድርጅት እነዚህን አጠናክሮ አቀላጥፎ ስለሚሰራ ጥሩ ግንኙነት አለን።

ድርጅታችን ብዙ አይታወቅም፤ ሥራው ላይ ነው የሚያተኩረው። የተለያዩ ፖሊሲዎች እንዲወጡ በማድረግ በኩልም እገዛ ያደርጋል። ነገር ግን ስራው ላይ በማተኮራችን የሰራናቸውንም ስለማናስተዋውቅ ብዙ ሰው አያውቀንም። በውጭው ዓለም የተለያዩ ሽልማቶችን አግኝተናል። ትልልቅ ደጋፊዎችም ያውቁናል። በሀገር ውስጥ ግን ባለፈው ዓመት የበጎ ሰው ሽልማትን አግኝተናል። ይሄ ሰዎች እያዩን እንደሆነ አመላክቶናል። ነገር ግን የምንሰራውን ያህል ሰዎች አላወቁንም።ለማስተዋወቅም እንሞክራለን ስራችንንም አጠናክረን እንቀጥላለን።

ድርጅታችን የሙያተኞች ስብስብ ነው። አመሰራረቱም አቶ ወንዱ ማቲዎስን በማጣታቸው ሌሎችን ለማገዝ ያቋቋሙት ድርጅት እንደመሆኑ እያንዳንዷን ነገር በጥልቀት ነው የሚመለከቱት። ሌላውም ሰራተኛ የሳቸውን ፈለግ በመከተል በጥንቃቄ ሥራው ላይ አትኩሮ ስለሚሰራ ላለፉት 22 ዓመታት ኦዲት ተደርገናል፤ ምንም ችግርና ጉድለት ተገኝቶብን አያውቅም። ኢፕሳስና ኩዊክ ቡክ ተግባራዊ በማድረግ የተሻለ የሂሳብ አሰራር እንዲኖረን አድርገናል፤ ሌሎችም ትልልቅ ሀገራዊ ፋይዳቸው ከፍ ያሉ ተግባራትን ስናከናውን ድርጅታችንም ሆነ ሰራተኞቻችን ምንም ዓይነት ችግር ተነስቶባቸው አያውቅም። ወደፊትም ምንም አይገጥመንም ብዬ አምናለሁ፤ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር ባህል ስለሆነ ድርጅታችን ዓለማቀፍ ድርጅቶችን ሳይቀር የሚመራበት ሁኔታ አለ።

ለምሳሌ ሳንባ ካንሰር ላይ የሚሰራው ፕሮጀክት ውስጥ መሪ ነን። ሁለት ዓለማቀፍ ግብረሰናይ ድርጅቶችን ማለትም እንደ አምረፍ ኸልዝ አፍሪካና ዶክተርስ ዊዝ አፍሪካ ኩዋም የመሰሉትን ይዘን ሌሎችም ሜሪጆይና የኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲ ተካተውበት  እነዚህን ድርጅቶች በጥሩ አፈጻጸም እየመራን ነው። በተመሳሳይ ከህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከፒ. አይ. ኤች. ባገኘነው የገንዘብ ድጋፍ የኢትዮጵያ ስኳር ማህበር፣ የልብ ህሙማን ማህበርና ሌሎቹንም እየመራ ሥራውን አከናውኗል። ከዩ.ኤስ.አይ.ዲ ለ18 ወራት ስልጠና ወስደን የልህቀት ማዕከል ተብለናል።: ያ ማለት የትኛውንም ፕሮጀክት መተግበር የሚችል ከየትኛውም ዶነር ጋር መስራት የሚችል አቅምና ብቃት ያለው መሆኑ ተረጋግጧል። ስለዚህም ከመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑ፣ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከዓለማቀፍ ድርጅቶች ጋር በቅርበት ይሰራል።

በዚህ ሁሉ ሥራ ውስጥ ለ22 ዓመታት ችግር የሆነብን ነገር የራሳችን የሆነ የሥራ ቦታና መሬት አለመኖር ነው። የካንሰር ህሙማንን በኪራይ ቤት ስናኖር የተከራየነውም ቤት ድንገት ፈርሶ ህሙማኑን ትምህርት ቤት ውስጥ ያስጠለልንበት አሳዛኝ ጊዜ ነበር። የመሬትና የቦታ ጥያቄያችን ተቀባይነት አግኝቶ 10ሺ ካሬ ሜትር ሰሚት ተሰጥቶን በመረከብ ላይ እንገኛለን።

ጤናማ አፍሪካ "Healthy Africa" የሚል ትልቅ ፕሮጀክት አለን። መሬት ስላገኘን እውን እንደሚሆን እንጠብቃለን። ድርጅቱ 14 ዓመት የኖርኩበት ቤቴ ነው። ልጆች አፍርቼበታለሁ ፤ አቅሜን አሳድጌበታለሁ። እንደ አካሌ ነው የምቆጥረው። በተለይ ጤናማ አፍሪካ የተሰኘው ፕሮጀክት በጣም ሰፊ ፕሮጀክት ነው፤ ለአገራችን የሱስ ማገገሚያ ማዕከል፣  የምርምር ማዕከል፣ ትልቅ ሆስፒታል፣ መዝናኛ ማዕከል፣ የህሙማን ማረፊያ፣ ቢሮዎች አሉት። ይህ ቢሳካ የውጭ ምንዛሬን ያስቀራል ፤ገቢም ስለሚኖረው  ድርጅቱ በራሱ ገቢ መተዳደር ይችላልና ይህ ፕሮጀክት ተሳክቶ ማየት እመኛለሁ።



# ጤናማ አፍሪካ

# Healthy Africa

## የልህቀት ማዕከል ማቋቋሚያ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ

ጤናማ አፍሪካ በማህበረሰባችን የሚያጋጥሙ ተደራራቢ የጤና ችግሮችን ለመቅረፍና የጤና አገልግሎት በከፍተኛ ጥራትና ተደራሽነት ለመስጠት ያለመ ፕሮጀክት ሲሆን አገልግሎቱም በዋናነት ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች መከላከል፣ ቅድመ ልየታ፣ ምርመራና ህክምናን ያካትታል፡፡ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ ትኩረት አድርጎ እ.ኤ.አ 2018 የተሰራው ሪፖርት እንዳመለከተው በኢትዮጵያ 52 በመቶ ሞት ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞችና አደጋዎች ሳቢያ ይከሰታል፡፡ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ደግሞ ከ100 ሺህ ህዝብ 554 ሰው በነዚህ ህመሞች ሳቢያ እንደሚሞቱ አሳውቋል፡፡ ይህ ማለት 25 ኢትዮጵያውያን በየሰዓቱ ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ሳቢያ ይሞታሉ እንደማለት ነው፡፡ በምርታማነት ላይ የሚያጋጥመውም ችግርም ከፍተኛ ነው፡፡ ከነዚህ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ዋና ዋናዎቹ የልብና የደም ስር ህመሞች፣ ካንሰር፣ የመተንፈሻ አካላት ህመሞችና ስኳር ሲሆኑ 80 በመቶ የሚሆነውን ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ሳቢያ የሚከሰት ሞት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡ ይህም ኢትዮጵያን 31 ቢሊየን ብር በየዓመቱ እንድታወጣ የሚያደርጋት ሲሆን ይህም ከዓመታዊ የገቢ ምርቷ 1.8 በመቶ ይሆናል፡፡



በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ጫና ለመቀነስ መንግስት ዘላቂ የልማት ግቦች 3.4 ላይ ተመርኩዞ የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል። ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ጤናማ አፍሪካ የተሰኘውን ፕሮጀክት ሲቀርፅ ለዚህ ግብ መሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ በመተማመን ነው። የዚህ ፕሮጀክት ዋና አላማ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ጫና መቀነስ ቢሆንም በቀዳሚነት ለማህበረሰቡ ስለጤናማ የአኗኗር ዘይቤ ግንዛቤ በመፍጠር በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት የተለያዩ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ጠቅላላ አገልግሎት የሚሰጥ እንደ ጤናማ አፍሪካ ያለ ብቁ ተቋም ተፈጥሯል።



## የፕሮጀክቱ ርዕይ

ኢትዮጵያውያንን ተላላፊ ካልሆኑ ህመሞች መከላከልና ለነዚህ ህመሞች ህክምና በመስጠት የአፍሪካ ምሳሌ ማድረግ

## የፕሮጀክቱ ተልዕኮ

በአፍሪካ አገራት ለህዝብ ሁሉ ተደራሽ፣ ጥራት ያለውና ፍትሃዊ የጤና አገልግሎት እንዲኖር መርሀ ግብር ማቅረብ ነው። በተለይም ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን (NCDS) በመከላከልና መቆጣጠር፣ በምርመራና በጤና እውቀት ማስጠንቀቂያ ላይ ትኩረት በማድረግ ጤናማ ኑሮን ማበረታታት ነው።

## የፕሮጀክቱ ግብ

በኢትዮጵያ እየጨመረ የመጣውን የተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ጫና ለመቀነስ ማህበረሰቡን በማስተማር ፣ በመከላከል፣ በመመርመርና በጊዜ በማከም እንዲሁም በምርምር ላይ መስራትና የልህቀት ማዕከል በመሆን በሀገር ውስጥና ከሌሎች አገራት ታካሚዎችን በመቀበል የሚሊዮኖችን ህይወት ማዳንና ለውጭ ህክምና የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማዳን።

## የፕሮጀክቱ ዓላማ

ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን በተመለከተ በማስተማር፣ ህመሞቹን በመከላከል፣ በመመርመር፣ በማከምና ህሙማንን በመንከባከብ የኢትዮጵያን አቅም በዘርፉ ከፍ ማድረግ።

ጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት የራሱ አርማና ምልክት የሚኖረው ሲሆን ጽ/ቤት ኖሮት ሥራዎቹም በራሱ ድረ-ገጽና ማህበራዊ ሚዲያዎቹ የሚገለጽ ይሆናል።

ጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን በመከላከልና በማከም ህሙማኑ እንዲያገግሙ ከማድረግ ባለፈ የምርምር ስራዎችንም አጠቃሎ የያዘ ነው። ደሃ ተኮር በመሆኑ ዘላቂ አገልግሎት እንደሚሰጥም ታምኖበታል። ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በመፍጠርና ህመሞቹን መከላከልና ምርመራው ላይ በማተኮሩ በተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች የሚያጋጥመውን ሞት በመቀነስ የህሙማኑና የቤተሰቦቻቸውን ስቃይ ይቀንሳል፤ ታክመው የመዳን ዕድላቸውንም ይጨምራል።

ፕሮጀክቱ የምስራቅ አፍሪካ የጤና ቱሪዝም መዳረሻ በመሆን ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት የሚያበረክተው አስተዋፅኦም ከፍተኛ ነው። የተሻለ ምርመራና ህክምና በመስጠት ብቻ ሳይሆን ለህሙማኑ በሚሰጠው የላቀ ድጋፍና አገልግሎት ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም በተመጣጣኝ ክፍያ አገልግሎት የሚያገኙ ብዙ ይሆናሉ።

ይህ ብቻ ሳይሆን በርካታ ኢትዮጵያውያን ህክምና ፍለጋ ከኢትዮጵያ መሄዳቸውን በማስቀረት የውጭ ምንዛሬን ያድናል። ለተለያዩ የስራ ዘርፎችም አዳዲስ የስራ ዕድሎችን ያመቻቻል።



## የምርመራና ህክምና የልህቀት ማዕከል

የጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት ዋናው አካል ይህ የምርመራና የህክምና የልህቀት ማዕከል ሲሆን ተላላፊ ላልሆኑ ህመሞች ብቻ ሳይሆን ለተላላፊዎቹም ያገለግላል። ማዕከሉ ለጊዜው 500 አልጋዎች የሚኖሩት ሲሆን ጥራት ባላቸው የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች የተሟላ ሲሆን ህክምናውም ውጭ መሄድ ሳያስፈልግ ዓለምአቀፍ ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል።  የህጻናት የካንሰር ህክምና አገልግሎት መስጫው በኢትዮጵያ የልጆችን የህክምና ደረጃ የሚያሻሽል ሲሆን ልዩ ህክምና በመስጠት የታካሚዎችንና የቤተሰቦቻቸውን ኢኮኖሚያዊ ጫና የሚቀንስ ይሆናል። ይህም ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀጠና ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን በማከም የተሻለችና ቀዳሚ እንድትሆን ያደርጋል።



## የስነልቦናና ማህበራዊ ድጋፍና እንክብካቤ ማዕከል

ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች የሚያሳድሩትን የስሜትና የስነልቦና ቀውስ በመገንዘብ የስነልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ ማዕከሉ ከህክምናም ባሻገር ሁለንተናዊ የሆነ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል። ታካሚዎች በህክምና መካከል የምግብ፣ የመኝታ፣ የመድሃኒትና የምርመራ አገልግሎትንም በበቂ ሁኔታ የሚያገኙ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ በሚያገኙት የምክር አገልግሎት ታካሚዎችና ቤተሰቦቻቸው ስለህመማቸውና ህክምናው በቂ መረጃ አግኝተው በህሙማኑና በቤተሰቦቻቸው ላይ የሚደርሰውን ስቃይ በመቀነስ ታክመው የመዳን ዕድላቸው ከፍ እንዲል ያደርገዋል።



## የሱስ ማገገሚያ ማዕከል

የሱስ ማገገሚያው ማዕከል በተለያዩ ሱሶች ተጠምደው የሚመጡትን ህሙማንና ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ለመከላከል ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። ትንባሆ ማጨስና አልኮል መጠጣትን እንዲሁም ሌሎችም ሱስ አስያዥና አነቃቂ ነገሮችን  የመሰሉ ጎጂ የሆኑትን ልማዶች አስቀድሞ መከላከል ላይ ቅድሚያ በመስጠት በሱስ ተይዘው ለድጋፍ የሚመጡትን ማዕከሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች የባህሪ ለውጥና ምክክር ላይ ያተኮሩ አገልግሎቶችን  ይሰጣል። በዚህም ማዕከሉ ህሙማኑ በአጭር ጊዜ እርዳታ አግኝተው ወደ ስራቸው እንዲመለሱና ጤናማ ኑሮ እንዲኖሩ ያበረታታል።



## የምርምርና ጥናት ማዕከል

የጤናማ አፍሪካ የጥናት ማዕከል ለፈጠራና ለማስረጃ ማደራጃ እንዲሁም ለዕውቀት ማበልጸጊያ የሚያገለግል ሆኖ ይሰራል፡፡ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን በተመለከተ በተለያየ የሙያ ዘርፍ የሚገኙ መረጃዎችን ዲጂታላይዝ በማድረግ ጥራት ያለው መረጃ እንዲኖር ይሰራል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ከሀገር ውስጥና ዓለማቀፍ አጋር አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ምላሽ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ዓለማቀፍ ልምዶችን ይቀምራል፡፡ የሚያመነጫቸው መረጃዎችም ሀገራዊ ጥቅማቸው የጎላ ይሆናል፡፡



## እጅግ ዘመናዊ ሆቴል


ፕሮጀክቱን በዘላቂነት ለመደገፍ እንዲሁም በመላው ዓለም የሚገኙ ባለሙያዎች የተለያዩ ፈቃዶች ወስደው ለተወሰነ ጊዜ መጥተው የሚያርፉበትና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እየተዝናኑ የተለያየ ምርመራ የሚያደርጉበትና የሚዝናኑበት እንዲሁም የጤናማ አኗኗር ጥበብ የሚገበዩበትን ዕድል   ታሳቢ በማድረግ ጤናማ አፍሪካ እነዚህን የሆቴልና የመዝናኛ አገልግሎቶች ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ያቀርባል፡፡ ከእነዚህ አገልግሎቶች የሚገኘው ገቢ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ለማከም የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ይሆናል፡፡ በተለይ የኢትዮጵያን የጤና ቱሪዝም በማጠናከር በኩል አገራችንን መዳረሻ ያደርጋታል ተብሎ ታምኗል፡፡



## ቢሮዎች

ለመስራት የታሰበው ባለ 7 ወለል ህንጻ አስተዳደራዊ ስራዎችን ዘመናዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ከቢሮ ስራ በተጨማሪ የስብሰባ አዳራሽና የስልጠና ማዕከል በማዘጋጀት ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር ለመስራት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡

## ጫካ ሀይቅና የቤት ውስጥ ማዘውተሪያዎች



ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን መከላከልና ከሱስ ማገገም ሲታሰብ አረንጓዴ ስፍራ፣ የተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያ አማራጮች  ማለትም ጎልፍ፣ የእግር ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ የእጅ ኳስ ፣ መዋኛ፣ የባህር ላይ ቀዘፋ አማራጮችን በከፍተኛ ጥራት ሰርቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለአገልግሎት በማቅረብ ለህሙማን ብቻ ሳይሆን ጤናማ የሆነው የህብረተሰባችን ክፍል ጊዜውን ጤናማና አዝናኝ በሆነ አኳኋን እንዲያሳልፉ ያበረታታል፡፡ መለስተኛ ሀይቅና ከቤት ውጪ የስፖርት ማዘውተሪያዎች ጤናን ለመጠበቅ አስፈላጊ በመሆናቸው በጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት ተካተዋል፡፡ አረንጓዴ ስፍራ፣ የእግር ጉዞ መንገድና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት የአካል ብቃት እንቅስቃሴን የሚያበረታታ ሲሆን የመዝናናት ስሜትንም ይፈጥራል፡፡ ይህም ጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት ያቀደውን አገልግሎት እንደሚሰጥ ማሳያ ነው፡፡

## የፕሮጀክቱ አሁናዊ ሁኔታ

ጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክትን ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ እርምጃ ተራምዷል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ድጋፍ የአዲስ አበባ መሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ በለሚኩራ ክፍለ ከተማ ሰሚት እጅግ በለማና የተለያዩ አገልግሎቶች የተሟሉለት አካባቢ 10 ሺህ ካሬሜትር መሬት ለፕሮጀክቱ አስረክቧል፡፡ ይህ ስኬት ለፕሮጀክቱ እውን መሆን ትልቅ መሰረት ነው፡፡ መሬቱ መሰጠቱ መንግስት ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ለመከላከል የያዘውን ቁርጠኝነት ያሳያል፡፡ ቀጣዩና ዋናው ተግባር መሬቱን ተረክቦ ሀብት ለማሰባሰብ ኢትዮጵያውያንንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማሳተፍ ግንባታውን መጀመር ይሆናል፡፡

## ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው ሀብት የሚሰበሰብባቸው አማራጮች

1. ይህ ፕሮጀክት የሶሻል ኢንተርፕራይዝ ሞዴል ሲሆን ለትርፍ የተቋቋመ ሆኖ ደሃ ተኮርና ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም የተቋቋመ በመሆኑ ባለድርሻ አካላት በየዓመቱ የሚያገኙትን የተወሰነ ወይም በዘላቂነት ባለድርሻ አካላት በሚወስኑት መሰረት አይወስዱም፤ ይልቁንም ፕሮጀክቱን ይበልጥ ለማጠናከር መልሶ ይውላል፡፡ የባለድርሻ አካላቱ ትርፍ አገርና ወገን ጤናማ ሆነው ማየት ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት አክሲዮን ይሸጣል፤ይህንንም ለማድረግ የሚያበቃ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
2. የፕሮጀክቱን ህልውና በዘላቂነት ለማስቀጠል የተለያዩ  የገቢ ማስገኛ አማራጮችን(Income Generating Activities) ሥራ ላይ ያውላል፡፡ በንግድ፣ በግብርና ፣ በሆቴል፣ በመዝናኛ አገልግሎቶች ላይ ያተኮሩ የንግድ ሥራዎች ላይ ይሳተፋል፡፡
3. ለፕሮጀክቱ ሀብት ማሰባሰቢያ የተለያዩ ፕሮግራሞች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን አማራጮች ይቀርባሉ፡፡ፕሮግራሞቹ በምርምርና ስርፀት ላይ የተመሰረቱ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን የሚያበረታቱና አዝናኝ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
4. ይህ ፕሮጀክት ኢትዮጵያ በዘርፉ ያለባትን ክፍተት ለመድፈን የሚሰራ በመሆኑ ቋሚና ዘላቂነት ያለው ድጋፍ ያደርጋል ፤ በዚህም ዓመታዊ በጀት በመመደብ የተለያዩ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡
5. የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡
6. ይህ ፕሮጀክት በዓይነቱ ልዩና ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን ለኑሮና ሥራ አመቺ እንዲሆኑ ለማድረግ አቅዶ የሚሰራ በመሆኑ የተለያዩ የንግድና እርዳታ ድርጅቶችን ከፕሮጀክቱ አካሎች አንዱን መርጠው ሙሉ ወጪውን በመሸፈን ሰርተው ሲያስረክቡ በእነሱ እንደተሰራ ጎልቶ በማዕከሉ ላይ ይጻፋል፤ይህም በመገናኛ ብዙሀን እንዲገለጽ ይደረጋል፡፡ በመላው ዓለም በዘርፉ የታወቁት እንደ ጆን ሆፕኪንስና ታታ ፋውንዴሽን ወዘተ… የመሳሰሉት ድርጅቶችን ልምድና የሥራ ተሞክሮ ከግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል፡፡
7. በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚገኙ ድርጅቶችና ግለሰቦችን በውርስና በድጋፍ የተለያዩ እርዳታዎችን እንዲሰጡ ያበረታታል፤ ለዚህም በቂ እውቅና ይሰጣል፡፡
8. ይኸ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ውስጥ መቋቋምና መገኘቱ እንጂ ከመጠሪያው ጀምሮ የአፍሪካን ስም የያዘ በመሆኑ በአፍሪካ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ ድርጅቶች፣ የተለያዩ የቴሌኮም ድርጅቶችና ባንኮች በሚሰጡት አገልግሎት ላይ አነስተኛ ጭማሪ በማድረግ የፕሮጀክቱን ሙሉ ወጪ ወይም የተወሰነውን እንዲሸፍኑ ያበረታታል፡፡በዚህ ረገድ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከኢትዮ ቴሌኮምና ሳፋሪኮም ወዘተ… ብዙ ይጠበቃል፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየርመንገድ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ዓለማቀፍ አየር መንገድ በመሆኑ በየዓመቱ ከሚያመላልሳቸው 20 ሚሊዮን መንገደኞች ላይ 5ዶላር ለፕሮጀክቱ ዓላማ ቢጨምር በአንድ ዓመት ብቻ 100 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት ይችላል፡፡ ይህም የፕሮጀክቱ ሙሉ በጀት ስለሆነ ፕሮጀክቱ በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ለአፍሪካ አህጉርና ህዝቦቿ ያበረከተው እጅግ የላቀ አስተዋጽኦ ሆኖ ይመዘገብለታል፡፡ በተጨማሪም ከመላው አፍሪካ ወደ አዲስ አበባ ለህክምና የሚመጡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተጨማሪ መንገደኞችን ለማግኘት ያስችለዋል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታም የቴሌፎን ድርጅቶች በእያንዳንዱ ጥሪ ላይ መጠነኛ ዋጋ በመጨመር የፕሮጀክቱን ሙሉ ወይም ከፊል ወጪ መሸፈን ይችላሉ፡፡

## የፕሮጀክቱ ተግባራዊነት፣ ዘላቂነትና አዋጭነት

ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያና ህዝቦቿን እየከፋ ከመጣው የጤና ችግር ለማዳን የተቀረጸ ቢሆንም ዘላቂነትና አዋጭነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል። ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት ፋውንዴሽኑ ከፍተኛ በጀት በመመደብ በዘርፉ ከፍተኛ ብቃትና የሥራ ልምድ ያላቸውን በማወዳደር አሸናፊ በሆነው አማካሪ ድርጅት የአዋጭነት ጥናት አስጠንቷል።ጥናቱም የፕሮጀክቱን የውስጥ ድርጅትና አደረጃጀት በሰው ኃይልና በመሳሪያ የሚኖረውን ገፅታ ለይቶ ያሳየ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ የኦፕሬሽንና ካፒታል ወጪዎችን ግምት አሳይቷል። ምንም እንኳን ደሃ ተኮርና ኢትዮጵያና  አፍሪካን ምቹ የመኖሪያና የመስሪያ ቦታ እንዲሆኑ የሚሰራ ድርጅት ቢሆንም እንደማንኛውም አትራፊ ድርጅት አዋጭና አትራፊ መሆኑን አረጋግጧል።

## የድጋፍና ትብብር ጥሪ

ጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት ስራውን ሲጀምር ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ለመከላከልና ለማከም የሚደረገውን ጥረት ከፍ የሚያደርግ ነው። ከባለድርሻ አካላት፣ ለጋሾችና የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር ጥምረት በመፍጠር ግንባታውን ለማስጀመር ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን በመሆኑም፡-




**ከማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ጋር እጅ ለእጅ በመያያዝ ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች የሚደርሰውን ሞት በመቀነስ የሚሊዮኖች ኢትዮጵያውያንን ህይወት መታደግ ይቻላል። ኢትዮጵያ በጤናው ዘርፍ የቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆን ሁሉም ሰው እንዲሳተፍ ጥሪ እናቀርባለን።**



# በማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የሃብት ማሰባሰብ፣ አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር

**ዶ/ር መታሰቢያ ዘውዱ**

### ድርጅቱንና አቶ ወንዱን እንዴት አገኘሻቸው? ብርታታቸውን ግለጪልን?

ድርጅቱን እጅግ ድንቅ ሆኖ ነው ያገኘሁት። የልጅ ሃዘንን ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር የብዙ ታካሚዎችን ህይወት መታደግ ትልቅ መሰጠትና መልካም ልብን ይጠይቃል። አቶ ወንዱ ደግሞ ይህንን በተግባር አሳይተውናል። ህፃን ማቲዎስን ለማስታወስ የመረጡበት መንገድ ለብዙዎች በህይወት መኖር ምክንያት ሆኗል። ይህ ብርታት ደግሞ እጅግ ያስደንቃል። ድርጅቱ የሚመራባቸው መሰረታዊ እሴቶች አብሮነት፣ ትብብር፣ ፍቅርና እንክብካቤ ናቸው። አቶ ወንዱ እንደ አለቃም እንደ አባትም አቅጣጫ የሚያሳዩን መሪ ናቸው።

ሁልጊዜም የአገልግሎት ጥራታችንን እንድናሻሽልና ትልቅ ነገሮችን እንድናልም ይመክሩናል። ድርጅቱ ውስጥ በጣም ደስ የሚል የቤተሰባዊነት ስሜት አለ። ይህንን ድርጅት በመቀላቀሌ በጣም እድለኛ ነኝ ብዬ አምናለሁ።

### ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ከአጋር ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት ምን ያህል ጠንካራ ነው?

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ከአጋር ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር እጅግ የጠበቀ ግንኙነትና ቁርኝት አለው። ላለፉት 22 ዓመታት ከጤና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን እንዲሁም ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አጋር ድርጅቶች ጋር በትብብር ሲሰራ ቆይቷል። ድርጅቱ እስከዛሬ ላበረከተው አተዋፅኦ የእነዚህ አካላት ሚና እጅግ ቁልፍ ነው። አቅጣጫ በመጠቆም፣ አስፈላጊውን አመራር በመስጠት፣ እንዲሁም የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ከተለያዩ አገር በቀል ተቋማትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ከፍተኛ መተማመን ገንብቷል። እንደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ካሉ ተጽዕኖ ፈጣሪ አካላት ጋር በመሆን በካንሰርና ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ዙሪያ ትልቅ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው የፖሊሲ ለውጦችን ማምጣት ችለናል። ለዚህም ምስክሩ የተቀበልናቸው በርካታ ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ሽልማቶች እንዲሁም በመሬት ላይ ያለው ዘላቂ ለውጥ ነው። በመሆኑም ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ላለፉት ሃያ ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ ውስጥ የገነባው ስም ከሥራ ተቋምነት ባለፈ፣ የፅናትና የጋራ ስኬት ተምሳሌት ሆኗል ብዬ አምናለሁ።

### እንደ ጤና ሚኒስቴር ያሉት የመንግስት አካላት ስለ ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ምን ይላሉ?

የጤና ሚኒስቴር ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽንን በኢትዮጵያ የካንሰር ሕክምናን ለማሳደግና ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ አጋር አድርጎ ይመለከተዋል። ፋውንዴሽኑ በጤና ሚኒስቴር አቅጣጫ ሰጪነት የተለያዩ መከላከል፣ ቅድመ ልየታ፣ ምርመራና ህክምና ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን በመተግበር ለሀገራዊ ስትራቴጂዎቻችን መሳካት ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል።

### በ22 ዓመታት ውስጥ ብዙ ስራ ሰርቶ ታዋቂ ያልሆነው ለምንድነው?

ባለፉት 22 ዓመታት፣ ትኩረታችን ሙሉ በሙሉ "ተግባር ከቃላት በላይ ይናገራል" በሚለው እምነት ላይ የተመሰረተ ነበር። ለታካሚዎች የሚደረግ ሁለንተናዊ ድጋፍ፣ አድቮኬሲ ሥራዎች ቅድሚያ መስጠትና የጤና ሥርዓቶችን ማጠናከር ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫዎቻችን በመሆናቸው፣ ለሚዲያና ለህዝብ እይታ (ፐብሊሲቲ) የሰጠነው ቦታ አነስተኛ ነበር። ይህ አካሄዳችን እንደ ድርጅት ካለን ግዙፍ አሻራ አንጻር ብዙም እንዳንታይ ቢያደርገንም፣ በታካሚዎቻችን ልብ ውስጥ ግን ትልቅ ቦታ እንዲኖረን አስችሎናል።

ይሁን እንጂ ዛሬ ላይ በደረስንበት የእድገት ደረጃ የተቋማችንን ተልዕኮ ይበልጥ ለማስፋፋት ማህበረሰቡ ጋር መድረሳችን ቁልፍ መሆኑን ተገንዝበናል። ለዚህም ሲባል የሀብት ማሰባሰብ፣ አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት በይፋ አቋቁመን ስራ ጀምረናል። ይህ ለውጥ ፋውንዴሽኑ ካካበተው የ22 ዓመታት ልምድ ጋር ተዳምሮ ለነገው ጉዟችን አዲስ ጉልበትና ለተልዕኳችንም ምቹ ሁኔታና ሰፊ አድማስ የሚፈጥር ይሆናል።

### አሁን ትልቅ ፕሮጀክት ነድፏል ለዚህ የማህበረሰቡ ድጋፍ ምን ያህል ወሳኝ ነው?

**የጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት ጥራት ያለውና ተደራሽ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ብቻ ሳይሆን፤ የመከላከል፣ ቅድመ ልየታና የምርምር ሥራዎችን የሚያቀናጅ የልህቀት ማዕከል ነው። ይህም ተላላፊ የሆኑና ያልሆኑ ህመሞች በሃገሪቱ ላይ የሚያደርሱትን ጫና ከመቀነስ አልፎ የምስራቅ አፍሪካ የጤና ቱሪዝም መዳረሻ በመሆን ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ነው።**

**ይሁን እንጂ የዚህ ታላቅ ራዕይ ዕውን መሆን ከመሠረተ ልማት ግንባታና ከባለሙያዎች ክህሎት ባለፈ የሕዝባችንን ንቁ ተሳትፎና ድጋፍ በእጅጉ ይሻል። ማህበረሰቡ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ከመከተል ጀምሮ፣ በግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄዎች ውስጥ በመሳተፍና ለሀብት ማሰባሰብ ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት ለፕሮጀክቱ መሳካት ከፍተኛ አተዋፅኦ ማበርከት ይችላል። በመሆኑም የጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት የሁላችንም የጋራ ኃላፊነትና በሃገር አቀፍ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጠው አጀንዳ በመሆኑ የእያንዳንዱ ዜጋ ድምፅ፣ እገዛና አጋርነት ለስኬቱ ወሳኝ ነው።**

### ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ዲጂታላይዜሽንን የሚያበረታታና ዘመኑን የሚመጥን አሰራር የሚከተል ነው ማለት ይቻላል?

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የአሠራር ስፋቱን ይበልጥ ለማጠናከር እንዲሁም አገራዊው የዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ዕቅድ ለመደገፍ የተለያዩ ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረጉ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። ድርጅታችን ሰው ሠራሽ አስተውሎትን (AI) መሰረት ያደረገ ኢንተርፕራይዝ ሪሶርስ ፕላኒንግ (ERP) የተሰኘ ቴክኖሎጂ በመተግበር ላይ ይገኛል። ይህም የአሠራር ቅልጥፍናን ከማሳደጉም በላይ በሁሉም ስራዎቻችን ውስጥ ከፍተኛ ግልጽነት የሰፈነበት ወጪ ቆጣቢ ሥርዓት እንዲኖር አስችሏል።



# የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የፓንጋሲሌ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ ማዕከል ኃላፊ

**ዶ/ር ኃይማኖት ንጉሤ**

የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን እየሰራቸው የሚገኙት ሥራዎች እንደ ሀገር ብዙም ትኩረት ያልተሰጠባቸው ነገር ግን እጅግ በጣም አስፈላጊ ተግባራት ናቸው፡፡ እኔ በምሰራበት ፓንጋሲሌ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ ማዕከል የሚሰጠው አገልግሎት ካንሰር ከሚያደርሰው የጤና ቀውስ ጎን ለጎን የሚያደርሰውን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጫና ተገንዝቦ ለመቅረፍ ያለመ ተቋም ሲሆን እንደ ማህበረሰብ ከባድ ሸክም የሚያቀል ስለሆነ ትልቅ አክብሮት አለኝ፡፡

**የማዕከላችን ዓላማ ካንሰር የሚያመጣቸውን ዘርፈ ብዙ ቀውሶች ተገንዝቦ እነዚያ ላይ በመስራት ታካሚዎች ሁለገብና አጠቃላይ ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ሲሆን ካንሰርን ቶሎ ለይቶ ህክምና መጀመር የሚያስችል ድጋፍ መስጠት ፣በገንዘብና በማረፊያ እጦት ምክንያት ህክምና እንዳይቋረጥ ድጋፍ ማድረግ፣ ታማሚዎችም ሆኑ አስታማሚዎች የካንሰር ህመምን እስከመጨረሻው እንዲታገሉ በስነልቦና ብቁ ማድረግ ነው፡፡**

ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ከክልል መጥተው ማረፊያ ላጡ በካንሰርና ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች የሚሰቃዩ ሰዎች ከነአስታማሚዎቻችው ማረፊያ መስጠት ፣ታማሚዎች ለህክምና ከክልል ሲመጡና ሲሄዱ የትራንስፖርት ወጪ መሸፈን፣ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የማይገኝ መድሃኒትና ምርመራ ወጪን መሸፈን፣ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለህክምና ሲሄዱና ሲመለሱ ትራንስፖርት ማመቻቸት፣ በማዕከሉ በሚቆዩበት ጊዜ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ለህመማቸው የሚስማማ ገንቢ የሆኑ ምግቦችን ታሳቢ ያደረገ ቁርስ፣ ምሳ ፣ መክሰስና እራት ማቅረብ፤ እንዲሁም በቂ የንጽህና መጠበቂያ መስጠት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በሆስፒታል ተኝተው በሚታከሙበት ጊዜ ለአንዳንድ ወጪዎች መሸፈኛ በወር አንድ ሺህ ብር መስጠትና ህክምናቸውን እየተከታተሉ ወደ ትምህርት ለተመለሱ ልጆች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግና በወር 1ሺህ ብር መስጠት ይገኙበታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ የፕሮግራሞቻችንን የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ወደ ዲጂታል ለማሸጋገር ከጤና ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት እየሠራን እንገኛለን። ይህ ተቋማዊ ትስስር የፋውንዴሽኑ የፕሮጀክት መረጃዎች ከአገራዊው የዲጂታል ጤና ሥነ ምህዳር ጋር ያለምንም እንከን እንዲዋሃድ ያደርጋል። ይህም የመረጃ አያያዝን ለማዘመን፣ የታካሚዎችን የሕክምና ክትትል ደረጃ በደረጃ ለመከታተል፣ የተለያዩ የመረጃ ሥርዓቶችን እርስ በርስ ለማስተሳሰርና አሰራራችንን ለማሳለጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

### አርማና ስያሜውን ለምን ቀየረ? ትርጓሜውስ?

የበፊቱ ስያሜያችን ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ሲሆን ድርጅቱ ለመመስረቱ ምክንያት የነበረውን ህፃን ማቲዎስን ለመዘከርና ድርጅታችን ካንሰር ላይ የሚሰራ ሃገር በቀል ድርጅት መሆኑን ለማመላከት ነበር። ድርጅታችን በህፃናት ላይ የሚከሰት ካንሰርን እንደመነሻ አድርጎ የጀመረ ቢሆንም ላለፉት 22 ዓመታት የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት ሌሎች የካንሰር አይነቶች፣ የተለያዩ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችና አጋላጭ ምክንያቶቻቸው ላይ እየሰራ ይገኛል።

**ተልዕኳችን እየሰፋ ሲሄድ የቀድሞ ስማችን የስራችንን ስፋት ሙሉ በሙሉ እንደማይወክል ለመረዳት ችለናል። ይህንንም ታሳቢ በማድረግ የስም ለውጥ አካሂደናል። አዲሱ ስያሜያችን ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ሲሆን ለድርጅቱ መመስረትና እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው ታካሚዎች መደገፍ ምክንያት የሆነውን ህፃን ማቲዎስን ለማስታወስና ከካንሰር ድጋፍ ባሻገር እየሰፋ ያለውን የድርጅቱን የአገልግሎት ምህዳር ለማሳየት ያለመ ነው። የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን አርማ "ማ" ና "ወ" የሚሉት የአማርኛና** M ና W **የእንግሊዝኛ ፊደላት ላይ የተመሰረተ ሲሆን የልብ ቅርፆቹና የሰው ምልክቶቹ ለሰብዓዊነት የተቋቋመ ድርጅት መሆኑንና መሠረታዊ እሴቶች የሆኑትን ትብብር፣ እንክብካቤንና ፍቅርን ያመለክታል።**

**ሁለቱ ትልልቅ አረንጓዴ ምልክቶች ድርጅቱንና ምልዐተ ጤና ላይ መስራታችንን ሲያመላክቱ አነስ ያሉት ወርቃማ ምልክቶች ደግሞ የምናገለግለውን ማህበረሰብ ያሳያሉ። አርማው ላይ የሚታየው ወርቃማ ቀለም በአለም አቀፍ መድረኮች የሕፃናት ካንሰርን፣ ተስፋና አልበገር ባይነትን በመወከል በሰፊው ይታወቃል። ይህም የህፃናት ካንሰር ላይ ትኩረት አድርገን እደምንሰራና ካንሰርን መቆጣጠር እስክምንችል ድረስ ትግላችን እንደማይቋረጥ ያመላክታል።**

**አረንጓዴው ቀለም ደግሞ ጤናን የአካባቢን ልምላሜና ዕድገትን ሲወክል ዘላቂ የሆኑ የማህበረሰብ ጤናን የሚያስጠብቁ ስራዎችን እንደምንሰራ ያመላክታል። ወርቃማው ቀለም በአርንጓዴ ቀለም መከተሉ ፋውንዴሽኑ ከህፃናት ካንሰር በመነሳት ሰፊና ሁሉን አካታች ወደሆነው የምልዓት ጤና ትኩረቱን እያሰፋ መሄዱን ይወክላል።**

### ለድርጅቱና ለአቶ ወንዱ መልካም ምኞትሽን ግለጪልን?

ለአቶ ወንዱ ሙሉ ጤናንና ረጅም ዕድሜን ከልብ እመኛለሁ። አሁን ላይ ካጋጠማቸው ህመም ሙሉ ለሙሉ አገግመው ለብዙዎች አስተማሪ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም። ፋውንዴሽኑም ከዚህ በላይ ተጠናክሮ በኢትዮጵያና በአፍሪካ የሕክምናን ልህቀት ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚያሸጋግረውን የጤናማ አፍሪካ ፕሮጀክት በድል ዕውን ሲያደርግ ለማየት በጉጉት እጠብቃለሁ።

# የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን የሰራተኞች ዝርዝር

| ክፍል / ዳይሬክቶሬት | ተ. ቁ | የሰራተኛው ስም | የስራ መደብ | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| **ዋና ስራ አስፈፃሚ ጽ/ ቤት** | 1 | አቶ ወንዱ በቀለ | ዋና ስራ አስፈፃሚ | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 2 | ወ/ሮ ወይንሸት ሀይሌ | ኤክስኪዩቲቭ ፀሃፊ | ቢ.ኤ. ዲግሪ |
| **የህሙማን ድጋፍ ማዕከል** | 3 | ዶ/ር ሀያማኖት ንጉሴ | የፓንጋሲሌ የካንሰር ህሙማን ማዕከል ኃላፊ | የህክምና ዶክትሬት |
| | 4 | ዶ/ር ቬሮኒካ ዝናቡ | የፓንጋሲሌ የካንሰር ህሙማን ማዕከል ሐኪም | የህክምና ዶክትሬት |
| | 5 | ወ/ሮ ነብያት ከድር | የምግብ ባለሙያ/ Chef/ | 8ኛ ክፍል |
| | 6 | ወ/ሮ አዲሴ ፋንቱ | ረዳት የምግብ ባለሙያ/ Assistant Chef/ | 8ኛ ክፍል |
| | 7 | ወ/ሮ እታፈራሁ አበበ | ጽዳትና ተላላኪ | 8ኛ ክፍል |
| | 8 | ወ/ሮ አስቴር ታዬ | የህሙማን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ | 12ተኛ ያጠናቀቀች |
| | 9 | አቶ ተፈራ በላይ | የጥበቃ ሠራተኛ | 12ኛ ያጠናቀቀ |
| | 10 | አቶ ታዬ ሃሚካኤል | የጥበቃ ሠራተኛ | 8ኛ ክፍል |
| | 11 | አቶ ሃይሉ ሃደጎ | የጥበቃ ሠራተኛ | 11ኛ ክፍል |
| | 12 | አቶ ዘላለም ዳኛው | የጥበቃ ሠራተኛ | 12ኛ ያጠናቀቀ |
| **ኦፕሬሽን** | 13 | አቶ ለማ አየለ | የኦፕሬሽን ዳይሬክተር | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 14 | ወ/ት ወሰኔጌታነህ | የፋይናንስና አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 15 | ወ/ሮ ማህሌት ወንድይፍራው | ዋና የሂሳብ ሰራተኛ | ቢ.ኤ ዲግሪ |
| | 16 | ወ/ት ብርሃን ሃይሌ | የሂሳብ ሰራተኛ | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 17 | ወ/ሮ ናርዶስ ደረጄ | ሎጀስቲክና ፋይናንስ ኦፊሰር | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 18 | አቶ አሌክስ ዮሴፍ | የጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ | ቢ.ኤ ዲግሪ |
| | 19 | አቶ ኤሊያስ ክበበው | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኦፊሰር | ቢ.ኤ ዲግሪ |
| | 20 | አቶ አስራት አባይ | ሹፌር | ቢ.ኤ ዲግሪ |
| | 21 | አቶ አበብዬ እሸቴ | ሹፌር | 12ኛ ያጠናቀቀ |
| | 22 | አቶ ደጀኔ ታደሰ | የጥበቃ ሠራተኛ | 7ኛ ክፍል |
| | 23 | ወ/ሮ አሰገደች ሽመልስ | ፅዳትና ተላላኪ | 4ኛ ክፍል |
| **ፕሮግራም** | 24 | አቶ ዘላለም መንግስቱ | የፕሮግራም ዳይሬክተር | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 25 | ወ/ሮ ትዝታ ወንድወሰን | የፕሮጀክት ፕሮግራም ሥራአስኪያጅ | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 26 | አቶ ተመስገን ስለሺ | የፕሮጀክት ፕሮግራም ሥራአስኪያጅ | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 27 | ወ/ሮ ቤተልሔም ድረስ | የክትትልና ግምገማ ሥራአስኪያጅ | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 28 | ዶ/ር በሱፈቃድ ሙሉጌታ | የህክምና አስተባባሪ / Medical Coordinator/ | የህክምና ዶክትሬት |
| | 29 | ዶ/ር ምትኩ ቦንሳ | የምርምር አስተባባሪ /Research Coordinator/ | ፒ . ኤች . ዲ |
| | 30 | ሲ/ር ቅድስት ታዬ | ፕሮጀክት ኦፊሰር | ቢኤስ ሲ ዲግሪ |
| | 31 | ሲ/ር አበባ አበበ | ፕሮጀክት ኦፊሰር | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 32 | አቶ አበበ ሻረው | ፕሮጀክት ኦፊሰር | ቢኤስሲ ዲግሪ |
| | 33 | አቶ ቶሎሳ ቶልቻ | ፕሮጀክት ኦፊሰር | ቢኤስሲ ዲግሪ |
| | 34 | አቶ ኤሊያስ ሁሴን | የክትትልና ግምገማ ኦፊሰር | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 35 | ወ/ት ቤዛነሽ መለሠ | የመረጃ ተንታኝ /Data Analyst/ | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 36 | አቶ አዳነ ትኩ | የሳይኮ ሶሻል ድጋፍ ባለሙያ | ቢኤስሲ ዲግሪ |
| | 37 | ዶ/ር ዮናስ ግርማ | የህግ አገልግሎት አማካሪ | የህግ ዶክትሬት |
| | 38 | ዶ/ር ሰመሀል ልኡል | የጥናት አስተባባሪ / Study Coordinator/ | የህክምና ዶክትሬት |
| | 39 | ዶ/ር ዮርዳኖስ ሽፈራው | የጥናት አስተባባሪ / Study Coordinator/ | የህክምና ዶክትሬት |
| | 40 | አቶ አብረሃም ሙሉጌታ | የሳይኮ ሶሻል ድጋፍ ባለሙያ | ቢኤስሲ ዲግሪ |
| **ሃብት ማሰባሰብ ፤ አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት** | 41 | ዶ/ር መታሰቢያ ዘውዱ | የሀብት ማሰባሰብ፤ አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር | የህክምና ዶክትሬት |
| | 42 | ወ/ሮ አዜብ ታምሩ | የህዝብ ግንኙነት ሥራአስኪያጅ | ማስተርስ ዲግሪ |
| | 43 | አቶ እዮብ መርሻ | የሥርዓት አስተዳደር/System Administrator/ | ቢኤ ዲግሪ |




# የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን አመራሮች በኮፕ 11 ስብሰባ፣ ጄኔቫ

cop11

**20 years of change.**
**Uniting generations for a tobacco-free future**

**Geneva, Switzerland**
**17-22 November 2025**

COP 11
17-22 November 2025
Geneva, Switzerland

FCTC
WHO FRAMEWORK CONVENTION ON TOBACCO CONTROL

ህፃናት ህሙማኑ ወደ እኛ የሚላኩት ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሲሆን ሌሎቹ ከተለያዩ የህክምና ተቋማት ነው። ቀደም ሲል ባደረግነው ስምምነት መሰረት ህሙማኑን ለማገዝ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ያላቸውን ታሪካቸውን በተዘጋጀ ቅጽ ላይ ሞልቶ ያስረክበናል። እስካሁን በማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ከአምስት ሺህ በላይ ህሙማን ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። አሁን ደግሞ 176 ህሙማን ከነ አስታማሚዎቻቸው ድጋፍ እያገኙ ነው። እነዚህን ህሙማን ለመርዳት በአሁኑ ወቅት ቋሚ የሆነ የውጭ ድጋፍ የሚያደርግልን አካል የለም። ዓላማው ልባቸውን የነካ በጎ ፈቃደኞች ድርጅቱን በገንዘብም ሆነ በቁሳቁስ ይደግፋሉ። በዚህ አጋጣሚ ሁሉም ሰው በአቅሙ ድጋፍ እንዲያደርግልን ጥሪ አቀርባለሁ።

አስታማሚዎች ጋር ከፍተኛ የሆነ የመንፈስ መረጋጋትና ደስታ ነው ያለው።ምንም እንኳን በካንሰርና ሌሎች ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ህክምና ሂደት ውስጥ ሀዘን፣ ጭንቀትና ፍርሃት ቢኖርም ድርጅቱ እንደቤተሰብ ሆኖ ከባዱን ሥራ አቅልሎ አለኝታ ስለሆናቸው ሁልጊዜም ደስታና ምስጋናቸውን በእንባ ጭምር ነው የሚገልፁት ምክንያቱም ከዚያ በፊት የሚያሳልፉት ውጣ ውረድ እጅግ በጣም ከባድ ስለሆነ እኛጋ ከመጡ በኋላ ተረጋግተው ህክምናቸውን ይከታተላሉ።

የካንሰር ህመም ከፍተኛና ዘርፈብዙ ቀውሶችን ያመጣል ፤ በተለይ እንደኛ ያሉ ታዳጊ ሀገራት ላይ ህክምናው ውስን በሆኑ ቦታዎች በመሰጠቱ ምክንያት አብዛኛው ሰው በማረፊያ እጦት፣ ስለካንሰር በቂ መረጃ ባለማግኘት፣ በሰነልቦና ዝግጅት ማነስና በሌሎችም ችግሮች ከፍተኛ ለሆነ የገንዘብ ወጪ ይዳረጋል። በዚህም ምክንያት ተስፋ በማጣት ህክምናውን ለማቋረጥ ይገደዳል። ይህ እንዳይሆን ነው የምንሰራው።

ከምስረታው ጀምሮ በማዕከሉ ህክምናቸውን እየተከታተሉ ቆይተው በጥሩ ጤንነት ላይ ያሉ አሉ። በየጊዜው ምርመራ ያደርጋሉ በሙሉ ጤንነት ላይ መገኘታቸው አሁን ህክምና ለሚከታተሉት ትልቅ ተስፋ ነው። ያለፉበትን ውጣውረድ በማየት አሁን ለሚገኙበት የጤንነት ደረጃ ድርጅቱንና ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ።

ለህሙማኑ በምናደርገው ድጋፍ ከፍተኛ ችግር የሆነብን ማዕከሉ ድጋፍ የሚሰጥበት የራሱ የሆነ ማረፊያ አለመኖሩ ነው። ከፍተኛ ለሆነ የቤት ኪራይ ወጪ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች ቤት በመልቀቅና ሌላ ቤት በመፈለግ በጣም ተቸግረን ነበር:::: ለህሙማኑ አመቺ የሆነ ቦታ ማግኘት አለመቻል ለከፍተኛ እንግልት ዳርጎን ነበር::::

ማዕከሉ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች አሉት ፤ በሀገር ውስጥ ሰዎች እንዲያውቁት፣ እንዲጎበኙትና ድጋፍ እንዲደርጉለት የተለያዩ ስራዎችን የመሥራት ዕቅድ አለው። ከጤና ተቋማት ጋር በመስራት ድጋፍ የሚያደርግላቸውን ህሙማን ቁጥር ጨምሮ ተደራሽነቱን ለማስፋት እየሰራ ነው። የረጅም ጊዜ ዕቅዳችን ደግሞ "ጤናማ አፍሪካን" መገንባት ነው። ይህ ትልቅ ለሀገር የሚጠቅም ፕሮጀክት ዘርፈ ብዙ አገልግሎት የሚሰጥበት በመሆኑ ስኬታማ ሆኖ ማየት እመኛለሁ።




# ማፓዎ አይበገሬዋ ቀንበጥ

# ከማፓዎ ጋር ...

ማፓዎን ያገኘኋት በማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን እንግዶች ማረፊያ ውስጥ ነው፡፡ግቢውን አልፌ ወደ ሳሎኑ ስዘልቅ በልዩ ፈገግታ ተቀበለችኝ፡፡ የካንሰር ህክምናዋን እየተከታተለች ነው፡፡ ሰውነቷ ተጎድቷል፡፡ ውስጤ ክፉኛ አዘነ ፡፡የሁለተኛ ክፍል ተማሪ መሆኗን አወጋችኝ፡፡አተኩሬ እያየኋት በእሷ ላይ ያለፈውን መከራ  አሰብኩት፡፡ ማፓዎ የማይቻለውን ችላ እያለፈች ያለች ጠይም ዕንቁ፡፡  ስለነገዛሬን በጽናት የቆመች አይበገሬዋ   ቀንበጥ፡፡

## በራዊጋ ...

ጎፋ ዞን ዛላ ወረዳ ፡፡  የ‹‹በራዊጋ›› ለም  ምድር  ሁሌም  የሰጧትን  ታበቅላለች፡፡ ከአገሬው   እጅ የምርት በረከት  አይነጥፍም ፡፡ ከመንደሩ  ነዋሪዎች    ደግሞ  የአቶ ሞሰበ  ቤተሰብ   ይለያል፡፡    ከቀናት በአንዱ በአቶ ሞሰበ እልፍኝ  አንዲት  ቆኝጅዬ ጨቅላ ሰፈውን ቤተሰብ ተቀላቀለች፡፡ይህ  የቤቱ ሲሳይ   ካለፉት ጊዚያት ሁሉ  የላቀ ሆነ፡፡አዲሷ  እንግዳ ከስድስቱ  ወንዶች  ኋላ   የተሰጠች  ልዩ በረከት ነች፡፡ ሰባተኛዋ ልጅ ብርቅዬና  ብቸኛ  ሴት ሆና ተቆጥራለች ፡፡

# ማፓዎ ሰባተኛዋ በረከት

ሰባተኛዋን ብላቴና ዘወትር ቤተሰቡ በስስት እያያት ነው ። ከእሷ ቀድመው የተወለዱ ስድስቱ ወንዶች የተረሱ እስኪመስል ፍቅር ለእሷ አመዝኗል። ጨቅላዋ ማፓዎ እጅግ ታምራለች።በግንባሯ የተደፋው ለስላሳ ጸጉር ከመልኳ ውበት ተዳምሮ ማራኪነቷን ያጎላል።ድንቅዬዋ ህጻን በእናቷ እቅፍ በቤቱ ልዩ ፍቅር ታጅባ ልጅነቷን ጀምራለች። ቆንጆዬዋ ማፓዎ በዕድሜ ጨምራለች ።ከፍ ማለት ስትይዝ ትምህርት ቤት መግባት ከእኩዮቿ መዋል አለባት።ይህን ቀን በጉጉት የሚሹት ቤተሰቦች የሚያስፈልጋትን አሟልተዋል።ማፓዎ ጠይሟ ዕንቁ ውበቷ ዓይን ይስባል፣ዞማ ጸጉሯ ከትከሻዋ ወርዶ ይዘናፈላል። ማፓዎ የቤቱ መብራት ሆና ፍቅርን እያደመቀች ነው።

# ድንገቴው እይታ...

በ2014 ዓም ከቀናት በአንዱ። ከትንሽዋ ቀንበጥ ገላ አንድ ነገር ተስተዋለ።የማፓዎ ሆድ ከወትሮው በተለየ ያልተለመደ ምልክት ታየበት።ምልክቱ በሆዷ ዙሪያ ቆዳዋን ያስቆጣ፣ደም የለበሰ ነበር።ቤተሰቡ ባየው ነገር ግራ ገባው።ሁሉም የቤቱ ስስት የሆነችው ብርቅዬ ልጅ አንዳች እንዲያገኛት አይፈልጉም።ዋል አደር ሲል ምልክቱ ሳይጠፋ ቀጠለ።ይህኔ መላ የተባለው መፍትሔ ሊፈለግ ግድ ሆነ። ማፓዎ ሰባተኛ ልጅ ከሆነች በኋላ ሌሎች ሶስት ልጆች ታክለዋል። አብነት ለቤቱ የመጀመሪያ ነው።አስራአንድ ልጆች ተወልደው አስሩ ባደጉበት ጎጆ ይህ ወጣት የሁሉም ታላቅና የበላይ ሆኖ አድጓል። እሱ ታናናሾቹን በተለየ ሥሥት ያያል። እንደታላቅነቱ ከሁሉም የላቀ ሐላፊነት ይሰማዋል። አሁን በማፓዎ አካል ያስተዋለው ምልክት ወስጡን እያሰጋው ነው።

# ህክምናው ...

አብነት ከቤተሰቦቹ ተማክሮ ማፓዎን ወደ ሕክምና ሊያደርስ ወስኗል።የመጀመሪያው ክትትል ዛላ ወረዳ ላይ ከሚገኝ የግል ክሊኒክ ሆነ።ትንሽዋ ማፓዎ ምርመራ አግኝታ መድሀኒቶች ታዘዙላት።ጉዳዩ በዚህ ብቻ አልበቃም።ለተሻለ ህክምና ወላይታ ሶዶ ወደሚገኘው የመንግስት ሆስፒታል ተጻፈላት። አብነት የትንሽ እህቱ ጉዳይ ሰላም አልሰጠውም።በተባለው መሰረት ማፓዎን ይዞ ወደ ሆስፒታሉ አደረሰ።ሆስፒታሉ ለትንሽዋ ልጅ ተገቢውን ምርመራ አካሂዶ ለውጤቱ አስራ አምስት ቀናትን ቀጠረ።አብነት ቀኑን ቆጥሮ የህክምና ውጤቱን ጠየቀ። የእህቱ ችግር የሳምባ ህመም መሆኑ ተነገረው።ለሶስትወራት የታዘዘላትን መድሀኒት ተቀብሎ ወደቤት መለሳት። ማፓዎ እንደ ቀድሞው ንቁ አልሆነችም።የልጅነት ወዟ ገርጥቷል።ቅልጥፍናዋ ተፋዟል።አሁን የታዘዘላትን መድሀኒት ያለማቋረጥ መዋጥ አለባት።

በወንድሟና በቤተሰቡ ክትትል መድሀኒቷን ወስዳ አጠናቀቀች።መድሀኒቱ በጊዜው ቢያልቅም በማፓዎ ጤና ላይ ለውጥ አልታየም።ዛሬም ትንሽዋ ልጅ ከነህመሟ አሮጌውን ዓመት ተሻግራ አዲሱን ዘመን ይዛለች።

አሁንም በልጅቷ ሆድ ላይ ደም ያዘለ ዕብጠት ይታያል።ሰውነቷ ቀጭጮ ዞማ ጸጉሯ ረግፏል። ይህ ምልክት እናውቃለን ለሚሉት ሰዎች ጥሩ ማሳያ ሆኗል።መፍትሄው በእጃቸው ነውና ወደ ባሕላዊ መድሀኒት አዋቂ ዘንድ አድርሰዋታል። በጤናዋ ላይ የሚጠበቀው ለውጥም አልመጣም። መላው ቤተሰብ ማፓዎ በሆነችው ነገር ሀሳብ ገብቶታል።ሁሉም ስለእሷ ጤና የተሻለውን ለማድረግ እየመከረ ነው። አብነት ዝም አላለም። ከቀናት በአንዱ ያሰበው ተሳካለት። እህቱን ይዞ ከአንድ የግል ሆስፒታል ተገኘ።

# ምርመራን እንደገና...

በሆስፒታሉ ለማፓዎ በአዲስ መልክ ምርመራው ተጀመረ።ትንሽዋ ልጅ በህመም ስትደክም ሰንብታለች።ስትወስደው የቆየችው መድሀኒትና የባህላዊው መንገድ ያለ አንዳች ፈውስ መላ አካሏን አጠውልጓል። ቀናት የፈጀው የሀኪም ቤት ቆይታ ውሎ አድሮ አዲስ ውጤት ይዞ መጣ። አብነት የማፓዎ ምርመራ አራተኛ ደረጃ የደም ካንሰር እንደሚያሳይ ተነገረው። ህመሙ በውስጧ መሰራጨት መጀመሩንም ሰማ። ማዳንን አስቦ ከቤቱ ለራቀው ፣ብዙ ለታገለው አብነት ከባድ ይሉት መርዶ ሆነ ።እሱና አገሬው እስከዛሬ ስለካንስር ሲወራ ይሰማሉ ።ሁሉም ግን ከወባና ትኩሳት የከፋ ጉዳት እንዳለው ገምተው አያውቁም።

ማፓዎ ፈጥና የካንሰር ህክምናውን መጀመር አለባት ። ይህ እንግዳ ጉዳይ በግብርና ለሚተዳደረው ቤተሰብ ደግሞ አስደንጋጭ ዜና ነው። ህክምናው በቀላልና በአጭር ግዜ አይቋጭም። ልዩ ትኩረት፣ በብዙ የሚቆጠር ገንዘብና ትዕግስት ይጠይቃል።
እነ አብነት ያሉበት ሆስፒታል የግል ነው። ከመንግስት ይልቅ በዚህ ቦታ ወጪው ይበረክታል። መድሀኒቱ፣ አልጋው፣ የእለት ወጪው ቀላል አይደለም።አሁን የመጀመሪያውን የኬሞ ቴራፒ እንድትጀምር ታዛለች። ኬሞ የራሱ ሂደትና የበዛ ፈተና አለው። አይቀሬ ህክምና መሆኑ ተነግሯቸዋል።

አሁን በስቃይ ስትዝል፣ስትንገላታ የቆየችው ብላቴና ለሌላው መከራ ራሷን ማዘጋጀት አለባት፡፡ እህትና ወንድም በተባለው ቀን በቦታው ተገኝተዋል፡፡ ለሰድስት ዙር የታዘዘው ኬሞ ቴራፒም አንድ ብሎ ተጀምሯል፡፡ ትንሸዋ ማፓዎ ስቃይዋ በርትቷል፡፡ አካል መንፈሷ በድካም ዝሏል፡፡ ስደስተኛው ዙር አልቆ ለሰባተኛው ቀነ ቀጠሮ እንደተያዘ አብነት ከእጁ ያለው ገንዘብ መሟጠጡን አወቀ፡፡ ከዚህ በኋላ አንድ እርምጃን የሚያርቅ ሰባራ ሳንቲም ከእሱ ዘንድ የለም፡፡ እስካሁን ስለ ማፓዎ ጤና ቤተሰቡ ብድር ገብቷል፣ ቤት ንብረቱን ሸጧል፡፡ አሁን ተፈላጊው ገንዘብ እስኪገኝ ደግሞ ጊዜ መውሰድ ግድ ነው፡፡ እንዲህ ሲሆን ልጅቷ ያለ መፍትሔ ልትቆይ ትገደዳለች፡፡

ማፓዎ ያለመድሀኒትና ህክምና ያሳለፈችው ጊዜ ዋጋ እያስከፈላት ነው፡፡ አሁን ማገገም የጀመረችው ቀንበጥ ዳግም መጠውለግ ይዛለች፡፡ አብነት እህቱን ይዞ ወደ ሆስፒታሉ ሲመለስ ህመሟ አገርሽቶ በእጅጉ ዝላ ነበር፡፡ በወቅቱ ሁኔታዋን ያዩ ሀኪሞች በእሱ ላይ አብዝተው ጮኹበት፡፡ እስካሁን ለምን እንዳቆያት በመውቀስም ጥፋተኝነቱን ሊነግሩት ሞከሩ፡፡

ይህ እውነት በግል ሕክምና፣ በገንዘብ እጦት መከራ ሲያይ ለቆየ ብቸኛ አሳካሚ ልብ ይሰብራል፣ አንገት ያስደፋል፡፡ ታላቅ ወንድም ምርጫ አልነበረውም፡፡ የሚባለውን ቀጣይ ትዕዛዝ ለመስማት ራሱን አዘጋጀ፡፡ አብነት ጥቂት ቆይቶ ከሀኪሞች የደረሰው መረጃ ክፉኛ አስደነገጠው፡፡ ከዚህ በኋላ የእህቱ ህክምና የሚቀጥለው አዲስአበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ ነው፡፡

አብነት እንኳን አዲስ አበባን ወላይታ ሶዶን በቅጡ አያውቅም፡፡ አዲስ አበባ ሰፊና ግራ የሚያጋባ ከተማ መሆኑን ሰምቷል፡፡ እሱ ከጎፋ ቋንቋ የዘለለ አማርኛን በወጉ አይናገርም፡፡ ይህ ሁሉ ሲገባው ራሱን ይዞ አንገቱን ደፋ፡፡ እሱ የሰማውን ለቤተሰቦቹ መልሶ ለመናገር ቃል አንደበት አነሰው፡፡ ወጣቱ ልጅ እህቱን በማሳከም ዓመታትን ቆጥሯል፡፡ እስከዛሬ ወላጆቹ ለብቸኛዋ ሴት ልጃቸው የአቅማቸውን አሟጠዋል፡፡ ሀብታቸውን ከፍለው ቤት ንብረታቸውን ሸጠዋል፡፡ ይህን ሀቅ አሳምሮ የሚያውቀው አብነት የሰማውን እውነት ለእነሱ አድርሶ ሊያሳዝን፣ሊያስደነግጣቸው አልፈለገም፡፡ ራሱን አረጋግቶ ከውስጡ መከረ፡፡ አሁን ማፓዎን ይዞ ወደ አዲስ አበባ መሄድ አለበት፡፡ በእጁ ላይ ከስምንት ሺህ ብር የማይበልጥ ገንዘብ አለ፡፡ ያሰበውን ለመፈጸም አፍታ አልቆየም፡፡ ከሆስፒታሉ የተጻፈለትን ማስረጃና ማፓዎን ይዞ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ገሰገሰ፡፡

# አዲስ አበባ ...

አዲስ አበባና አብነት አይተዋወቁም፡፡ በስፍራው የሚያውቀው ዘመድ፣ የሚቀበለው ቤተሰብ የለም፡፡ እየከፋው፣ ሆድ እየባሰው ሆስፒታሉን ጠይቆ ከግቢው ደረሰ፡፡ የ2017 የመስከረም ወር ፍጻሜ ከሚፈልገው አገናኘው፡፡ ማፓዎን ያዩ የህክምና ባለሙያዎች የመጀመሪያ እርዳታ አደረጉላት፡፡ በመንገድና በበዛ እንግልት የደከመችው ልጅ ህመሙ አሸንፏታል፡፡ አሁንም የሆዷ ላይ ዕብጠት አልጎደለም፡፡ በድንገተኛ ክፍል አልጋ ሰጥተው ለህክምናው አመቻችዋት፡፡ ከሰባት ቀን በኋላ እንደ አዲስ ኬሞ ቴራፒውን ጀመረች፡፡ የሆዷ ዕብጠት መቀነስ ጀመረ፡፡ ዓይኖቿን ገለጠች፡፡ ትንፋሽዋ ተመልሶ አካሏ አገገመ፡፡ ማፓዎ አሁን አስራ አምስተኛ ዓመቷን ይዛለች፡፡ እስካሁን ከሆዷ ዕብጠት ጋር ሀያ ዘጠኝ ኪሎ እየመዘነች ነበር፡፡ ከህክምናው በኋላ ዕብጠቱ መጉደል ጀመረ፡፡ ማፓዎ ዳግም ሚዛን ላይ ቆመች፡፡ አስራ ስምንት ኪሎ ሆናለች፡፡ አብነት ማፓዎን ባየ ቁጥር ውስጡ በሀዘን ይመታል፡፡ እሷ ማለት የልጅ አዋቂ ናት፡፡ ብዙ መከራ አሳልፋ እንኳን ፊቷ ፈገግታ አያጣውም፡፡ ለእናቷ ታዛዥ ለቤቱ አገልጋይ የሆነችው ቀንበጥ ዛሬ የልጅነት መልኳ ከእሷ የለም፡፡ ለዘጠኝ ግዜ በወሰደችው ኬሞቴራፒ ዞማ ጸጉሯ ረግፎ መላ አካሏ ተለውጧል፡፡ ከዘጠኝ ወንዶች መሀል የተገኘችው ብቸኛ ዕንቁ፡፡ የዕድሜዋን ግማሽ ያለፈችው ተነግሮ በማያልቅ ስቃይ ነው፡፡ ዛሬም ግን ደማቅ ፈገግታ ከፊቷ አይጠፋም፡፡ በማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ሙሉ የህክምና ና ተዛማጅ ወጪዋ ተሸፍኖ ውላ እያደረች ህክምናዋን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ትከታተላለች፡፡ አብነት ስለብቸኛ እህቱ ብዙ ዋጋ ከፍሏል፡፡ ስለነገዋ ደግሞ ብዙ ተስፋዎችን ሰንቋል፡፡ እሷን አስተምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ማድረስ ዕቅዱ ነው፡፡



በማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ድጋፍ የሚደረግላቸው ልጆች ሲዝናኑ



ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን 21ኛ ዓመት የምስረታ በዓል አከባበር






ኢመርጂንግ ሚዩዚክ ላብ የተሰኘው የኢትዮ-ጀርመን
አኮስቲክ ጥምረት የካቲት 14, 2017 ዓ.ም
በማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ያካሄደው
ልዩ የሙዚቃ ምሽት




የ2025 የዓለም የካንሰር ቀን ክብረ በዓል



ኒያ ፋውንዴሽን ጆይ የኦቲዝም ማዕከል 65,000.00 የኢትዮጵያ ብር የሚያወጣ የህፃናት ልብስ ድጋፍ ሲያደርጉ



የጤና ሚኒስቴር በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ዴስክ ኃላፊዎች በማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ጉብኝት ሲያደርግ



የላየን ክለብ አባላት ማዕከላችንን በመጎብኘት የተለያዩ ድጋፎችን አድርገዋል



የዘጸአት አፓስቶሊክ ሪፎርሜሽን ቤተ ክርስቲያን ቡድን ዋና መሥሪያ ቤታችንንና ፓንጋሲሌ
የስነ ልቦና እና ማህበራዊ ድጋፍ ማዕከልን ታህሳስ 4 2017 ዓ.ም. ሲጎበኙ




የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ወንዱ በቀለ 70ኛ ዓመታቸውን አክብረዋል፡፡






ሚያዚያ 9 ቀን 2018 ዓ.ም.
የማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን 22ኛ ዓመት
አቶ ወንዱ በቀለና ባለቤታቸው
በተገኙበት ሲከበር



ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በአገር አቀፍ  የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ላይ

# ፋውንዴሽኑ ያገኛቸው ዐበይት ሽልማቶች




በ 2010 ዓ.ም የፋውንዴሽናችን ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ወንዱ በቀለ በተባበሩት መንግስታት ተጓዳኝ ስብሰባ ላይ የ/Enabler of Vision Award/ ሽልማት ተቀብለዋል፡፡

በ2010 ዓ.ም የፋውንዴሽናችን ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ወንዱ በቀለ ፒፕል ቱ ፒፕል ድርጅት በዋሽንግተን ከተማ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ እጅግ የላቀ የማህበረሰብ አገልግሎት /Distinguished Community Service Award/ ሽልማት ተቀብለዋል፡፡

በ 2010 ዓ.ም 1200 አባላት ያሉት ዩ አይ ሲ ሲ /UICC/ የተሰኘው አለም አቀፍ የካንሰር ድርጅት ባዘጋጀው አለም አቀፍ ምርጥ ዋና ስራ አስፈፃሚዎች /CEO/ ውድድር ለመጨረሻ ዙር ካለፉት ሶስት ተወዳዳሪዎች ውስጥ አቶ ወንዱ በቀለ አንዱና ከአፍሪካ አህጉር ብቸኛ ሆነው ተመርጠዋል፡፡

በ2011 ዓ.ም ሶሳይቲያችን ወርየር አጌንስት ካንሰር /Warrior Against Cancer/ ሽልማት ከቢ ኤም ኤስ ኤፍ /BMSF/ በደቡብ አፍሪካ ደርባን በተደረገው ስብሰባ ላይ ተሸልሟል፡፡

በ2012 ዓ.ም በአለም ጤና ድርጅት ከአፍሪካ አህጉር ሜዳሊያ ሽልማት ከተሰጣቸው ስድስት ሰዎች ውስጥ አቶ ወንዱ በቀለ አንዱ ሆነው ትምባሆ የማይጨስበት ቀን ሜዳሊያና ሰርቲፊኬት ተሸልመዋል፡፡

የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ማህበራት ኅብረት 50ኛ ዓመቱን ሲያከብር በመልካም አፈፃፀም ከሸለማቸው ድርጅቶች አንዱ ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ነው፡፡

በ2016 ዓ.ም በተዘጋጀው የበጎ ሰው ሽልማት ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በበጎ አድራጎት ዘርፍ ተሸላሚ ሆኗል፡፡

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን በፋይናንስ አስተዳደርና ፕሮጀክት አተገባበር ከዩ.ኤስ.አይ.ዲ. የልህቀት ማዕከል የብቃት ምስክር ወረቀት ተበርክቶለታል፡፡

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን ከኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲ በሳምባ ካንሰር ህክምና ላይ ላበረከተው አስተዋፅኦ የዕውቅና ምስክር ወረቀት ተበርክቶለታል፡፡

መሪር የቤተሰብ
ሀዘንን ወደ ስኬት የቀየረ

# ታሪካዊ ተልዕኮ!

4ተኛ
ዕትም

# ፍርቱና FERTUNA

www.mathycancersoc.org

ማቲዎስ ወንዱ ፋውንዴሽን
Mathiwos Wondu Foundation


**MWF, HEAD OFFICE AND PSYCHOSOCIAL SUPPORT CENTER**

Queen Elizabeth 11 Street, Kebena
beside Mini Football Stadium
+251-118-122838 /+251-975-414243
80571
www.mathiwos.org
ict@mathiwos.org
wondub@mathiwos.org
https://facebook.com/mwecspage/
Addis Ababa, Ethiopia